ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

በአጠቃላይና መሰረታዊ ጤና ኬላዎች የሚተገበሩ የእናቶች፣ ህጻናት፣ አፍላ ወጣቶች ጤና እና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች ማኑዋል

መጋቢት 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

በአጠቃላይና መሰረታዊ ጤና ኬላዎች የሚተገበሩ የእናቶች፣ ህጻናት፣ አፍላ ወጣቶች ጤና እና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች ማኑዋል

መጋቢት 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ

መግቢያ VIII

የማንዋሉ ዓላማ 1

የማንዋሉ አጠቃቀም 1

የእናቶች፣ ህጻናት፣ አፍላ ወጣቶች ጤና እና የስርዓተ-ምግብ ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ አገልግሎቶች 1

ምዕራፍ 1:- የቤተሰብ ዕቅድ፣ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስነ-የተዋልዶ ጤና አገልግሎት 2

ክፍል 1፡ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት 3

1.1. የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ለማጠናከር የሚከናወኑ ተግባራት 3

1.1.1. ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም 3

1.1.2. ከማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶች ጋራ መስራት 4

1.1.3. ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር 5

1.2. ጥራቱን የጠበቀ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት 6

1.2.1. የምክር አገልግሎት መስጠት 6

1.2.2. የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎችን ለተጠቃሚዎች መስጠት 6

1.2.3. የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ማቀናጀት 7

1.2.4. የሪፈራል አገልግሎት መስጠት 7

1.2.5. በቤተሰብ ዕቅድ ላይ የንቅናቄና ኮሚዩኒኬሽን ስራዎችን መስራት 7

1.2.6. የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ግብዓቶችን ማሟላት 8

1.2.7. መልካም ተሞክሮን መቀመርና ማስፋት 9

1.3. የሚጠበቁ ውጤቶች 9

1.4. ክትትልና ግምገማ 10

1.4.1. የመገምገሚያ ነጥቦች እና የፕሮግራም (የፓኬጅ) መለኪያዎች /indicators/ 10

1.4.2. የግምገማ ማስፈፀሚያ ስልቶች 10

ክፍል 2፡ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት 11

2.1. በመሰረታዊና አጠቃላይ ጤና ኬላ ባለሙያዎች የሚከናወኑ ተግባራት 11

2.1.1. መሠረታዊ መረጃን መሰብሰብ 11

2.1.2. በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ውጤቱን ለኅብረተሰቡ መግለጽና በጋራ የሥራ ዕቅድ ማውጣት 12

2.1.3. ለወጣቶችና አፍላ ወጣቶች የሚሰጡ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅና ማነቃቃት 12

2.1.4. የአቻ ለአቻ አስተባባሪዎች/ አስተማሪዎች ሥልጠና ማካሄድ 12

2.1.5. ስራውን ሊያግዙ ከሚችሉ ድጋፍ ሰጪ አካላት ጋር ቅንጅት መፍጠር 12

2.1.6. ፆታዊ ጥቃትን የመከላከልና ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ 13

2.1.7. መልካም ተሞክሮን ማስፋፋት 14

2.1.8. ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ቀን ማዘጋጀት 14

2.1.9. በትምህርት ቤቶች ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞችን ማስፋፋት 14

2.2. የሚጠበቁ ውጤቶች 14

2.3. ክትትልና ግምገማ 15

2.4. ለፓኬጁ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ መድኃኒትና ቁሳቁሶች 16

ምዕራፍ 2:- የጨቅላ ህጻናት እና ህጻናት ጤና አገልግሎት. 17

2.1. በአጠቃላይና መሰረታዊ ጤና ኬላዎች የሚሰሩ ባለሙያዎች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት 18

2.1.1. የቀበሌውን የህጻናትና ጨቅላ ህጻናት ክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም 19

2.2. የተቀናጀ የጨቅላና የሕፃናት በሽታዎች ህክምናና ክብካቤ (Integrated Management of Newborn and Childhood Illness) 22

2.2.1. የተቀናጀ የጨቅላዎችና የሕጻናት በሽታዎች ሕክምናና ክብካቤ ስልት ዋና ዋና ተግባራት 22

2.2.2. ከሁለት ወር እስከ 5 ዓመት ያሉ ሕጻናት ሲታመሙ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ እንክብካቤና ክትትል እንዲያገኙ ማድረግ 29

2.3. የሚሰጡ አገልግሎቶችና የሚሰጡባቸዉ ቦታዎች 35

2.3.1. በጤና ኬላ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር 35

2.3.2. በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር 35

2.3.3. በቤት ለቤት ጉብኝት ወቀት የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር 35

2.4. አገልግሎቶቹን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች. 36

2.4.1. የስራ አጋዥ (Job Aids) 36

2.4.2. የህክምና ቁሳቁሶች 36

2.5. የሚጠበቁ ውጤቶች 38

2.6. ዋና ዋና መለኪያዎች 39

2.7. ጠቋሚ መረጃዎች (Core Indicators) 39

ምዕራፍ 3:- የክትባት አገልግሎት 40

3.1. በመሰረታዊና አጠቃላይ ጤና ኬላ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት (Activities/interventions) 41

3.1.1. የሁኔታ ትንተና እና ዕቅድ ዝግጅት (Sitautional Analysis and planning) 43

3.1.2. ግንዛቤና ባለቤትነት ማሳደግ 43

3.1.3. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እና በቅንጅት መስራት 44

3.2. የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት 44

3.2.1. የክትባት አገልግሎት ለመስጠት የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች 44

3.2.2. አገልግሎት መስጠት 45

3.3. የቅዝቃዜ ሰንሰለት ቁሶች እና ቁልፍ መልዕክቶቻቸው 46

3.3.1. የቅዝቃዜ ሰንሰለትን መጠበቅና መከታተል 46

3.3.2. የክትባት መድኃኒቶች አቀማመጥ 47

3.4. ፍሪጅ እንዳይበላሽ መደረግ የሚገባቸዉ የቅድመ መከላከል/Preventive Maintenance/ ስራዎች፡- 49

3.5. የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ. 50
3.5.1. የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም ክትትል 50
3.5.2. የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም ግምገማ 50
3.5.3. በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸው በሽታዎች ቅኝትና ዳሰሳ ማካሄድ 50
3.6. አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች 51
3.6.1. መዛግብትና የሪፖርት ቅጻቅፆች 51
3.6.2. የክትባት ትምህርትና የመግባቢያ መርጃ መሳሪያዎች .51
3.6.3. የቀዝቃዜ ሰንሰለት ለማስጠበቅ የሚረዱ ግብአቶች 51
3.6.4. የክትባት መድኃኒቶች እና ሴሎች ቀሳቀሶች 51
3.6.5. የእጅ መታጠቢያ ግብዓቶች 52
3.7. ከክትባት አገልግሎቱ የሚጠበቁ ውጤቶች. 52
3.8. የአገልግሎቱ ዋና ዋና ጠቋሚዎች 52
ምዕራፍ 4:- የእናቶች ጤና አገልግሎት. 56
4.1. በመሰረታዊና አጠቃላይ ጤና ኬላዎች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት 57
4.1.1. ለእናቶችና ጨቅላ ህጻናት የጤና አገልግሎት ለመስጠት የቀበሌውን ሁኔታ ያገናዘበ ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈጸም 58
4.1.2. በቅድመ-እርግዝና፣ በቅድመ ወሊድ፣ ወሊድ፣ ድህረ ወሊድና የጨቅላ ህፃናት ጤናን ለማሻሻል የባህሪ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ትምህርት መስጠት 58
4.2. ቅድመ ወሊድ አገልግሎት መስጠት 60
4.2.1. በመጀመሪያ የቅድመ-መወሊድ ክንታክት/ጉብኝት የሚከናወኑ ተግባራትና የሚሰጡ አገልግሎቶች 60
4.2.2. በሁለተኛው ክንታክት የሚከናወኑ ተግባራት 61
4.2.3. በሶስተኛው ክንታክት የሚከናወኑ ተግባራት 62
4.2.4. በአራተኛው ክንታክት የሚከናወኑ ተግባራት 62
4.2.5. በአምስተኛው ክንታክት የሚከናወኑ ተግባራት .62
4.2.6. በስድስተኛው ክንታክት የሚከናወኑ ተግባራት .62
4.2.7. በሰባተኛው ክንታክት የሚከናወኑ ተግባራት 63
4.2.8. በስምንተኛው ክንታክት የሚከናወኑ ተግባራት .63
4.3. የማዋለድ አገልግሎትና የጨቅላ ህጻናት ክብካቤ 63
4.3.1. በምጥና በወሊድ ጊዜ የሚደረግ ክብካቤ 63
4.3.2. የመጀመሪያ የምጥ ደረጃ (First Stage of labour) 64
4.4. የጨቅላ ሕፃናት እንክብካቤ. 66
4.4.1. በህብረተሰቡ ውስጥ የሚሰሩ ዝርዝር ተግባራት .66
4.4.2. ለሁሉም አዲስ ጨቅላ ሕፃናት አስፈላጊ ክብካቤ (Essential Newborn Care) 66
4.4.3. በተጨማሪ ለእናትየዋ መሰጠት ያለበት ምክር .67
4.4.4. የጨቅላ ሕፃናትን በተመለከተ በቤት ለቤት ጉብኝት ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት 67

4.5. የድህረ ወሊድ ክብካቤ 68
4.6. ደህንነቱን የጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት 70
4.7. ከወሊድ ጋር በተያያዘ ምክንያት የሚከሰት ፊስቱላን መከላከል. 70
4.7.1. ህብረተሰቡን ስለ ፊስቱላ ምንነት የማሳወቅ ስራ መስራት 70
4.7.2. ከወሊድ ጋር የተያየዘ ፊስቱላና የማህፀን መውጣት ተጠቂዎችን ለየታ፣ ምርመራና ሪፈራል 71
4.8. በጎ ፈቃድ ደም ለጋሾችን በመመልመል ደም ማሰባሰብ 72
4.9. የእናቶች ሞት ቅኝትና ምላሽ 72
4.9.1. ህብረተሰቡን ስለ እናቶች ሞት ቅኝትና ምላሽ ማስተማር 72
4.9.2. በህብረተሰቡ ውስጥ የእናቶች ሞት ለየታን ማከናወን 73
4.9.3. በህብረተሰቡ ውስጥ የሞቱትን እናቶች መረጃ ወደ አቅራቢያ ጤና ጣቢያ መላክ 73
4.10. አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች 73
4.10.1. የስራ መርጃ መሳሪያና መመሪያዎች (Job aids) 73
4.10.2. የህክምና ቁሳቁሶች እና ሲኖሩ የሚገቡ የህክምና መድሐኒቶችና የህክምና ቁሳቁሶች 73
4.10.3. በጤና ኬላ ሲኖሩ የሚገቡ የህክምና ግብዓቶችና መድሐኒቶች 74
4.11. በማህበረሰብ/ጤና ኬላ ደረጃ የሚሰጠውን አገልግሎት እንዴት በጤና ጣቢያ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ማስተሳሰር እንደሚቻል 75
4.12. በእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚጠበቁ ውጤቶች 75
4.13. የእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ክትትልና ግምገማ 75
4.14. የእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ መለኪያዎች 76
ምዕራፍ 5:- የስርዓተ-ምግብ አገልግሎት 77
5.1. በመሰረታዊና በአጠቃላይ ጤና ኬላዎች የሚከናወኑ የስርዓተ-ምግብ ተግባራት 78
5.1.1. መረጃ መሰብሰብና ማቀድ 80
5.2. ለነፍሰጡር እናቶች የስርዓተ-ምግብ ሁኔታ ማሻሻል 80
5.3. የሚያጠቡ እናቶች ስርዓተ-ምግብ ማሻሻል 81
5.4. የህፃናት የስርዓተ-ምግብ ማሻሻል. 81
5.5. የወጣቶች ስርዓተ-ምግብ ማሻሻል 82
5.6. የጎልማሶችና አዋቂዎች አመጋገብ እንዲሻሻል ማድረግ 83
5.7. የአረጋውያን ሥርዓተ ምግብ ሁኔታን ማሻሻል 83
5.8. የሕመምተኞች አመጋገብን ማሻሻል 83
5.9. የጥቃቅን ንጥረ ነገሮች እጥረት ችግሮችን መከላከል እና መቆጣጠር 84
5.10. የእድገት ክትትልና ማበልፀግ 86

5.11. የስርዓተ-ምግብ እጥረትን በምርመራ መለየት 87

5.11.1. የአንትሮፖሜትሪ ልኬት 87

5.11.2. የታችኛው እግር እብጠትን ማረጋገጥ 89

5.12. ከፍተኛ የምግብ እጥረት ህክምና 90

5.13. የሥርዓተ-ምግብ ቅንጅታዊ አሠራር 92

5.13.1. ከግብርና ሴክተር ጋር የሚሰሩ ተግባራት፣ 92

5.13.2. ከትምህርት ሴክተር ጋር የሚሰሩ ተግባራት፣ 93

5.13.3. ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዩ ዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር የሚሰሩ ተግባራት 93

5.13.4. ከሥርዓተ-ምግብ ፕሮግራም ተግባሪ ሴክተር መስሪያቤቶች በትብብር መስራት 93

5.14. አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች. 94

5.15. የሚጠበቁ ውጤቶች 95

5.16. ክትትልና ግምገማ 96

5.16.1. ክትትል 96

5.16.2. ግምገማ 96

5.17. የፕሮግራም ጠቋሚዎች 97

መግቢያ

የሀገር ዕድገትና ብልጽግና ሲወሰ የእናቶችና ሕጻናት ሕመምና ሞት ከመስፈርቶቹ ውስጥ ጉልህ ስፍራ አለው፡፡ እንደ የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መርጃ ድርጅት ሪፖርት በዓለም በየዓመቱ 295,000 እናቶች ሲሞቱ ከ5 ሚሊዮን የሚበልጡ ህጻናት አምስተኛ የልደት በዓላቸውን ሳያከብሩ ይሞታሉ፡፡ ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት ባከናወነችው ዘርፈ ብዙ የእናቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች እና ስነተዋልዶ አገልግሎት የማሻሻል ስራዎች በእናቶች እና ህጻናት ጤና ዙሪያ ከፍተኛ መሻሻል አሳይታለች፡፡ በዚህም የእናቶች እና ህጻናትን ሞት ምንም እንኳን በሚፈለገዉ ደረጃ ባይቀረፍም በ2011 ዓ.ም የተደረገው የኢትዮጵያ የጤናና ስነ-ህዝብ ጥናት እንደሚያሳየው በሕይወት ከሚወለዱት 1000 ህፃናት 55ቱ አምስት ዓመት ሳይሞላቸው፤ 43 ያህሉ አንድ ዓመት ሳይሞላቸው እንዲሁም 33 ያህሉ አንድ ወር ሳይሞላቸው ይሞታሉ፡፡ በ2009 ዓ.ም የተደረገው የኢትዮጵያ የጤናና ስነ-ህዝብ ጥናት እንደሚያሳየው የእናቶች ሞትንም ወደ 401 ከ100000 በህይወት ከሚወለዱ ህጻናት መቀነስ ተችሏል፡፡ ሁሉንም ዓይነት ክትባት የተከተቡ ህጻናት 43% ሲሆን እ.ኤ.አ በ2025 ወደ 75% ለማድረስ እየተሰራ ነዉ፡፡ በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትም ዕምርታዊ ለውጦች ቢመዘገቡም የቤተሰብ ዕቅድ መጠቀም እየፈለጉ ያላገኙ 22% ሴቶች ያሉ ሲሆን እ.ኤ.አ በ2025 ወደ 17 በመቶ ለመቀነስ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከተመጣጠነ ምግብ ዕጥረት የሚከሰተውን መቀንጨርን አሁን ካለበት 37% ወደ 25%፣ መቀጨጭ ከ7% ወደ 5% ለመቀነስ እየተሰራ ነዉ፡፡

የህጻናት ጤንነትና ደህንነት ከእናቶች ጤንነትና ደህንነት ከስነተዋልዶ ጤና እና ከስርዓተ-ምግብ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ የእናቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች እና አፍላ ወጣቶች ጤና አንዱ ያለ ሌላ ብቻዉን የሚፈጸም ሳይሆን በህይወት ዑደት በመስራት ሁሉንም ግብ ማሳካት ይቻላል፡፡ በተለይ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሮአዊና ማህበራዊ ለውጦች የሚከሰቱበት የዕድሜ ክልል ላይ በመሆናቸው በቂ የሆነ የጤና አገልግሎት ካላገኙ ለጤናና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ተጋላጭ ናቸው፡፡ በመሆኑም የወጣቶች የተዋልዶ ጤና አገልግሎት በገጠር ውስጥ በማቅረብ እና በማስፋፋት ይህንን ችግር ወሳኝ በሆነ መልኩ መቅረፍ ይቻላል፡፡ የወጣቶቸና አፍላ ወጣቶችን ጤና የተሟላ በማድረግ እና ያልተፈለገ እርግዝናን ማስቀረት ላይ በአግባቡ ከተሰራ የእናቶችን እና የጨቅላ ህጻናትን ሞት በመቀነስ እንዲሁም ዝቅተኛ ክብደት ያላቸዉን ህጻናት መቀነስ ላይ ከፍተኛ ተጸእኖ ይኖረዋል፡፡

በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተደራሽ፣የተሟላ፣ የተቀናጀና ጥራት ያለው ለማድረግ የእናቶች፣የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ የጨቅላዎች እና የሕጻናት በሽታዎች ሕክምናና ክብካቤን፣የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች እና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎት በጤና ኬላ ደረጃ በሥራ ላይ እንዲውል በመደረጉ በእናቶችና ህጻናት ጤና እንዲሁም በስርዓተ-ምግብ ላይ ለውጥ እየተመዘገበ መሆኑን የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ፡ ፡ ይህንን አገልግሎት የበለጠ ለማጠናከርና በጥራት እንዲሰጥ ለማስቻል በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ማሻሻያ ፍኖተ-ካርታው በተቀመጠው አግባብ ለመተግበር እንዲቻል በአጠቃላዩና እና በመሰረታዊ ጤና ኬላዎች ደረጃ የሚተገበሩ የእናቶች፣ ህጻናት፣ አፍላ-ወጣቶችና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶችን የያዘ ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡

የማንዋሉ ዓላማ

የዚህ ማኑዋል ዓላማ በአጠቃላዩ እና መሰረታዊ ጤና ኬላዎች ደረጃ የሚተገበሩ የእናቶች፣ ህጻናትና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎት ተግባራትን በግልጽ በማስቀመጥ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል ነው።

የማንዋሉ አጠቃቀም

የዚህ ማኑዋል ዋና ተጠቃሚዎች በአጠቃላዩ በመሰረታዊ ጤና ኬላዎች ተመድበው የሚሰሩ ሁሉም ባለሙያዎች ሲሆኑ ከጤና ሚኒስቴር ጀምሮ በደረጃው ያለው የጤና መዋቅር፣ፕሮግራሙን የሚደግፉ አጋር አካላት፣ የትምህርትና የምርምር ተቋማትም የሚጠቀሙት ይሆናል።

የእናቶች፣ ህጻናት፣ አፍላ ወጣቶች ጤና እና የስርዓተ-ምግብ ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ አገልግሎቶች

- ✓ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት፣ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት
- ✓ የጨቅላ ህጻናትና ህጻናት ጤና አገልግሎት
- ✓ የክትባት አገልግሎት
- ✓ የእናቶች ጤና አገልግሎት እና
- ✓ የስርዓተ-ምግብ አገልግሎት

ምዕራፍ 1
የቤተሰብ ዕቅድ፣ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስነ-የተዋልዶ ጤና አገልግሎት



1

ክፍል 1፡ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት

1.1. የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ለማጠናከር የሚከናወኑ ተግባራት

ተ.ቁ	ዋና ዋና ተግባራት	መሰረታዊ ጤና ኬላ	አጠቃላይ ጤና ኬላ
1	ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም	✓	✓
2	የምክር አገልግሎት መስጠት	✓	✓
3	የአጭር ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች መስጠት	✓	✓
4	የረጅም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች መስጠት	✓	✓
5	የረጅም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች ማስወጣት፡- ❖ ኢምፕላንትስ ❖ ሉፕ	✓	✓
6	ድህረ ወሊድ (በ48 ሰዓት) የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት ❖ ኢምፕላንትስ፣የሚዋጥ እንክብል (ፒልስ/POP)	✓	✓
	❖ ሉፕ	×	✓
7	የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ማቀናጀት	✓	✓
8	የሪፈራል አገልግሎት መስጠት	✓	✓
9	በቤተሰብ ዕቅድ ላይ የንቅናቄና ኮሚዩኒኬሽን ስራዎችን መስራት	✓	✓
10	መልካም ተሞክሮን መቀመርና ማስፋት	✓	✓
11	ወሉ ገብ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት	✓	✓
12	የተከናወኑ ተግባራትን አፈጻጸም በማጠናቀር ሪፖርት ማድረግ	✓	✓

1.1.1. ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም

በቀበሌ ውስጥ ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ጠቃሚ የሆኑትን መረጃዎች መዝግቦ መያዝ

- ❖ የህዝብ ብዛት
- ❖ የቤተሰብ ቁጥር በዕድሜ፣ በፆታ፣ በሐይማኖት፣በሥራ የገቢ ምንጭ፣ የልደት፣ የስደትና የሞት
- ❖ በመውለድ እድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች ብዛት
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛትና የሚጠቀሙት የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዓይነት
- ❖ አገልግሎቱን ከየት እንደሚያገኙና እንደሚጠቀሙ
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት የማይጠቀሙ ሴቶች ብዛት
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድ የማይጠቀሙ ነገር ግን ለመጠቀም የሚፈልጉ ከ15-49 ዕድሜ ክልል ያሉ ሴቶች ብዛት

- የቤተሰብ ዕቅድ የማይጠቀሙ ነገር ግን ለመጠቀም የሚፈልጉ በተለይ ከ15-19 ና ከ20-24 ዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ብዛት
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት በመጠቀም ላይ የነበሩና የቋረጡ ተጠቃሚዎች ብዛት
- የሚያጠቡ እናቶች ቁጥር

መረጃዎች ከየትና እንዴት ይሰበሰባሉ ?

- የቤተሰብ ጤና ማህደር፣ መዘግብቶችንና ከዓመታዊ ዕቅድና ሪፖርቶች በማገላበጥ
- በቀበሌ ደረጃ ከሚገኙ የተለየየ ሴክተሮች (ለምሳሌ፡- ቀበሌ አስተዳደር፣ ት/ቤት፣ ግብርና፣ ከወሳኝ ኩነቶች ጽ/ቤት፣ ወዘተ)
- ቤት ለቤት በመሄድና ከቤተሰቦች ጋር ውይይት በማድረግ፣
- ከጎጥ ጤና መሪዎች፣ ከልማት ቡድንና ከትስስር መሪዎች፣

መረጃውን መነሻ በማድረግ ወቅታዊ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ መፈጸምና ሪፖርት ማድረግ

- በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዙሪያ ያሉ ችግሮችንና ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ተግባራት በመለየት ማቀድ፣
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ያልሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግና የአገልግሎት ሽፋንንና ጥራትን ለማሻሻል ማቀድ፣
- የተዘጋጀውን ዓመታዊ ዕቅድ በየሩብ ዓመቱ እና በየወሩ በመከፋፈል መፈጸም፣
- የስራ አፈጸጸም በወቅቱ እና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለጤና ጣቢያ ሪፖርት ማድረግ፣

1.1.2. ከማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶች ጋራ መስራት

የጎጥ ጤና መሪዎችንና የሴቶች ልማት ቡድንን ተሳትፎ ማጎልበት

- የጎጥ ጤና መሪዎች የሴቶች ልማት ቡድን መሪዎችን በቤተሰብ ዕቅድ ዙሪያ የሚያከናውኑትን ተግባራት መደገፍ እንዲችሉ ማብቃት፣
- የሴቶች ልማት ቡድን መሪዎችን በቤተሰብ ዕቅድ ዙሪያ ማሰልጠን፣
- የሴቶች ልማት ቡድን መሪዎች በስራቸው የሚገኙትን በወሊድ ዕድሜ ክልል ያሉትን ሴቶች መዝግበው እንዲይዙና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በእቅዳቸው እንዲይዙ ማድረግ፣
- የሴቶች ልማት ቡድን መሪዎች በስራቸው የሚገኙትን በወሊድ ዕድሜ ክልል ያሉትን ሴቶች ስለቤተሰብ ዕቅድ እንዲያስተምሩ ለማድረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- የሴቶች ልማት ቡድን መሪዎች በስራቸው የሚገኙትን በወሊድ ዕድሜ ክልል ያሉትን ሴቶች የቤተሰብ ዕቅድ ስለመጠቀማቸው እንዲመዘግቡና እንዲከታተሉ ማስቻል፣
- የሴቶች ልማት ቡድን መሪዎችን እንደአስፈላጊነቱ በየቤታቸው በመጎብኘት ስራቸውን ማየት፣ ችግሮቻቸውን መፍታትና ማበረታታት፣
- በቤተሰብ ዕቅድ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን ከሴቶች ልማት ቡድኖች ጋር በየጊዜው መገምገም፣ የልምድ ልውውጥ ማድረግና የጋራ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፣

የወንዶችን ተሳትፎ ማጎልበት

- በቀበሌ ደረጃ ወንዶች በብዛት የሚሰተፉባቸው አደረጃጀቶች (የግብርና ልማት ቡድን) ስለ ቤተሰብ ዕቅድ አስፈላጊነት እና የወንዶች ሚና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፣
- የቤተሰብ ዕቅድ ባለመጠቀም ምክንየት በእናቶችና ህጻናት ላይ የሚደርሰውን ችግር ማስረዳት እና ስለጥቅሙ ማስተማር፣
- ለወንዶች አማራጭ የቤተሰብ ዕቅድ መኖሩን ማሳወቅና ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል ማስረዳት፣
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን በተመለከተ ወንዶችን/ባሎችን ያሳተፈ በቤት እና በጤና ኬላ ደረጃ ምክክር ማድረግ፣
- በቀበሌ ደረጃ በሚካሄዱ የሴቶች ኮንፈረንስ ላይ ወንዶችን/ባሎችን ተሳታፊ ማድረግ፣

ለተፅዕኖ ፈጣሪ አካላት የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ጠቀሜታን ማስተዋወቅ እና ማነቃቃት

- በቀበሌው ለሚገኙ ተጽእና ፈጣሪ አካላት (የኃይማኖት አባቶች፣ የጎሳ መሪዎች፣ የእድር መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የቀበሌ መስተዳድር አካላት ወዘተ) በቤተሰብ ዕቅድ ምንነትና አስፈላጊነት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፣
- በቀበሌው ለሚገኙ ተጽእና ፈጣሪ አካላት ለጉዳዩ ስኬታማነት በየዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ህብረተሰቡን የማንቃትና የማስተማር ስራ እንዲሰሩ መጎትጎትና ማስተባበር፣
- በቀበሌው ከሚገኙ ተጽእና ፈጣሪ አካላት ጋር የተከናወኑ ተግባራትና የመጡ ለውጦችን በየጊዜው መገምገምና ልምድ ልውውጥ ማድረግ፣

1.1.3. ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር

- በቀበሌ የሚገኙትን ደጋፊ አካሎችን መለየት
  - ✓ የቀበሌ መስተዳድር፡- አስተዳደራዊ ድጋፍ እንዲሰጥ፣
  - ✓ ግብርና፡- የልማት ሠራተኞች ድጋፍ እንዲሰጡ፣
  - ✓ ትምህርት፡- ለመምህራንና ተማሪዎች ትምህርት በመስጠት ራሳቸው ተጠቃሙ በመሆን፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ እንዲያስተምሩ፣ ወዘተ...፣
  - ✓ በሴቶች/የወንዶች የተደራጁ ልማት ሠራዊትን /የጎጥ ጤና መሪዎች/ በማንቀሳቀስ ስለቤተሰብ ዕቅድ እንዲያስተምሩ፣
  - ✓ ማህበራት (የሴቶች፣የወጣቶች ወዘተ..) ግንዛቤ በመፍጠር በማመቻቸት አባላቶቻቸውን በማንቀሳቀስና በማሳተፍ የድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ፣
  - ✓ የሐይማኖት ተቋማት፡- የውይይት መድረክ በማመቻቸትና በየቤተ-እምነታቸው ተከታዮቻቸውን በመቀስቀስ እንዲያሳትፉ፣
  - ✓ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፡- ሙያዊና በቁሳቁስ ወዘተ.. በመደገፍ
- ከአጋር አካላት ጋር ውይይት ማካሄድና የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ፣
- ዕቅድና ፍላጎትን ማጣጣምና በትብብር መሠራት፣
- የተከናወኑ ተግባራትን በጋር መገምገምና የወደፊት አቅጣጫ ማስቀመጥ፣

1.2. ጥራቱን የጠበቀ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት

1.2.1. የምክር አገልግሎት መስጠት

- ❖ አገልግሎቱን ፈልገው ወይንም ለሌላ አገልግሎት የሚመጡ ተገልጋዮችን በመመሪያው መሠረት (ለምሳሌ፡ በየደረጃው የሚሰጡ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዓይነቶችንና ጥቅማቸውን፣ የጎንዮሽ ጉዳቶችንና መፍትሄዎቻቸውን ጭምር) ጥራቱን በጠበቀ መልኩ የምክር አገልግሎት መስጠት፣
- ❖ ምርጫቸውን መሠረት በማድረግ ተገቢውን የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴ መስጠት፣ መከታተል እና ችግር ሲከሰት ችግሮቻቸውን በአፋጣኝ መፍታት

1.2.2. የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎችን ለተጠቃሚዎች መስጠት

ሀ.የአጭር ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች (ኮንዶም፣ የሚዋጥ እንክብል (ፒልስ)፣ መርፌ፣ ድንገተኛ እርግዝና መከላከያ)– ለአጭር ጊዜ የሚያገለግሉ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች ምርጫቸው የሆኑ ተጠቃሚዎች እንደየምርጫቸውና እንዴት መጠቀም እንደሚገባቸው እንዲሁም ስለጎንዮሽ ጉዳታቸው በአግባቡ በማስረዳት መስጠት፣

ለ.የረጅም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች

- ❖ **በክንድ ሥር የሚቀመጡ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች (ኢምፕላንትስ) አሰጣጥ፡** አያንዳንዱን አሰራር (procedures) ለተገልጋዮች አስቀድሞ መንገር/ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ ዋና ዋና የሚከናወኑ ተግባራት፡-
  - ✓ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን ማዘጋጀት፣
  - ✓ ትክክለኛ የብክለትና የኢንፌክሽን መከላከል አሰራርን መከተል፣
  - ✓ ኢምፕላንቱ በሚሰጥበት ቦታ ላዩ (በላዩኛው የውስጥ ክንድ) ማደንዘዣ መስጠት፣
  - ✓ ኢምፕላንቱ በሚሰጥበት ቦታ (በላዩኛው የውስጥ ክንድ) ቆዳ ላዩ በትንሹ መብጣት
  - ✓ ኢምፕላንቱን በተበጣው ቆዳ ስር ማስቀመጥ፣
  - ✓ ኢምፕላንቱን በተበጣው ቆዳ ስር ከተቀመጠ በኋላ የተበጣውን ቆዳ በፕላስተርና በፋሻ ማሸግ፤ የታሸገው መቼ እንደሚፈታና መደረግ ስለሚጋባው ጥንቃቄ ለተገልጋዩዋ ማስረዳት፣
- ❖ **በክንድ ቆዳ ስር የተቀመጠዉን ኢምፕላንትስ ማውጣት (Implants Removal)**
  - ✓ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ማዘጋጀት፣
  - ✓ ትክክለኛ የብክለትና የኢንፌክሽን መከላከል አሰራርን መከተል፣
  - ✓ ኢምፕላንቱ ያለበትን ቦታ በትክክል ማረጋገጥና በሚወጣበት ቦታ ላዩ (በላዩኛው የውስጥ ክንድ) ማደንዘዣ መስጠት፣
  - ✓ ኢምፕላንቱ በሚወጣበት ቦታ (ኢምፕላንቱ በገባበት አጠገብ) ቆዳ ላዩ በትንሹ መብጣት፣
  - ✓ ኢምፕላንቱን ለዚህ ተግባር በተዘጋጀው መሣሪያ (forceps) ቆንጥጦ ማውጣት፣

- ✓ ኢምፕላንቱን ትውጣ ከወጣ በኋላ የተበጣውን ቆዳ በፕላስተርና በፋሻ ማሸግ፤ የታሸገው መቼ እንደሚፈታና መደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ለተገልጋዩዋ ማስረዳት፣
- ✓ ተገልጋዩዋ አዲስ ኢምፕላንት እንዲሰጣት ከፈለገች የቀድሞው ከወጣበት በላዩ ወይንም በታች ቦታ ላይ አለበለዚያም በሌላኛው ክንድ ላዩ መስጠት፣

❖ **በማህፀን ውስጥ የሚቀመጥ (ሉፕ) የማስገባት ሂደት**

- ✓ ተገልጋዩዋ ከማህጸን ጋር የተያየዘ የጤና ሁኔታ ማረጋገጥ (screening)፣
- ✓ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች /Speculum,Tenaculum,uterine sound እና ሌሎች/ማዘጋጀት እና በጥንቃቄ መጠቀም፣
- ✓ ትክክለኛ የብክለትና የኢንፌክሽን መከላከል አሰራርን መከተል፣
- ✓ ተገልጋዩዋ በደንብ እስክትረጋጋ ድረስ እንድታርፍ ማድረግና ሉፑን ማስገባት፣
- ✓ ተገልጋዩዋ ምን ማድረግ እንዳለባት በመምከርና ስለክትትል ቀጠሮ በመስጠት ማሰናበት፣

1.2.3. የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ማቀናጀት

የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ከሌሎች በጤና ኬላው ከሚሰጡ አገልግሎቶች ጋር ተቀናጅቶ ሊሰጥ ይችላል።ለምሳሌ፡- ከክትባት አገልግሎት፣ከህጻናት ጤና ክብካቤ፣ከወሊድና ድህረ ወሊድ፣ከስርዓተ ምግብና የእድገት ክትትል ወዘተ አገልግሎቶች ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰጥ ማድረግ አጋጣሚዎችን ሁሉ ለመጠቀም ያስችላል።

1.2.4. የሪፈራል አገልግሎት መስጠት

ተገልጋዮች በጤና ኬላ የማይሰጥ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ከመረጡ ወይም አገልግሎቱ ከመሰጠቱ በፊት ምርመራ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ወደ ሚቀጥለው የጤና ድርጅት ማስተላለፍ/መላክ ያስፈልጋል።

ማስታወሻ፡- ***የቤተሰብ ዕቅድ አሰጣጥን በተመለከተ ለዚህ ተግባር የተዘጋጀዉን ሀገራዊ መመሪያ በትክክል መከተል ያስፈልጋል።***

1.2.5. በቤተሰብ ዕቅድ ላይ የንቅናቄና ኮሚዩኒኬሽን ስራዎችን መስራት

❖ **የተናጠል ኮሚኒኬሽን** - ከግለሰቦችና ጥንዶች ጋር መወያየት በቤት ለቤት ጉብኝት ወይንም በጤና ኬላ ደረጃ ሲሆን ይችላል።

❖ **የቡድን ኮሚኒኬሽን/ውይይት-** የቤተሰብ ውይይት፣ የ1ለ5 አባላት ውይይት፣ የልማት ቡድን ውይይት፣ የተማሪዎች ውይይት፣

❖ **የማህበረሰብ ውይይት-** በአካባቢው የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚነት ዝቅተኛ ከሆነ ወይም እንዳይጠቀሙ የሚያደርጉ ማነቆዎችን ለመፍታት ውይይት ማድረግ

ስለቤተሰብ እቅድ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ወቅት መካተት ያለባቸው ቁልፍ ጉዳዮች

1. ስለቤተሰብ እቅድ ምንነት
2. የቤተሰብ እቅድ ጠቀሜታዎች ለምሳሌ፡- በጤና፣ በማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች
3. የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች -በሁለት እንደሚከፈል

ሀ/ **የተፈጥሮ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች** ፣ ስለ አያንዳንዳቸው የሚያስገኙት ጥቅሞችና ውስንነቶች

- ጡት ማጥባት
- በቀን አቆጣጠር
- የማህጸን ፈሳሽ በማየት
- የሰውነት ሙቀት በመለካት
- ከግብረ ስጋ ግኑኝት መታቀብ
- የወንድ የዘር ፍሬ ወደ ውጭ ማፍሰስ

ለ/ **ዘመናዊ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች**- ዘመናዊ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች የሚሰጡት ጥቅምና ሊያስከትሉ የሚችሉ መጠነኛ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ማስተማርና ተጠቃሚው በአግባቡ ከተጠቀመበት ውጤታማነቱን ማስረዳት።

ለአጭር ጊዜ የሚያገለግሉ

- በአፍ የሚዋጥ
- የሴትና የወንድ ኮንደም
- በመርፌ የሚሰጥ
- ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ

ለረዥም ጊዜ የሚያገለግሉ

- በክንድ ቆዳ ስር የሚቀመጥ ኢምፕላንት
- በማህጸን ውስጥ የሚቀመጥ (ሉፕ)

ለዘለቄታ የሚያገለግሉ

- የሴት ዕንቁላል ማስተላለፊያ ቧንቧ መቋጠር፣
- የወንድ የዘር ፍሬ ማስተላለፊያ መቋጠር፣

1.2.6. የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ግብዓቶችን ማሟላት

- ❖ ለጤና ኬላው የሚያስፈልገውን የቤተሰብ ዕቅድ ግብዓት በዓይነትና በመጠን አስቀድሞ መተንበይ፣ መጠየቅና ማሟላት፣
- ❖ በጤና ኬላው የሚገኙ የቤተሰብ ዕቅድ ግብዓትን በአግባቡ መመዝገብና መያዝ፣

ሰንጠረዥ፡ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችና የሥራ መሣሪያዎች

የተለያዩ አይነት የጽንሰት መከላከያ ዘዴዎች	**የህክምናና ሌሎች ቁሳቁሶች**
❖ ኮንደም (የወንድና የሴት) ❖ ፒልስ (ጥምርና ነጠላ) ❖ ዲፖፕሮቬራ ❖ ኢምፕላንትስ (ጃዴል፣ ኢምፕላኖን፣ ሲኖ ፕላንት ወዘተ) ❖ ሉፕ ❖ የድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ **የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች** ❖ ማደንዘዣ (ሊዶኬን) ❖ አድሬናሊን ❖ አዮዲን/ሳቭሎን ❖ የሉፕ እና ኢምፕላኖን ማስገቢያና ማውጫ ኪቶች ❖ አስፈላጊ የሆኑ ጸረ- ተዋህስያን መድሃኒቶች (Amoxacillin, Ampicillin, metronidazole, Cotrimoxazole, Procaine pencillin)	❖ ሲርንጅና መርፌ ❖ የህክምና ሳህን/ትሬይ ❖ የደም ግፊት መለኪያ ❖ የሙቀት መለኪያ ❖ የክብደት መለኪያ ሚዛን ❖ ግሎቭ ❖ አድሄሲቭ ፕላስተር ❖ ባንዴጅ/ጎዝ/፣ጥጥ ❖ መመርመሪያ አልጋ ❖ የማዋለጃ አልጋ ❖ ሴፍቲ ቦክስ ❖ ሎግ ቡክ (መከታተያ ቅጽ) ❖ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች (የቤተሰብ ጤና መመሪያ፣ ቤተሰብ ዕቅድ ማስተማሪያ ቻርት (FP decision making tool) ፣ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መመሪያዎች ወዘተ.) ❖ የጽሕፈት መሣሪያዎች

1.2.7. መልካም ተሞክሮን መቀመርና ማስፋት

- **በቀበሌ ወይም በመንደር ደረጃ፡-** መልካም ተሞክሮ ያላቸው ጎጦች/መንደሮች ወይንም የልማት ቡድኖች ዘቀተኛ አፈጻጸም ላላቸው ጎጦች/መንደሮች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ እና ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማስተባበር እና ማመቻቸት
- **በቤተሰብ ደረጃ፡-** የቤተሰብ ዕቅድ በአግባቡ የሚጠቀሙ ቤተሰቦችን እንደ አርአያ መጠቀምና ሌሎች ከእነርሱ ልምድ እንዲቀስሙ ማድረግ
- **በግለሰብ ደረጃ፡-** በአገልግሎቱ የረኩ ተጠቃሚዎችን በሞዴልነት በመጠቀም ህብረተሰቡን ማስተማር

1.3. የሚጠበቁ ውጤቶች

- ቤተሰቦች ስለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት የተሟላ መረጃ ያገኛሉ፤ ዕውቀታቸው ይዳብራል፣
- ቤተሰቦች የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚ ይሆናሉ፣
- ከቤተሰብ ገቢ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ቤተሰብ ይመሠረታል፣
- ቤተሰቦች የግል ህይወታቸውን በማሻሻል ገቢያቸው ይዳብራል፤ የቤተሰብን መተፋፈግን ይቀንሳል፣
- የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚነት ተሻሽሎ ባልተፈለገ እርግዝናና ወሊድ ጋር ተያይዞ የሚመጣ የህክምና ወጪን ይቀንሳል፣

- የሴቶች የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ያድጋል፣
- የኮንዶም ተጠቃሚዎች ቁጥር ስለሚጨምር የኤች አይ ቪ/ ኤድስና ሌሎች አባላዘር በሽታዎች ስርጭት ይቀንሳል፣
- የቅንጅታዊ አሰራር ባህል ይዳብራል፣
- የቤተሰብ ዕቅድ የማይጠቀሙ ታሳሚዎች ተጠቃሚ ከሆኑት ዕውቀትና ልምድ በመቅሰም በራሳቸው ተነሳሽነት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ፣
- ያልተፈለገ /ያልታቀዱ እርግዝናዎችን፣ ውርጃን እና የእናቶችና ህጻናት ህመምና ሞትን ይቀንሳል
- አፍላ ወጣት ሴቶች ላይ ያለ ዕድሜ የሚከሰት እርግዝናን ይቀንሳል፡፡

1.4. ክትትልና ግምገማ

በአጠቃላይና መሰረታዊ ጤና ኬላዎች የሚሰሩ ባለሙያዎች የጎጥ ጤና መሪዎችና የልማት ቡድን መሪዎች ያቀዱትን ስለመተግበራቸው እና ለሌሎች ክትትልና ድጋፍ ማድረጋቸውን የሙያ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ አፈጻጸማቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መገምገም፣ በሚስተዋሉ ክፍተቶች ላይ የጋራ የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥና ተግባራዊነታቸው መከታተል ያስፈልጋል፡፡

1.4.1. የመገምገሚያ ነጥቦች እና የፕሮግራም (የፓኬጅ) መለኪያዎች /indicators/

- በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ላይ ትምህርት ያገኙ ሰዎች ብዛት (ሴት፣ ወንድ)፣
- ነባርና አዲስ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ታሳሚዎች ብዛት፣
- በጤና ኬላ ደረጃ የሚሰጡ የእርግዝና መከላከያ አማራጮች በበቂ መጠን መኖራቸው፣
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነው ያቋረጡ ተገልጋዮች ብዛትና ያቋረጡበት ምክንያት፣
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በሚጠቀሙት የዕቅድ አገልግሎት ዓይነት ለያይቶ መመዝገብ፣
- ከጤና ኬላ ደረጃ በላይ የሆኑትን የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት እንዲያገኙ ወደ ሌሎች የጤና ድርጅቶች የተላኩና ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ብዛት መመዝገባቸው፤

1.4.2. የግምገማ ማስፈፀሚያ ስልቶች

- ቤት ለቤት በመዘዋወር
- በማህበረሰብ ደረጃ ያሉ አደረጃጀቶችንና የጤና ኬላው ሪፖርቶችን በማሰባሰብና በመተንተን
- ተገልጋዮችን በማነጋገር

ክፍል 2፡ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት

2.1. በመሰረታዊና አጠቃላይ ጤና ኬላ ባለሙያዎች የሚከናወኑ ተግባራት

ተ.ቁ	ዋና ዋናተግባራት	መሰረታዊ ጤና ኬላ	አጠቃላይ ጤና ኬላ
1	መሠረታዊ መረጃን መሰብሰብና ውጤቱን ለኅብረተሰቡ በመግለጽ በጋራ የሥራ ዕቅድ ማዘጋጀት መፈፀም	✓	✓
2	ለወጣቶችና አፍላ ወጣቶች የሚሰጡ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ፓኬጆችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅና ማነቃቃት	✓	✓
3	የአቻ ለአቻ አስተባባሪዎች፣ አስተማሪዎች ሥልጠና መስጠት	✓	✓
4	በተዋልዶ ጤና ጉዳዮች ላይ መረጃና የምክክር አገልግሎት መሥጠት	✓	✓
5	የድንገተኛ እርግዝና መከላከያን ጨምሮ ስለ ተለያዩ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች መረጃ፣ምክርና ምቹ አገልግሎት ማቅረብ	✓	✓
6	የምክርና ምርመራ አገልግሎት (የእርግዝና፣የኤች.አይ.ቪ ምክክርና ምርመራ) መስጠት	✓	✓
7	የውርጃና የድህረ-ውርጃ አገልግሎት መስጠት	X	✓
8	በወላጆች እና ታዳጊዎች መካከል ግልፅ የስነ ተዋልዶ ውይይት እንዲደረግ ምክርና ትምህርት መስጠት	✓	✓
9	መልካም ተሞክሮን መቀመርና ማስፋፋት	✓	✓
10	የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ቀን ማዘጋጀት	✓	✓
11	በህብረተሰቡ ዉስጥ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞችን ማስፋፋት	✓	✓
12	በትምህርት ቤቶች የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና መረጃና ትምህርት ማስፋፋት	✓	✓
13	ፆታዊ ጥቃት መረጃና ትምህርት መስጠት አንዳስፈላጊነቱ ሪፈር ማድረግ	✓	✓
14	የተከናወኑ ተግባራትን አፈጻጸም ሪፖርት ማድረግ	✓	✓

2.1.1. መሠረታዊ መረጃን መሰብሰብ

- ❖ መረጃ መሰብሰብና ያለውን ወቅታዊ አድርጎ መጠቀም
- ❖ ከወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መለየት
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድና ሌሎች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ እና ያልሆኑ ወጣቶች ብዛት
- ❖ የስነ-ተዋልዶ ክበብ ያላቸው ትምህርት ቤቶች ብዛት፣
- ❖ በቀበሌው በሚገኙ የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራት የታቀፉ ታዳጊዎችና ወጣቶች ብዛት፣
- ❖ በተዋልዶ ጤና ዙሪያ የሠለጠኑ ወጣቶች/ታዳጊዎች ብዛት፣ (በጾታ)
- ❖ ወላጅ የሌላቸው ታዳጊዎች ብዛት፣ (በጾታ)

❖ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች ብዛት (በጾታ፣በዕድሜ፣በጋብቻ ሁኔታ፣በሥራሁኔታ፣በትምህርት ደረጃ ወዘተ.የተከፋፈለ ሲሆን ይገባል።)

2.1.2. በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ውጤቱን ለኅብረተሰቡ መግለጽና በጋራ የሥራ ዕቅድ ማውጣት

❖ የተገኙ መረጃዎችን መተንተንና ለዕቅድ ዝግጁ ማድረግ

❖ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ የስራ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ዕቅዱን ለታዳጊዎችና ወጣቶች እንዲሁም ለኅብረተሰቡ መግለጽና መወየየት

❖ የተሰበሰበውን መረጃ መሠረት ያደረገና ታዳጊዎችን፣ ወጣቶችን፣ኅብረተሰቡን ያሳተፈ የሥራ ዕቅድ ማውጣት

❖ እንደአስፈላጊነቱ የወር፣ የሩብ ዓመት፣የግማሽ ዓመትና የዓመት የሥራ ዕቅድ ማውጣት

2.1.3. ለወጣቶችና አፍላ ወጣቶች የሚሰጡ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅና ማነቃቃት

❖ የጎጥ ጤና መሪዎች፣ የልማት ቡድንና የወጣቶች አደረጃጀቶችን በመጠቀም የማኅበረሰብ ንቅናቄ ማካሄድ፣

❖ ለመስተዳድር አካላት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት በአገልግሎቱ ዙሪያ የግንዛቤ ማዳበር ሥራ መሥራት፣

❖ ከህብረተሰቡ እና ከወጣቶች ጋር ውይይት በማድረግ መግባባት ላይ መድረስ፣

❖ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሥልጠና መስጠት (ሴቶች፣ህዓናትና ወጣቶች ፤ መምህራን.....)

2.1.4. የአቻ ለአቻ አስተባባሪዎች/ አስተማሪዎች ሥልጠና ማካሄድ

❖ ለሥልጠናው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችንና አጋዥ መሣሪያዎችን መለየትና ማዘጋጀት

❖ በመሥፈርቱ መሠረት ሰልጣኞችን መመልመል

❖ ከሰልጣኞች ጋር በሥልጠናው ዙሪያ ውይይት ማድረግ

❖ የሥልጠና ሥፍራና ጊዜ በጋራ መወሰን

❖ ሥልጠናውን ማካሄድ

❖ የመመረቂያ መሥፈርቱን ያሟሉትን ሠልጣኞች ማስመረቅ

❖ የአቻ ለአቻ አስተባበሪነት ስልጠና በመሥጠት ወደ ተግባር ማሰማራት፣

❖ ድህረ ስልጠና ክትትልና ግምገማ ማድረግ

2.1.5. ስራውን ሊያግዙ ከሚችሉ ድጋፍ ሰጪ አካላት ጋር ቅንጅት መፍጠር

❖ በቀበሌው የሚገኙትን አጋዦችን (ደጋፊዎችን) መለየት

- ✓ መስተዳድር:- አስተዳደራዊ ድጋፍ እንዲሰጥ
- ✓ ግብርና:- የልማት ጣቢያ ሰራተኞች ወጣቶችን በመለየት ድጋፍ እንዲሰጡ

- ✓ ትምህርት፡- ለመምህራንና ተማሪዎች ትምህርት በመስጠት የወጣቶች ተወልዶ ጤና ክብባት እንዲያቋቁሙ ወዘተ...
- ✓ ማህበራት (የሴቶች፣ የወጣቶች ወዘተ...) ፡- አባላቶቻቸውን በማንቀሳቀስና በማሰተፍ በታዳጊዎችና ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ላይ ድጋፍ እንዲያደር፣
- ✓ የኀጥ ጤና መሪዎችና የልማት ቡድኖች ስለ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስነ ተዋልዶ ጤና ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ማድረግና የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስነ ተዋልዶ ጤና ላይ ድጋፍ እንደሰጡ ማበረታታት
- ✓ የኃይማኖት ተቋማት - ተከታዮቻቸውን በማንቀሳቀስና በማሰተፍ በታዳጊዎችና ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ላይ ድጋፍ እንዲያደርጉ፣
- ✓ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች - ሙያዊና ቁሳዊ ወዘተ. ድጋፍ እንዲያደርጉ

- ❖ ውይይት ማካሄድና የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ
- ❖ ዕቅድና ፍላጎትን ማጣጣም እና በትብብር መሥራት

2.1.6. ፆታዊ ጥቃትን የመከላከልና ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ

- ❖ ፆታዊ ጥቃት ላይ ለህብረተሰብ መረጃ መስጠት
- ❖ ፆታዊ ጥቃትን ለመከላከል የወንዶች ተሣትፎን ማሣደግ
- ❖ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ወጣትና አፍላ ወጣቶችን የስነ-ልቦና ድጋፍ እንዲያገኙ ሪፈር ማድረግ
- ❖ በፆታዊ ጥቃት ዙርያ ሴሎች ደጋፊ አካላትን ማስተባበር

ለወጣቶች የሚሰጡ ዋና ዋና የጤና አገልግሎቶች የሚከተሉት ናቸው

- ❖ በተዋልዶ ጤና ጉዳዮች ላይ መረጃና የምክክር አገልግሎት መሥጠት
- ❖ የአቻ ለአቻ ትምህርትን ጨምሮ በተለያዩ ዘዴዎች ጤናማ የወሲብ ባሕርያትን ማበልጸግ
- ❖ የድንገተኛ እርግዝና መከላከያን ጨምሮ ስለ ተለያዩ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች መረጃ፣ምክርና ምቹ አገልግሎት ማቅረብ
- ❖ ስለኮንዶም አጠቃቀም ማስተማርና ማቅረብ
- ❖ የምክርና ምርመራ አገልግሎት (የእርግዝና፣የኤች.አይ.ቪ ምክክርና ምርመራ) መስጠት
- ❖ የአባላዘር በሽታዎችን ምርመራ፣ ህክምና፣መከላከያና መቆጣጠሪያ ላይ ምክርና አገልግሎት መስጠት
- ❖ የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድ፣ የድኅረ ወሊድ እና የኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍን መከላከል አገልግሎቶች መስጠት
- ❖ የውርጃና የድህረ-ውርጃ አገልግሎት መስጠት
- ❖ ለታዳጊዎች የመንጋጋ ቆልፍ መከላከያ ክትባት እና የደም ማነስ መከላከያ መድኃኒት መስጠት
- ❖ በወላጆች እና ታዳጊዎች መካከል ግልፅ የስነ ተዋልዶ ውይይት እንዲደረግ ምክርና ትምህርት መስጠት
- ❖ በየደረጃው ባሉ የጤና ተቋማት ተገቢውን የቅብብሎሽ ሰንሰለት መመሥረት

2.1.7. መልካም ተሞክሮን ማስፋፋት

❖ በቀበሌ ውስጥ ወጣቶች ያላቸውን ግላዊ ተሞክሮ እርስ በእርስ እንዲለዋወጡ የሚያስችል መድረክ በማዘጋጀት ተሞክሮን እንዲጋሩ ማመቻቸት፣

❖ መልካም ተሞክሮ ያላቸው ጎጦች/መንደሮች ወይንም የልማት በቡድኖች ዝቅተኛ አፈጻጸም ላላቸው ጎጦች/መንደሮች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ማስተባበር እና ማመቻቸት

❖ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች በተዋልዶ ጤና አገልግሎት ላይ የተሻለ ልምድ/ተሞክሮ ያላቸው ቤተሰቦችን እንደ አርአያ መጠቀምና ለሌሎች ከእነርሱ ልምድ እንዲቀስሙ ማመቻቸት

2.1.8. ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ቀን ማዘጋጀት

❖ አገልግሎቱን በስፋት ለማስተዋወቅ እንደአስፈላጊነቱ የወጣቶችን ቀን በቀበሌ ደረጃ በማዘጋጀት ህብረተሰቡን፣ አገር ሽማግሌዎች፣ ተማሪዎች፣ ታዳጊዎችና ወጣቶች፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች በመጋበዝ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ተዋልዶ ጤና አግልግሎቶች ላይ ውይይት ማድረግ

❖ ወጣቶች የተለያዩ ሥራዎችንና የግል ተሞክሮአቸውን በበዓሉ ላይ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሌሎች ከእነርሱ እንዲማሩ ማድረግ

❖ በወጣቶችና አፍላ ወጣቶች የተዘጋጁ የተለያዩ ከተዋልዶ ጤና ጋር ቁርኝት ያላቸውን ተግባራት/ውጤቶች ለኅብረተሰቡ ማቅረብ፣

❖ ተዋልዶ ጤናን በተመለከተ የተለያዩ ድራማ፣ ጭውውት፣ፖስተርና ስዕላዊ መግለጫዎችን በማቅረብ

❖ በአገልግሎቱ ዙሪያ ጥሩ ተሳትፎና እንቅስቃሴ ላደረጉት ታደጊዎች፣ ወጣቶችና ቤተሰቦች እውቅና መስጠት፣ የማበረታቻ ሰጦታዎች እንዲሁም የምስክር ወረቀት መስጠት

2.1.9. በትምህርት ቤቶች ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞችን ማስፋፋት

❖ የወጣቶች ተዋልዶ ክበባትን ማቋቋም

❖ የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አራማጆች መመልመል እና ማብቃት

❖ የሚኒ-ሚዲያ መስፋፋትን መደገፍና በተዋልዶ ጤና ዙሪያ እንዲሠሩ ማበረታታት

❖ የተለያዩ መልዕክት ያላቸው ጽሑፎችን መበተን (በራሪ ጽሑፎች፣ ቡክሌቶች፣ ፖስተር፣ የተግባር ካርዶች ወዘተ.)

2.2. የሚጠበቁ ውጤቶች

❖ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስለ ተዋልዶ፣ ጤና በእድገት ምክንያት የሚከሰቱ ለውጦችና የመራቢያ አካላትን ተግባራት ያወቃሉ፣

❖ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች የጤናና የማህበራዊ ችግሮች (ጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈር፣ አደንዛዥ ዕጾች፣ አልኮል፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ የሴት ልጆች ግርዛት በመሳሰሉት) ችግሮች ላይ የተሟላ መረጃና ትምህርት በማግኘታቸው ችግሮቹ ይቀንሳሉ

❖ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ስለ ኤች ኤ ቪ ኤድስና ሌሎች በሽታዎች መረጃና ትምህርት በማግኘታቸው አንድ ለአንድ ጸንቶ መቆየትን ይመርጣሉ፣ ከጋብቻ በፊት ከወሲብ ይታቀባሉ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ያስቀራሉ፣ ኮንዶም ይጠቀማሉ።

❖ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች የተዋልዶ ጤና ችግሮች የሆኑት ያልተፈለገ እርግዝናና ውርጃ እንዳይከሰቱ ወጣቶች የተለያዩ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፣

- ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ተስማሚና ምቹ የሆነ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ይስፋፋል፤ የቅብብሎሽ ሥርዓቱም ይጠናከራል ፣
- ከወሲብ መታቀብን ጨምሮ የኃላፊነት ስሜት ያለውና ጤናማ የተዋልዶ ጤና ባህሪ በወጣቶች ዘንድ ይሰርጻል፣
- ወጣቶች በተዋልዶ ጤና ዙሪያ ያሉባቸውን የጤና ችግሮች ለማስወገድ ወጣቶችን ሳቢ የሆኑ መድረኮች ይፈጠራሉ፣
- በቀበሌው በሚገኝ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሴት ተማሪዎች የወጣቶች ተዋልዶ ጤና ፕሮግራም ተጠቃሚ ይሆናሉ፣
- በትምህርት ቤቶች የወጣቶች ተዋልዶ ጤና ክበባት እና ሚኒ ሚዲያዎች ይቋቋማሉ፣
- የሕይወት ክህሎታችን ያዳበሩ ወጣቶች ቁጥር ይጨምራል፣
- ያለእድሜ ጋብቻና ወሲድ ይቀንሳል፣
- ያልተፈለገና ያልታቀደ እርግዝና ይቀንሳል፣
- በእርግዝና ምክንያት ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ወጣቶች ቁጥር ይቀንሳል፣
- የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አራማጆች ቁጥር ይጨምራል።
- የቤተሰብ ዕቅድ የማይጠቀሙ ነገር ግን ለመጠቀም የሚፈልጉ (unmet need for Family Planning) ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ቁጥር ይቀንሳል

2.3. ክትትልና ግምገማ

ሀ. የክትትልና ግምገማ ነጥቦች

- የፕሮግራሙ አጠቃላዩ ዓላማዎች እና የታቀዱት ዝርዝር ተግባራት መፈጸማቸውን
- ኅብረተሰቡና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ስለ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ተዋልዶ ጤና አስፈላጊነት ያላቸው ግንዛቤ መጨመሩን፣
- ትምህርት ቤቶች የተዋልዶ ጤና ክበባትን ማቋቋማቸውንና በአግባቡ እየሠሩ መሆኑን፣
- ለጤና ጎጂ ድርጊቶችን የሚተገብሩ ወጣቶች ከድርጊታቸው ለመላቀቅ የሚያስችላቸውን ተግባር እየከናወኑ መሆኑን፣
- ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች በቀበሌው በሚገኙ የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራት ታቅፈው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን፣
- በተዋልዶ ጤና ዙሪያ የሠለጠኑ ወጣቶች/ታዳጊዎች የሚጠበቅባቸውን ተግባር እያስፋፉ መሆኑን፣
- ለወጣቶች የመወያያና የመማማሪያ መድረክ መፈጠሩንና ቀጣይነቱ መረጋገጡ፣
- ወላጆቻቸውን ያጡ ታዳጊዎች በኅብረተሰቡ የሚጠበቀውን እንክብካቤ እያገኙ መሆናቸውን፣
- ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ያላቸው የሕይወትና የተለያየ ክህሎት/ችሎታ እያዳበሩ መሆኑን፣
- ለተጨማሪ ሕክምና ወይም ለአገልግሎት ወደ ቀጣዩ የጤና እርከን የተላኩ ታዳጊዎችና ወጣቶች የሚጠበቀውን አገልግሎት ማግኘታቸውን፣

ለ. የግምገማ ማስፈጸሚያ ስልቶች

- ❖ በመስክ ቤት ለቤት ጉብኝት በማድረግ እና ተገልጋዮች ማነጋገር፤
- ❖ የማህበረሰብ ተሳትፎ አደረጃጀቶች የጤና ኬላ ሪፖርቶችን በማሰባሰብና በመተንተን የአቀዱን ስኬት ማረጋገጥ
- ❖ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመሆን የግምገማ መድረኮችን በመፍጠር የተከናወኑ ተግባራት አፈጻጸምን መፈተሽ
- ❖ የክትትልና ግምገማ መለኪያዎችን በመጠቀም የአፈጻጸም ሁኔታዎችን መገምገም

ሐ. የፕሮግራም (የፓኬጅ) መለኪያዎች /indicators/

- ❖ የተለያዩ የስነ ተዋልዶ ጤና መረጃዎችን ያገኙ ወጣቶች ብዛት/ ወንድ፡ሴት/
- ❖ የእርግዝና መከላከያ የሚጠቀሙ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ብዛት፣ /ወንድ፣ሴት/
- ❖ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች/አፍላ ወጣቶች ብዛት፣ (ወንድ፣ሴት)
- ❖ የአቻ ለአቻ አስተባባሪነት ሥልጠና የወሰዱ ወጣቶች/አፍላ ወጣቶች ብዛት (ወንድ፣ሴት)
- ❖ የተደረጉ የአቻ ለአቻ ውይይቶች ብዛት፣
- ❖ የተቋቋሙ የተዋልዶ ጤና ክበባት ብዛት፣
- ❖ ኤች.አይ.ቪ ምክክርና ምርመራ ያገኙ ታዳጊዎችና ወጣቶች ብዛት (ወንድ፣ሴት)
- ❖ ያለእድሜ የተከሰተ እርግዝና ቁጥር
- ❖ ያለእድሜ የተከሰተ ወሊድ ቁጥር

2.4. ለፓኬጁ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ መድኃኒትና ቁሳቁሶች

- ❖ የተለያዩ ተዋልዶ ጤና መረጃ የያዙ በራሪ ፅሁፎች፣ ፖስተሮችና መፅሔቶች
- ❖ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎችና የአገልግሎት መስጫ ቁሳቁሶች፣ ***(ለግብዓቶቹ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ክፍልን ይመልከቱ)***
- ❖ ለኤች ኤይ ቪ ኤድስ እና አባላዘር በሽታዎች ምርመራና ህክምና የሚያገለግሉ መድሃኒቶችና ግብዓቶች
- ❖ መዝገቦች እና መመሪያዎች
- ❖ ቅጾች እና የጽሕፈት መሳሪያዎች

ምዕራፍ 2
የጨቅላ ህጻናት እና ህጻናት ጤና አገልግሎት



2

2.1. በአጠቃላይና መሰረታዊ ጤና ኬላዎች የሚሰሩ ባለሙያዎች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

ተ ቁ	የተግባራት ዝርዝር	የሚከናወንበት	
		በአጠቃላይ ጤና ኬላ	መሰረታዊ ጤና ኬላ
1	የቀበሌውን የጨቅላ ህጻናት እና ህጻናት ጤና ክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀት	√	√
2	ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ የማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን	√	√
3	ማህበረሰብ ተኮሬ የተቀናጀ የጨቅላና የሕፃናት በሽታዎች ህክምናና ክብካቤ መተግበር		
3.1	አዲስ ለተወለዱ ህፃናት የሚሰጥ አስፈላጊ ክብካቤ (Essential newborn care)	√	√
3.2	በድህረ-ወሊድ ለህፃኑና ለእናተቱ የሚሰጡ አስፈላጊ ክብካቤዎችን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መስጠት፤	√	√
3.3	የጨቅላ ህፃናት አደገኛ ምልክቶች በቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ ክብካቤና ክትትል እንዳየገኙ ማድረግ ወይም ወደ ጤና ጣቢያ/ሆስፒታል መላክ	√	√
3.4	የታመሙ ጨቅላዎችን (ከዉልደት እስከ 2 ወር እድሜ ያሉ) በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ እንክብካቤና ክትትል እንዳየገኙ ማድረግ እንዲሁም በሪፍራል ወደ ሚቀጥለው የጤና አገልግሎት ዕርከን መሄድ የማይችሉ ህጻናት ህክምናን ጨምሮ	√	√
3.5	የህፃናት አደገኛ ምልክቶች በቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ ክብካቤና ክትትል እንዳየገኙ ማድረግ ወይም ወደ ጤና ጣቢያ/ሆስፒታል መላክ	√	√
3.6	የታመሙ ህጻናት (ከ2 ወር እስከ 59 ወር እድሜ ያሉ) በህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ እንክብካቤና ክትትል እንዳየገኙ ማድረግ	√	√
4	የተቀናጀ የጨቅላና የሕፃናት በሽታዎች ህክምናና ክብካቤ (Integrated Management of Newborn and Childhood Illness (IMNCI)) መተግበር		
4.1	በድህረ-ወሊድ ለህፃኑና ለእናተቱ የሚሰጡ አስፈላጊ ክብካቤዎችን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መስጠት፤የካንጋሮ እናት አያነት እንክብካቤን ጨምሮ	√	×
4.2	የጨቅላ ህፃናት አደገኛ ምልክቶች በቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ ክብካቤና ክትትል እንዳየገኙ ማድረግ ወይም ወደ ጤና ጣቢያ/ሆስፒታል መላክ ኮንቨልስ ለሚያደርግ ጨቅላ ህፃናት ዳያዜፓምን መስጠትን ጨምሮ	√	√
4.3	የታመሙ ጨቅላዎችን (ከዉልደት እስከ 2 ወር እድሜ ያሉ) በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ እንክብካቤና ክትትል እንዳየገኙ ማድረግ ሴላ አደገኝ ስየሚ ያሌለው ከፍተኛ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ ያለው ተቅማጥን ማከም እንዲሁም በሪፍራል ወደ ሚቀጥለው የጤና አገልግሎት ዕርከን መሄድ የማይችሉ ህጻናት ህክምናን ጨምሮ	√	√
4.4	የታመሙ ህጻናት (ከ2 ወር እስከ 59 ወር እድሜ ያሉ) በህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ እንክብካቤና ክትትል እንዳየገኙ ማድረግ	√	√
5	ቀዳማዩ ልጅነት እድገት (Early Childhood Development)ና መዳበር እድገት እንክብካቤ አገልግሎት መስጠት	√	√
6	የአፈጣጠር ችግር ያላቸውን ህጻናት መለየት እና ሪፈራል	√	√
7	የሕፃናት ጥቃትን መከላከል እና መለየት	√	√

2.1.1. የቀበሌውን የህጻናትና ጨቅላ ህጻናት ክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈፀም

2.1.1.1. ለፓኬጁ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ቤት ለቤት ሄዶ መሰብሰብ፤

በጤና ኬላ የሚሰሩ ባለሙያዎቹ በቀበሌ ውስጥ ከ5 ዓመት በታች ያሉ ህፃናት ጤና ክብካቤ አገልግሎት ለማስፈጸም የሚያግዙ መሠረታዊ መረጃዎችን መያዝ በቀጣዩ ለሚያከናውኑት ተግባራት አሰታፊ የሆነ ዕቅድ ለማዘጋጀትና በሂደትም ለመከታተል ያስችላቸዋል። ስለዚህም የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት በማከናወን መረጃዎችን ከጎጥ ጤና መሪዎች፣ ከሴቶች ልማት ቡድን አባላትና ሌሎች ባለድርሻዎች ጋር በመተባበር ማግኘትና መጠቀም ይኖርባቸዋል።

- ❖ ለመረጃ መሰብሰቢያ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን (ጤናና ጤና ነክ መረጃ መሰብሰቢያ ቅጾችን፤ መዝገቦችን፣ ወዘተ) ማግኘት/ማዘጋጀት
- ❖ የሚፈለጉ እንደ ከአንድ እና ከ5 ዓመት በታች ያሉ ህጻናት ብዛት፣ የተለያየ የጤና ችግር ያለባቸው ህጻናት እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን መሰብሰብና በአግባቡ በማጠናቀር በቤተሰብ ጤና ማህደር ማደራጀት፤
- ❖ መረጃዎች እንደገና በየተወሰነ ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ (በየወሩ፤ በየ3 ወሩ፤ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ) መከለስና ወቅታዊነቱን መጠበቅ፣

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ቀጣዩና ተከታታዩ የሆነ መረጃ መሰብሰብና ማጠናቀር የሚያስፈልጋቸው እንደ የልደትና የሞት ምዝገባ በየጊዜው በመሰብሰብ በቤተሰብ ማህደር ማካተት ያስፈልጋል ።እንዲሁም የተወለዱ ህጻናት ህጋዊ የልደት ምዝገባና ምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መስራት ያስፈልጋል።

2.1.1.2. የተሰበሰበውን መረጃ መተንተንና ማቀናበር

ቤት ለቤት በመሄድ የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተንና በመተርጎም የቀበሌው የህፃናት ጤና ችግር ምን እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡ ፡ ችግሮቹ ብዛት ያላቸው ከሆኑ ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ለይቶ በማውጣት በቅደም ተከተል የተለያዩ ሥልቶችን በመጠቀም ችግሮቹን ለማስወገድ በመረጃ የተደገፈና ሁሉን አሳታፊ የሆነ ዕቅድ ማዘጋጀትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

2.1.1.3. የመረጃ ትንተና ውጤትን መሠረት በማድረግ የህጻናት በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ስራዎችን እንዲሁም የህክምናና ክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀት፤

- ❖ በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በቀበሌው ያሉ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ ያስፈልጋል።
- ❖ የህጻናት በሽታዎችን መከላከልና ቁጥጥር ስራዎችን ለሚሠሩ አካላት እንደ ትምህርት ቤት፣ ወዘተ፡ በዕቅድ ዝግጅትና አተገባበር ላዩ ሙያዊ ድጋፍ መስጠትና ክትትል ማድረግ፤

2.1.1.4. ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ የማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን

2.1.1.4.1. የህጻናት ጤና አገልግሎቱን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ

ይህንን አገልግሎት ውጤታማ ለማድረግ ህብረተሰቡን ከዕቅድ ጀምሮ፣ በትግበራ፣ በክትትልና በግምገማ ወቅት ማሣተፍ ቁልፍ ተግባር ነው። በመሆኑም ወደሥራው ከመገባቱ በፊት ስለፕሮግራሙ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበር በቅድሚያ የጎጥ ጤና መሪዎችና ጤና ልማት ቡድን ማሰልጠን መጠቀም እንዲሁም ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ስፍራዎች፣ የማስተዋወቅና የማነቃነቅ ሥራ መሠራት ይኖርበታል፡፡

2.1.1.4.2. ህብረተሰቡን ማስተማርና የቤተሰብ/የሕብረተሰብን ጤና ነክ ባህሪያት ማሻሻል

- ❖ የተለያዩ ሥልቶችን በመጠቀም ለህጻናት ቤተሰቦችና ለሕብረተሰቡ በህጻናት በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ላይ ተከታታይነት ያለው ትምህርት መስጠት፣

- በመድኃኒት አወሳሰድና በበሽታ መከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ ለሕሙማን ቤተሰብ አባላት፣ ለሕሙማን ደጋፊዎች፣ ለልማት ቡድን አባላት ሥልጠና መስጠትና አፈጻጸሙን መከታተል፤
- በነፍሰ ጡር እናቶች ኮንፈረንስ ፣በቤት ለቤት ጉብኝት፤በጤና ኬላ ስለህጻናት ጤናማ አስተዳደግ፣ ስለ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች፤ የበሽታ ምልክቶች፤ ህክምናና መከላከያ መንገዶች ላይ ያተኮረ የጤና ትምህርት መስጠት፤
- በትምህርት ቤቶች ከሚገኙ መምህራን ጋር በመተባበር ተማሪዎች ለቤተሰቦቻቸውና በዙሪያቸው ለሚገኙ ማህበረሰብ ስለ ህጻናት ዋና ዋና በሽታዎች መተላለፊያ መንገዶች፤ መከላከያና ቁጥጥር ዘዴዎች አውቀው እንዲያስተምሩ ማስቻል፤
- ከቀበሌ አመራርና ከሴሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በተከታታይ በህጻናት ጤና ቀኖች የሚያስፈልጉ የጤና አገልግሎቶችን (ክትባት፣ቫይታሚን ኤ፣ ጥገኛ የአንጀት ትላትሎች መድኃኒት፣ የጤና አጠባበቅ ትምህርት፣ ወዘተ) ለመስጠት ማስተባበርና መምራት፤
- እናቶችና ህጻናት በተቻለ መጠን የተመጣጠነ ምግብ እንዲመገቡ የጤና ትምህርት ማስተላለፍ፤
- ቤተሰቦች በተለይም እናቶችና አዲስ የሚወለዱ ህፃናት ክትባቶችን በወቀቱ እንዲያገኙ ስለክትባት ጥቅም በቂ መረጃ መስጠት፤
- በአጠቃላይ ከታች በተጠቀሱት ዋና ዋና ቁልፍ መልክቶች ላይ በተከታታይ፣በተገነው አጋጣሚ ሁሉ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡

የህጻናት ጤና ቁልፍ መልክቶች

ሀ) የአካልና የአእምሮ ዕድገት ለማምጣት

- ህጻን ልጅ ከተወለደ በኋላ ገላውን በንፁህ ጨርቅ/ፎጣ ማድረቅ፤ ሌላ ንፁህ ጨርቅ/ፎጣ ማልበስና ገላውንም እስከ 24 ሰዓት ባለው ጊዜ አለማጠብ፣
- የእናት ጡት ወተት ምትክ የማይገኝለት ወይም ተወዳዳሪ የሌለው የሕፃን ምግብ ነው፡፡ የእናት ጡት ወተት ህፃኑ ጠንካራና ጤናማ ሆኖ እንዲያድግና ከዋና ዋና የሕፃናት በሽታዎች የሚከላከል ነው፡፡እንገር በጣም ጠቃሚ ምግቦችንና ከበሽታ ለመከላከል የሚረዱ ንጥረ ነገሮችን የያዘ ስለሆነ እንደ የመጀመሪያ ክትባት ይቆጠራል፡፡ ህፃናት በተወለዱ በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ እንገርን መጥባት እንዲጀምሩ ማድረግ፣
- አንድ ህፃን በተወለደ በአንድ ሰዓት ውስጥ ከእናቱ ደረት ላይ ሆኖ አካላቸው እንዲነካካ ማድረግ የጡት ወተት ቶሎ እንዲመጣ ከማድረጉም በላይ የእናትን ፍቅር በእጅጉ ይጨምራል፡፡ የህፃኑም የወደፊት ዕድገት ጥሩ እንዲሆንና ጡትንም በተሳካ ሁኔታ ለማጥባት ይረዳል፣
- ህጻን ልጅ ከተወለደ ጀምሮ የእናት ጡት ወተት ብቻ፣ውሀም በሆነ ሳይሰጥ እስከ 6 ወራት ድረስ እንዲጠባ ማድረግ፣
- ሕፃኑ በየንስ በቀን አስር ጊዜ (ሌሊትን ጨምሮ) ጡት እንዲጠባ ያስፈልጋል፤ ይህም የተስተካከለ እድገት እንዲኖረውና የእናት ጡትም የበለጠ ወተት እንዲኖረው ይረዳል፡፡ ሕፃኑ ጡቱን በደንብ እንዲጠባ በትክክል መታቀፍና ጡቱን መጉረስ አለበት ፡፡ ሕፃኑ ጡቱን በደንብ እንዲጠባ በቂ ጊዜ መስጠት እና በፈለገ ጊዜ ሁሉ ማጥባት ያስፈልጋል፡፡
- ተጨማሪ ምግብን ከ6 ወር ዕድሜ ጀምሮ መስጠትና የጡት ወተት ማጥባትን እስከ ሁለት ዓመት ዕድሜና ከዚያም በላይ መቀጠል ያስፈልጋል ፡፡ አሰጣጡን IMNCI/ICCM ቻርት ቡክሌት እና የቤተሰብ ጤና መመሪያን ይመልከቱ፡፡
- ሕፃናት በቂ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ከምግባቸው ጋር ወይም በተጨማሪነት እንዲያገኙና በቂ የሆነ የፀሐይ ብርሃንም ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣

- ❖ ለልጆች ፍላጎት በቂ ትኩረት በመስጠትና አካባቢውን ምቹ በማድረግ አእምሯዊና ማህበራዊ እድገታቸውን ማጎልበት፣
  - ✓ ህፃኑን የመውደድና የማፍቀር ምልክት ማሳየት፤ እንደሚወደድ በቃላትና በፈገግታ መግለጽ
  - ✓ ህፃኑን በቃላትና በተለያዩ መገለጫዎች ማነጋገር
  - ✓ ህፃኑ የሚያደርገቻውን ማድነቅ፤ ማስተዋል እንዲኖረው ማለማመድና ማገዝ፤
  - ✓ ህጻኑ ቀስ በቀስ አካባቢውን እንዲያውቅና እንዲረዳ ማድረግ፤
  - ✓ የህጻኑን ፍላጎት በመረዳትተገቢዉን ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ መስጠት
- ❖ ህፃኑ የቤተሰብ ደንቦችን፤ ገደቦችን እንዲያውቅ እንዲሁም ለነገሮች ዋጋ መስጠትን ማስተማር

ለ) በሽታን መከላከል ለማስቻል

- ❖ አይነ ምድር /የሕፃናትን ጨምሮ/ በአግባቡ ማስወገድ ከተጸዳዱ በኃላ፣ ምግብ ከማዘጋጀትና ልጆችን ከመመገብ በፊት እጅን በሳሙና መታጠብ፣
- ❖ ልጆች በየቀኑ ፊታቸውን እንዲታጠቡ ማድረግ፣ ከተፀዳዱ በኋላ እና ከመመገብ በፊት በሳሙናና በውሃ እጅን በመታጠብ
- ❖ ወባማ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ልጆች በአጎበር ውስጥ ሁልጊዜ እንዲተኙ ማድረግና የወባ ትንኝ መራቢያ መንገዶችን ማስወገድ፣
- ❖ በልጆች ላይ የሚደረግን እንግልትና ኢሰብአዊ ድርጊት በጊዜ ማወቅ፣ መከላከልና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፣
- ❖ ህብረተሰቡ ኤች አይቪ/ኤድስን እንዲከላከል በተለይም ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ተገንዝቦ ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግና ለታመሙና ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች ክብካቤና ድጋፍ መስጠት፣
- ❖ የመጠጥ ውሃን በንፅህና መጠበቅና መጠቀም
- ❖ ሁሉም ሕፃናት ክትባት እንዲወስዱና እንዲጨርሱ ማድረግ፡

ማሳሰቢያ፡- የታመሙና ዘጠኝ ወር ሰዩሞላቸዉ የተወለዱ ሕጻናት በክትባት ፕሮግራም መሰረት ማስከተብ ይቻላል፡፡

ሐ/ በቤት ውስጥ የሚሰጥ እንክብካቤን ለማሳወቅ

- ❖ ልጆች በሚታመሙበት ወቅት ከስድስት ወር በታች ለሆኑት የእናት ጡት ወተት ቶሎ ቶሎ እንዲጠቡ ማድረግና ከስድስት ወር በላይ ለሆኑ ደግሞ ከእናት ጡት በተጨማሪ ተመጣጣኝ ምግብ በትንሹና ቶሎ ቶሎ ከወትሮው በተሻለ መስጠትና በርከት ያለ ፈሳሽ መስጠት፣
- ❖ ሕፃኑ ተቅማጥ በሚይዘው ጊዜ ተጨማሪ በቤት ውስጥ የሚዘጋጅ ፈሳሽ ወይም ሕይወት አድን ንጥረ ነገር /ኦ.አር.ኤስ/ መስጠት፣
- ❖ ልጆች በታመሙ ጊዜ በቤት ውስጥ አስፈላጊውን ክትትል መስጠት፤ለምሳሌ የታዘዘላቸውን መድኃኒት በሰዓቱ መስጠት፣
- ❖ ከበሽታቸው እንዳያገግሙ ከተሻላቸውም በኋላ ለተከታዩቹ ሁለት ሳምንታት ከቤላው ጊዜ በበለጠ እንዲመገቡ ማድረግ ፣
- ❖ ልጆችን ከማንኛውም አደጋ መጠበቅና ጉዳት ሲደርስባቸው በወቅቱ ተገቢውን ህክምና እንዲገኙ ማድረግ፣
- ❖ ጎጂ ባህላዊ ህክምናዎችንና ልምዶችን ማስወገድ /እንጥል ማስቀረጥ፣ ግግ ማስባጠጥ፣ የሴት ልጅ ግርዛት፤ በጤና ባለሙያ ያልታዘዙ መድኃኒቶች፤ የፀሐይ ብርሃን እንዳያገኙ ማድረግ፤ ቅቤና የመሳሰሉትን ለጨቅላ ህፃን ማቅመስ፤ጣጣቴ ማስተኮስ፤ቅንድብ ማሰንጠቅ፤/

መ/ ከሰለጠነ ባለሙያ የጤና ክብካቤ ፍለጋና የሚሰጠውን ምክርና ህክምና ተግባራዊ ለማድረግ

- ❖ የታመሙ ልጆች ተጨማሪ ሕክምና በሚያስፈልጋቸው ወቅት ፈጥኖ መረዳትና ተገቢውን ህክምና ከሰለጠነ ባለሙያ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ❖ የጤና ባለሙያ ምክር፣ ህክምናና፣ የክትትል ቀጠሮን ማክበር፣
- ❖ ነፍሰ ጡር ሴቶች ከሶስት ወር በፊት እርግዝናቸውን እንዲያሳውቁና በየንስ ስምንት ጊዜ የቅድመ ወሊድ ምርመራ፣በሰለጠነ ባለሙያ የማዋለድ አገልግሎት እንዲሁም ከወለዱ በኋላ ጨቀላውና እናት በመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ ሶስት ጊዜ የድህረ ወሊድ ክትትል ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣

ማሳሰቢያ፡ - ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ቁልፍ መልዕክቶች የቤተሰብ ጤና መመሪያን በመጠቀም እናትን/ተንከባካቢዎችን ማማከር ያስፈልጋል፡፡

በህጻናት ጤና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶች የሚከናወኑባቸው ቦታዎችና ሁኔታዎች

- በቤት ለቤት ጉብኝት ወቅት
- ህብረተሰቡ የጤና አገልግሎት ለማግኘት ወደ ጤና ኬላ በሚመጣበት ወቅት
- በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ፣ ለምሳሌ፡- ቀበሌ ምክር ቤት፣ሴቶች ማህበር፣ወጣቶች ማህበር ወዘተ
- በአምልኮ ሥፍራዎች
- በትምህርት ቤቶች፤
- በገበያ ቦታዎች
- በጎጥ ጤና መሪዎችና ልማት ቡድን ስብሰባዎች
- በዕድሮች፣ወዘተ

2.2. የተቀናጀ የጨቅላና የሕፃናት በሽታዎች ህክምናና ክብካቤ (Integrated Management of Newborn and Childhood Illness)

የተቀናጀ የጨቅላና የሕዓናት በሽታዎች ህክምናና ክብካቤ ዋና ትኩረት አጠቃላዩ የህጻናትን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ ሲሆን ዋና ዋና ዩዘቶቹም፡-

- የጤና ባለሙያዎችን በጨቅላና ህጻናት መሰረታዊ ክብካቤና ህክምና ላዩ ያላቸውን ክህሎት ማሻሻል፤
- የጨቅላና ህዓናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን ማሻሻል፤
- የቤተሰብንና የህብረተሰቡን የጨቅላና ህዓናት ጤና አጠባበቅ ልምድ ማሻሻል ናቸው፡፡

የተቀናጀ የጨቅላዎችና የሕዓናት በሽታዎች ህክምና እና ክብካቤ ስልት ህዓናትን በመኖሪያ ቤታቸውም ሆነ በጤና ኬላ በሚታዩበት ጊዜ ከባድና ቀላል በሽታን በትክክል ለመለየትና ከባድ በሽታ ያላቸውን በአስቸኳይ ወደ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል ለመላክ፤ በጤና ኬላና በቤተሰብ ደረጃ የሚረዱትን ደግሞ ተገቢውን የህክምናና የምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዋና ዋና በሆኑት የሕዓናት ጤና ችግሮችና ጉዳዮች ላይ አንድናተኩር ከመርዳቱም በላይ እንዴት መከላከልና መቆጣጠር እንዳለብን ቤተሰብንና ህብረተሰብን በማሳተፍ ህብረተሰቡ የራሱን ጤና ለመጠበቅ ዋነኛ ተዋናዩ ሆኖ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ለማስተማር ነው፡፡

2.2.1. የተቀናጀ የጨቅላዎችና የሕፃናት በሽታዎች ሕክምናና ክብካቤ ስልት ዋና ዋና ተግባራት

ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራት በስፋት ለመረዳትና ለመተግበር የጨቅላ ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ማሳሰቢያ፡- የጨቅላ ህጻናት ህክምናና ክብካቤ የሚጀምረው ከእርግዝና ቀን ጀምሮ ነው፡፡ የእናቶችና ጨቅላዎች ጤና ለማሻሻል በ 4 ‘ ሲ’ የሚገለፅ የክብካቤ ሰንሰለት (continnum of care) መከተል አስፈላጊ ነው፡፡

- **ነፍሰጡሮችና ወላድ እናቶችን ማግኘት (Contact):-** በቅድመ ወሊድ እና ድህረወሊድ ጊዜ ነፍሰጡር እና የወለዱ እናቶችን እንዲሁም ጨቅላዎችን ማግኘትና የቅድመ ወሊድ (Antinatal Care) እና የድህረ-ወሊድ ክብካቤ በጤና ተቋም ካልተቻለ በቤት መስጠትን ይመለከታል፡፡

❖ **ነፍሰጡሮች፣ወላድ እናቶችንና ጨቅላ ህፃናትን መረጃ መያዝ (Capture):-** ዕድሜያቸው ሳይደርስ የተወለዱ ወይም ዝቅተኛ ክብደት ያላቸውን፤ የመታፈን (asphyxia) ችግር ደጋጠማቸውን፤ ኢንፌክሽን ያላቸውን ጨቅላዎች እና አደገኛ ምልክቶች ያላቸውን እናቶች በቅድመ ወሊድ በወሊድና ድህረወሊድ ጊዜ ፈልጎ ማግኘትን ይመለከታል

❖ **ተገቢውን አገልግሎት መስጠት (Care):-** ተገቢውን ህክምና ፈጥኖ መጀመር ይመለከታል

❖ **አገልግሎት ማስጨረስ (Completion):-** ተገቢውን ህክምና እስከ መጨረሻ ቀን ድረስ መስጠትን ይመለከታል

በዚሁ መሰረት ሁሉም ነፍሰጡር ሴቶች ፡

❖ ከሶስት ወር በፊት እርግዝናቸውን ለጤና ባለሙያዎች እንዲያሳውቁ፤

❖ ቢያንስ ስምንት ጊዜ የቅድመ ወሊድ ምርመራ እንዲያገኙ፣

❖ በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት እንዲገኙ።

❖ ጨቅላ ህፃኑ እና እናትዬዋ በመጀመሪያው ሃያ አራት ሰዓት፣ በሦስተኛው ቀን፣ በሰባተኛው ቀንና በስድስተኛው ሳምንት የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣

❖ በእርግዝና ወቅት ጽንሱን ማውራት፡ መዘፈን፡ እና ሙዚቃ ማደመጥ እንዲሁም እናትየዋ ከአባት እና ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር፡ አለመናደድ እና ዘና ማለት ለልጁ አዕምሮ እድገት ዋሳኝ እንደሆኑ መምከር።

2.2.1.1. አዲስ ለተወለዱ ህፃናት የሚሰጥ አስፈላጊ ክብካቤ (Essential newborn care)

የጤና ኬላ ባለሙያዎች ለተወለዱ ህፃናት ወዲያው ተገቢውን ክብካቤ በሚሰጡበት ጊዜ፤የታመሙ ህጻናትን በሚመረምሩበትና በሚያክሙበት ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ በተቀመጠው አግባብ መሠረት መሆን አለበት።

✓ አራስ ሕጻኑን ስናዋልድ ወደ እናቱ ሆድ ቀና በማድረግ ማዋለድ

✓ በደረቅ ጨርቅ የአራስ ሕጻኑን ገላ ማደራረቅና በሌላ ደረቅ ጨርቅ ጭንቅላቱን ጭምር መጠቅለል፤

✓ አተነፋፈሱን እና የሰውነቱን/ የቆዳውን ቀለም ማስተዋል፤ ትንፋሽ በደቂቃ ከ30 በታች ወይም ሰማያዊ ምላስ፣ ከንፈር፣ የሰውነት ቆዳ ካለው ወይም የሚያጣጥር (gasp) ከሆነ ነፍስ እንዲዘራ ለዚሁ በተዘጋጁ ግብዓቶች በመጠቀም ድጋፍ (resuscitate) ማድረግ፤

✓ እትብቱን ከአራስ ሕጻኑ ሆድ ሁለት ጣት በመራቅ መቋጠር፤ ከቋጠሮው እንደገና ሁለት ጣት በመራቅ ሁለተኛ መቋጠር። በሁለቱ ቋጠሮች መካከል እትብቱን መቁረጥ፤

✓ እናቱ የአራስ ሕጻኑን ገላ ከገላዋ አስጠግታ እንድታቅፈው እና ጡት መጥባት ወዲያውኑ እንዲጀምር ማድረግ፤

✓ አራስ ሕጻኑ አይን ውስጥ የቴትራሳይክሊን ቅባት ማድረግ፤

✓ የአራስ ህጻኑን እንብርት የክሎሬክሲዲን ቅባት መቀባትና እናትየዋን ስለአቀባቡ በማስገንዘብ በቀን አንድ ጊዜ ለሰባት ቀን መቀባት፤

✓ ጭኑ መሀል ላይ /በፊት ለፊት በኩል/ 1 ሚ.ግ ቫይታሚን ኬ መውጋት፤

✓ ክብደቱን መመዘን፤

ማሳሰቢያ፡-

- ✓ አራስ ሕጻኑን በየንስ በተወለደ በ24 ሰአት ውስጥ ገላውን እንዳየጥቡ ምክር መስጠት።
- ✓ አራስ ሕጻኑ በተወለደ ከ6-24 ሰዓት፣ በ3ኛውና በ7ኛው ቀን እንዲሁም በ6ኛው ሳምንት ለጨቅላውና ለእናትየዋ የድህረ ወሊድ አገልግሎት መስጠት፤
- ✓ እናት ኢንፌክሽንን እንዴት መከላከል እንደምትችል በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት መምከር
- ✓ የጨቅላውን ክብደት እና የጾንስ ዕድሜውን በተወለደ በ7 ቀን ውስጥ መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ክብካቤ እንዲያገኑ ማድረግ

2.2.1.2. በድህረ-ወሊድ ለህፃኑና ለእናቲቱ የሚሰጡ አስፈላጊ ክብካቤዎችን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መስጠት፤

ህጻኑ በተወለደ ከ6-24 ሰዓታት ውስጥ በሚደረግ የክትትል ጉብኝት ወቅት መሰጠት ያለባቸው አገልግሎቶች

- ❖ በህፃኑ እና በእናቱ ላይ አደገኛ ምልክቶች /danger signs/እንዳሉ ማጣራት እና ምልክት ከተገኘ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ
- ❖ እናትን/ቤተሰቡን የህፃኑን ሙቀት እንዴት እንደሚጠብቁ መምከርና በተግባር ማሳየት
- ❖ እናትን/ቤተሰቡን ስለ ጡት አጠባብ ማስተማር
- ❖ እትብቱ አለመድማቱን ማጣራት
- ❖ እናት እትብቱን የክሎርሄክሲዲን ቀባት በቀን አንዴ ለ7 ቀናት እንድትቀባ እሱ ካልተገኘ ምንም ነገር ሳትጨምር በንጽህና እንድትጠብቅ ማስተማር
- ❖ ሲወለድ ካልተመዘነ ህጻኑን መመዘንና ክብደቱን መመዝገብ
- ❖ ክብደቱ 2000 ግራም በታች ከሆነ ወይም ልጁ ያለጊዜው ከተወለደ፤ የካንጋሮ እናት አይነት ክብካቤ ላይ አድርገው ሪፈር ማድረግ
- ❖ የፖሊዮ ክትባት 0 እና ቢሲጂ (OPV0 እና BCG) መከተብ
- ❖ ሲወለድ ካልተሰጠው 1 ሚ.ግ ቫይታሚን ኬ እጭኑ ላይ መውጋት
- ❖ በጨቅላውና በእናቲቱ ላይ ቢከሰቱ ስለሚችሉ አደገኛ ምልክቶችና ባስቸኳይ ህክምና ስለመሻት ማስተማር
- ❖ የልጅን ፍላጎት መረዳት እና ተገቢዉን ምላሽ የመስጠት እንክካቤን ማስተማር
- ❖ ህጻኑ መስማት፡ ማየት፤ ማሽተት ስለሚችል ማዉራት እና ማጫወት ለአዕምሮአዊ እድገት እና መዳበር እንደሚጠቅም ማስተማር

በ3ኛ እና በ7ኛው ቀን የክትትል ጉብኝት ወቅት መሰጠት ያለባቸው አገልግሎቶች

- ❖ ከላይ የተገለፁት አገልግሎቶች እንዳሉ የሚሰጡ ሆነው በጨቅላውና በእናትየዋ ላይ ቢከሰቱ ስለሚችሉ አደገኛ ምልክቶችና በቶሎ ህክምና ስለመሻት ማስተማር ለጨቅላውና ለራሷ ስለሚደረግ የ3ኛው 7ኛው ቀናት እና የ6ኛው ሳምንት የድህረ ወሊድ ጉብኝት መምከር

በ6ኛው ሳምንት የክትትል ጉብኝት ወቅት መሰጠት ያለባቸው አገልግሎቶች

- ❖ አደገኛ ምልክቶች በጨቅላው ወይም በእናት መኖራቸውን መመልከት
- ❖ ጡት ብቻ ማጥባትን ማስተማርና ማበረታታት
- ❖ በበፊቱ ጉብኝት በተሰጡ ምክሮች እና ትምህርት ላዩ መነጋገር
- ❖ እናትን/ቤተሰቡን ሕጻኑን ከኢንፌክሽን ስለ መከላከል ማስተማር
- ❖ ጨቅላውን በኦፒቪ-1 ፔንታ-1 ፒሲቪ-1 እና ሮታቫይረስ-1 መከተብ
- ❖ የልጅን ፍላጎት መረዳት እና ተገቢዉን ምላሽ የመስጠት እንክካቤን ማስተማር
- ❖ ህጻኑ መስማት፡ ማየት፤ ማሽተት ስለሚችል ማዉራት እና ማጫወት ለአዕምሮአዊ እድገት እና መዳበር እንደሚጠቅም ማስተማር

2.2.1.3. የታመሙ ጨቅላዎችን በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ እንክብካቤና ክትትል እንዲያገኙ ማድረግ

<u>**ማሳሰቢያ፡-**</u> የሚከተሉት የጨቅላ ህፃናት አደገኛ ምልክቶች በጨቅላው ላዩ ከታዩ በፍጥነት በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ ክብካቤና ክትትል እንዲያገኙ ማድረግ ወይም ወደ ጤና ጣቢያ/ሆስፒታል መላክ

- ❖ ትንፋሹ በደቂቃ ከ30 በታች ወይም 60ና ከ60 በላዩ ከሆነ፣ ማቃሰት፣ ከባድ የደረት መሰርጎድ ካለው፣
- ❖ የምላስና ከንፈር መጥቆር/ሰማያዊ መሆን ካለው፤
- ❖ የማይጠባ ወይም በትንሹ ብቻ የሚጠባ ከሆነ፤
- ❖ ማንዘፍዘፍ ከነበረው ወይም አሁን ካለው፤
- ❖ የብብት ሙቀት ከ35.5⁰ ሴ በታች ወይም ሰውነቱ የሚቀዘቅዝ ከሆነ ወይም ትኩሳት (የብብት ሙቀት ከ37.5⁰ ሴ በላዩ) ካለው፤
- ❖ ሲነካካ ብቻ የሚንቀሳቀስ ወይም ሲነካካም ምንም የማይንቀሳቀስ ከሆነ፤
- ❖ የቀላ ወይም የሚመግል እትብት ካለው፤
- ❖ የሰውነት ቢጫ መሆን/ጆንዳስ ኖሮት እድሜው ከ24 ሰዓት ያነሰ ወይንም ከ14 ቀን በላዩ ከሆነ ወይም ቢጫ መሆኑ መዳፉን ወይም ውስጥ እግሩን ያካተተ ከሆነ፤

ሀ/ የታመመውን ጨቅላ ህፃን ከሚያሳየው የበሽታ ምልክት በመነሳት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መሰረት መሰየም

- ❖ የአተነፋፈስ ችግር ወይም የመታፈን ሁኔታ(Birth Asphyxia)
- ❖ በጣም ከቀኑ በፊት የተወለደ እና/ወይም በጣም ዝቅተኛ ክብደት፣ ከቀኑ በፊት የተወለደ እና/ወይም ዝቅተኛ ክብደት
- ❖ በጣም ከባድ በሽታ፣ውሱን የባክቴሪያ ኢንፌክሽን (Local Bacterial Infection)፣

- ❖ ከባድ የሰውነት ቢጫ መሆን/ጆንዲስን፣
- ❖ ተቅማጥ- ከፍተኛ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ፣ መለስተኛ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ፣ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ የሌለው፤ ከባድና የቆየ ተቅማጥ፣ የደም ተቅማጥ
- ❖ ለኤች አይ ቪ ኢንፌክሽን የተጋለጠ፣ያልታወቀ የኤች አይ ቪ ሁኔታ፣ የኤች አይ ቪ ኢንፌክሽን ያልተገኘበት
- ❖ የአመጋገብ ችግርና ዝቅተኛ ክብደት፣
- ❖ ለቀዳማዩ ልጅነት እድገት እና መዳበር ውስንነት የተጠረጠረ

በተጨማሪ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል።

- ✓ የክትባት ሁኔታ ማጣራት
- ✓ ከላዩ ከተጠቀሱት ሌላ የጤና ችግር እንዳለ ማጣራት
- ✓ ለእናት ስለ ራስዋ ጤንነት ተገቢውን ምክር መስጠት
- ✓ ቀዳማዩ ልጅነት እድገት ላይ ስለ ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ፤ መማር እና ማነቃቃት (early learning and stimulation) ላዩ መምከር

ለ/ የታመሙ ጨቅላ ህፃናትን በተሰጣቸው ስያሜ መሰረት ማከም

የአተነፋፈስ ችግር (Birth Asphyxia)-

- ❖ በአምቡ ባግና ማስክ/ጭንብል ተጠቅሞ ትንፋሽ መስጠት (ነፍስ እንዲዘራ ማድረግ)

በጣም ከቀኑ በፊት የተወለደ እና/ወይም በጣም ዝቅተኛ ክብደት ያለው ጨቅላ ህፃን፣

- ❖ **የጨቅላውን ሙቀት ጠብቆ የታለበ የጡት ወተት እየተሰጠው በካንጋሮ እናት አይነት ክብካቤ ላይ በማድረግ በፍጥነት ወደ ከፍተኛ ህክምና መላክ**

ከቀኑ በፊት የተወለደ እና/ወይም ዝቅተኛ ክብደት ያለው ጨቅላ ህፃን፣

- ❖ የጨቅላውን ሙቀት ጠብቆ፣ ጡት ቶሎ ቶሎ መስጠት
- ❖ ጡት መጥባት ካልቻለ ጡት በተገቢው ሁኔታ አልቦ በኩባያ ማጠጣት

በጣም ከባድ በሽታ፣

- ❖ የቅድመ ሪፈራል ህክምና መስጠት፤ በፍጥነት ወደ ከፍተኛ ህክምና መላክ።
- ❖ ህጻኑን ሪፈር ማድረግ ካልተቻለ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ማከም።

ውሱን የባክቴሪያ ኢንፌክሽን፣

- ❖ ህጻኑን በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ማከም።

ከባድ የሰውነት ቢጫ መሆን/ጆንዲስን፣

❖ የጨቅላውን ሙቀት ጠብቆ የታለበ/የጡት ወተት እየተሰጡ በፍጥነት ወደ ከፍተኛ ህክምና መላክ

የሰውነት ቢጫ መሆን/ጆንዲስ

❖ የጨቅላውን ሙቀት ጠብቆ፣ ጡት ወተት ቶሎ ቶሎ መስጠት

❖ ከተወለደ ከሁለት ሳምንት ጀምሮ በየቀኑ ከ15-20 ደቂቃ አብዛኛው የገላው ክፍል ተገልጦ የጠዋት ጸሐይ ብርሃን እንድታሞቀው እናትን መምከር

ተቅማጥ

✓ **ከፍተኛ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ፣**

❖ ጡት ቶሎ ቶሎ እንድታጠባ በመምከር፣ ለእናት የምታጠጣው ኦ አር ኤስ በመስጠት፣ ሙቀት በመስጠት ወደ ከፍተኛ ህክምና መላክ

✓ **መለስተኛ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ፣**

❖ በፕላን ቢ መሰረት ኦ አር ኤስ በጤና ኬላ ውስጥ መስጠት

❖ የዚንክ እንክብል መስጠት

❖ እናት ጡት ቶሎ ቶሎ እንድታጠባ በመምከር

✓ **የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ የሌለው፤**

❖ በፕላን ኤ መሰረት ኦ አር ኤስ በቤት ውስጥ መስጠት

❖ የዚንክ እንክብል መስጠት

❖ እናት ጡት ቶሎ ቶሎ እንድታጠባ በመምከር

✓ **ከባድና የቆየ ተቅማጥ ወይም የደም ተቅማጥ**

❖ የጨቅላውን ሙቀት ጠብቆ፣ የጡት ወተት ቶሎ ቶሎ እየተሰጠ ለእናት የምታጠጣው ኦ አር ኤስ በመስጠት፣ በፍጥነት ወደ ከፍተኛ ህክምና መላክ

ቀዳማይ ልጅነት ክብከቤ

✓ **የእድገት ዉስንነት የሌለዉ**

  ❖ ቤተሰብን በማድነቅ እንዲሁ እንዲቀጥሉ ማበረታት፤ ተጨማሪ ቁልፍ መልክትን መንገር

✓ **ለእድገት ዉስንነት የተጠረጠረ**

  ❖ የምክር አገልግሎትን ለቤተሰብ መስጠት እና ለክትትል ለወር መቅጠር

✓ **የእድገት ውስንነት ያለው**

❖ ለቤተሰብ ምክር መስጠት እና ለተሻለ ህክምና ሪፈር ማድረግ

ለኤች ኤይ ቪ ኢንፌክሽን የተጋለጠ፡

❖ ከሁለት አንዱ ብቻ ከተመረመሩ ሁለቱም እንዲመረመሩ ማድረግ፤

❖ ክትትል እንዲጀምሩ ወይም እንዲቀጥሉ መምከር፤

ያልታወቀ የኤች ኤይ ቪ ሁኔታ፡

❖ እናትየው በፈቃደኝነት እንድትመረመር መምከር፤

የኤች ኤይ ቪ ኢንፌክሽን ያልተገኘበት፡

❖ ምርመራ በማድረግዋ ማመስገንና በቀጣዩነት ራስዋን ከኤች ኤዩ ቪ እንድትጠብቅ መምከር፤

የአመጋገብ ችግርና ዝቅተኛ ክብደት፡

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት በተዘረዘረው መሰረት ተገቢውን የምክር አገልግሎት መስጠት፤

ሐ/ የታመሙ ጨቅላዎችን በተሰጣቸው ስያሜ መሰረት ተገቢውን ምክርና ክትትል መስጠት

❖ እናትዋን በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ምክር መስጠት

ክትትልና የጉብኝት ቀጠሮ የጊዜ ሰሌዳ

<table>
<tr><td>የህጻኑ ችግር</td><td>መመለሻ ቀን</td><td rowspan="8">በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት ውስጥ ዝርዝራቸው የተጠቀሰው የበሽታ መባባስ ምልክቶች ካሉ እናት ቀጠሮ ሳትጠብቅ ባስቸኳይ ጨቅላውን ይዛ እንድትመለስ መምከር</td></tr>
<tr><td>በጣም ከባድ በሽታ</td><td>በየቀኑ ለ7 ቀን</td></tr>
<tr><td>ውስን ባክቴሪያ ኢንፌክሽን</td><td rowspan="4">በ2ኛው ቀን</td></tr>
<tr><td>ጆንዲስ</td></tr>
<tr><td>ተቅማጥ</td></tr>
<tr><td>የአመጋገብ ችግር</td></tr>
<tr><td>ዝቅተኛ ክብደት</td><td>በ14ኛው ቀን</td></tr>
<tr><td>የእድገት ዉስንነት</td><td>30 ቀን</td></tr>
</table>

ማሳሰቢያ፡- በእያንዳንዱ ቀጠሮ ጊዜ ጨቅላውን በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት የክትትል ህክምና ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

2.2.2. ከሁለት ወር እስከ 5 ዓመት ያሉ ሕጻናት ሲታመሙ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት መመርመር፣ መሰየምና አስፈላጊውን ህክምና፣ እንክብካቤና ክትትል እንዲያገኙ ማድረግ

ሀ/ የታመሙ ህጻናት ከሚያሳዩት የበሽታ ምልክት በመነሳት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መሰረት በሽታቸውን መሰየም

አጠቃላዩ አደገኛ ምልክቶች- (ጡት መጥባት ወይም መጠጣት ፈጽሞ አለመቻል፤የሰዉነት መንዘፈፍዘፍ /ከንቫልሽን፤ራስን መሳት ወይም መንፍዘዝ፤በአፍ የወሰደው በሙሉና በወሰደዉ ቁጥር የሚያስመልሰው)

የሚታዩ በሽታዎች

- ❖ ለሳልና ለአተነፋፈስ ችግር ሲፈተሽ፤
    - ✓ ከባድ የሳንባ ምች ወይም በጣም ከባድ በሽታ፣የሳንባ ምች፣ጉንፋን ወይም ሳል
    - ❖ ለተቅማጥ ሲፈተሽ-
    - ✓ **ከፍተኛ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ**፣ መለስተኛ **የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ**፣ **የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ** የሌለው፤ ከባድና የቆየ ተቅማጥ፣ የቆየ ተቅማጥ፣ የደም ተቅማጥ
- ❖ ለትኩሳት ሲፈተሽ፤
    - ✓ በጣም ከባድ የትኩሳት በሽታ፣ ወባ፣ ወባ የሌለው ትኩሳት
- ❖ ህጻኑ ኩፍኝ አሁን ወይም ባለፈው 3 ወር ውስጥ ከነበረው መርምሮ መሰየም
    - ✓ የተወሳሰበ ከባድ ኩፍኝ፣ጉዳት ያደረሰ ኩፍኝ፣ኩፍኝ
- ❖ የጆሮ ችግር ካለበት፤
    - ✓ ማስቶይዳይተስ (Mastoditis)፣አጣዳፊ የጆሮ ኢንፌክሽን፣የቆየ የጆሮ ኢንፌክሽን
- ❖ ለምግብ እጥረት ሲፈተሽ፤
    - ✓ የተወሳሰበ ከባድ የምግብ እጥረት፣ያልተወሳሰበ ከባድ የምግብ እጥረት፣ መለስተኛ የምግብ እጥረት፣ ከባድ የደም ማነስ፣የደም ማነስ
- ❖ ለኤች ኤዩ ቪ ኢንፌክሽን ሲፈተሽ ፤
    - ✓ የተረጋገጠ የኤች ኤዩ ቪ ኢንፌክሽን፣ኤች ኤዩ ቪ ኢንፌክሽን ሊኖርበት የሚችል (ለኤች ኤዩ ቪ ኢንፌክሽን የተጋለጠ)፣ ያልታወቀ የኤች ኤዩ ቪ ሁኔታ፣ የኤች ኤዩ ቪ ኢንፌክሽን ያልተገኘበት

በተጨማሪ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

- ❖ የክትባትና የቫይታሚን ኤ እንክብል መውሰድ/አለመውሰድ ሁኔታ ማጣራት
- ❖ ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ የጤና ችግር እንዳለ ማጣራት

❖ ለእናት ስለ ራስዋ ጤንነት መጠየቅና ተገቢውን ምክር መስጠት

ለ/ የታመሙ ከሁለት ወር እስከ 5 ዓመት ህጻናትን በተሰጣቸው ስያሜ መሰረት ማከም

አጠቃላዩ አደገኛ ምልክቶች፡-አንድ ህጻን ማንኛውም አደገኛ ምልክት ሲኖረው በአስቸኳይ ምርመራውን በማጠናቀቅ አስፈላጊውን ዕርዳታ አድርጎ ለከፍተኛ ሕክምና መላክ

ከባድ የሳንባ ምች ወይም በጣም ከባድ በሽታ

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ቅድመ ሪፈራል ህክምና በመስጠት ለበለጠ ሕክምና ኦክሲጂን ላዩ አድርገው ሪፈር ማድረግ።

የሳንባ ምች

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ማከምና መንከባከብ

ጉንፋን ወይም ሳል

❖ በቤት ዉስጥ ስለሚደረግ እንክብካቤ ለእናት ምክር መስጠት (ለምሳሌ ሳሉን የሚታስታግስበትና ጉሮሮውን የምታርስበት አቤት የተዘጋጀ ፈሳሽ መስጠት)

ተቅማጥ

✓ **ከፍተኛ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ፤**

❖ በፕላን «ሲ» መሰረት ተገቢውን ፈሳሽ በመስጠት ማከም

✓ **መለስተኛ የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ፤**

❖ በፕላን «ቢ» መሰረት ኦ አር ኤስ በጤና ኬላ ውስጥ መስጠት

❖ የዚንክ እንክብል መስጠት

❖ እናት ጡት ቶሎ ቶሎ እንድታጠባ ወይም እንድትመግብ መምከር

✓ **የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ የሌለው፤**

❖ በፕላን « ኤ » መሰረት ኦ አር ኤስ በቤት ውስጥ መስጠት

❖ የዚንክ እንክብል መስጠት

❖ እናት ጡት ቶሎ ቶሎ እንድታጠባ ወይም እንድትመግብ መምከር

✓ **ከባድና የቆየ ተቅማጥ፤**

❖ ሌላ የከባድ በሽታ ምልክት ከሌለው ወደ ከፍተኛ ህክምና ከመላኩ በፊት **የሰውነት ፈሳሽ መቀነስ** በተገቢው ዕቅድ (ዕቅድ «ሲ » ወይም « ቢ ») ማከምና መላክ፤

❖ ቫይታሚን ኤ እንዳስፈላጊነቱ መስጠት

❖ የዚንክ እንክብል መስጠት

✓ **የቆየ ተቅማጥ፣**

❖ ቫይታሚን ኤ እንዳስፈላጊነቱ መስጠት

❖ የዚንክ እንክብል መስጠት

❖ ለበሽታው አስፈላጊ የአመጋገብ ምክር ለእናት መስጠት

✓ **የደም ተቅማጥ**

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ህክምና መስጠት

❖ የዚንክ እንክብል መስጠት

በጣም ከባድ የትኩሳት በሽታ

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት የቅድመ ሪፈራል ህክምና ሰጥቶ በፍጥነት ለከፍተኛ ህክምና መላክ

ወባ

❖ በምርመራ እንደተገኘው ወባ አይነት በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ህክምና መስጠት

ከባድና የተወሳሰበ ኩፍኝ

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት የቅድመ ሪፈራል ህክምና ሰጥቶ በፍጥነት ለከፍተኛ ህክምና መላክ

ጉዳት ያደረሰ ኩፍኝ

❖ ሙሉ የቫይታሚን ኤ ህክምና መስጠት

❖ የዓይን መግል ካለው የቴትራሳይክሊን ቅባት ማድረግ

❖ የአፍ ቁስል በጀቪ ማከም

ኩፍኝ

❖ ሙሉ የቫይታሚን ኤ ህክምና መስጠት

ማስቶይዳይተስ

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት የቅድመ ሪፈራል ህክምና ሰጥቶ በፍጥነት ለከፍተኛ ህክምና መላክ

አጣዳፊ የጆሮ ኢንፌክሽን

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ህክምና መስጠት

የቆየ የጆሮ ኢንፌክሽን

❖ የህጻኑን ጆሮ በመጥረግ ደረቅ ሆኖ እንዲቆዩ ማድረግ

የተወሳሰበ ከባድ የምግብ እጥረት

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት የቅድመ ሪፈራል ህክምና ሰጥቶ በፍጥነት ለከፍተኛ ህክምና መላክ

ያልተወሳሰበ ከባድ የምግብ እጥረት

❖ የተመላላሽ የምግብ እጥረትና ተዛማጅ በሽታዎች ህክምና (OTP) አገልግሎት እንዲያገኝ መዝግቦ በመመሪያው መሰረት ህክምናና እንክብካቤ መስጠት

መለስተኛ የምግብ እጥረት

❖ የህጻኑን የአመጋገብ ሁኔታ መርምሮ እንደ አስፈላጊነቱ በቻርት ቡክሌት መሰረት ለእናትየዋ ምክር መስጠት፣

ከባድ የደም ማነስ

❖ ህጻኑን በፍጥነት ለከፍተኛ ህክምና መላክ

የደም ማነስ

❖ የህጻኑን የአመጋገብ ሁኔታ መርምሮ እንደ አስፈላጊነቱ በቻርት ቡክሌት መሰረት ለእናትየዋ ህክምናና ምክር መስጠት፣

የተረጋገጠ የኤች ኤይ ቪ ኢንፌክሽን

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ህክምናና ክብካቤ መስጠት

ኤች ኤይ ቪ ኢንፌክሽን ሊኖርበት የሚችል (ለኤች ኤይ ቪ ኢንፌክሽን የተጋለጠ)

❖ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ህክምናና ክብካቤ መስጠት

❖ የኤች ኤዩ ቪ ምርመራ እንዲያገኝ ማድረግ

ያልታወቀ የኤች ኤይ ቪ ሁኔታ

❖ እናት በፈቃደኝነት ስለሚደረግ የኤች.ኤዩ.ቪ ምርመራ ማስረዳትና እንድትመረመር መምከር

የኤች ኤይ ቪ ኢንፌክሽን ያልተገኘበት

❖ ምርመራ በማድረጊ ማመስገንና በቀጣዩነት ራሰዋን ከኤች ኤዩ ቪ እንድትጠብቅ መምከር

የክትባትና የቫይታሚን ኤ ሁኔታ ማጣራት

❖ ክትባቶቹን በወቅቱ መውሰዱን ማረጋገጥ

❖ ከ6 ወር በላዩ ከሆነና ቫዩታሚን ኤ ባለፈው ስድስት ወር ካልወሰደ መስጠት

የአንጀት ትላትል ህክምና

❖ ህጻኑ በ24 ወር በላይ ከሆነና ባለፈው ስድስት ወር ሜቤንዳዞል ወይም አልቤንዳዞል ካልወሰደ መስጠት

ቀዳማይ ልጅነት ክብከቤ

✓ **የእድገት ዉስንነት የሌለዉ**

❖ ቤተሰብን በማድነቅ እንዲሁ እንዲቀጥሉ ማበረታት፤ ተጨማሪ ቁልፍ መልዕክትን መንገር

✓ **ለእድገት ውስንነት የተጠረጠረ**

❖ የምክር አገልግሎትን ለቤተሰብ መስጠት እና ለክትትል ለወር መቀጠር

✓ **የእድገት ውስንነት ያለው**

❖ ለቤተሰብ ምክር መስጠት እና ለተሻለ ህክምና ሪፈር ማድረግ

ማስታወሻ፡- መንዘፍዘፍ (Convulsion) ሳለው ልጅ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ህክምናና ክብካቤ መስጠት። ለሁሉም ህጻናት በቻርትቡክሌቱ መሰረት የእድገት ዳሰሳ (Developmental Assessment) መስራት፡ ቤተሰብን ስለልጅ እድገት መምከር እና ተገቢ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል።

እናት የሚከተሉትን ቀላል ኢንፌክሽኖችን በቤት ወስጥ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት እንዴት እንደምታክም ማስተማር

❖ የዓይን ኢንፌክሽን

❖ የአፍ ውስጥ ቁስል

❖ የአፍ ውስጥ ፈንገስ ኢንፌክሽን (thrush)

❖ የሚመግል ጆሮ

❖ ጉንፋን

ሐ/ የታመሙ ህጻናት በተሰጣቸው ስያሜ መሰረት ተገቢውን ምክርና ክትትል መስጠት

❖ ለእናትዬዋ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ምክር መስጠት

ክትትልና የጉብኝት ቀጠሮ የጊዜ ሰሌዳ

የህጻኑ ችግር	የሚመለሰበት ቀን
❖ የሳምባ ምች ❖ ወባ፣ /ትኩሳት ወባ ያልተገኘበት/ ❖ ወባ የሌለው ትኩሳት (ወባማ ያልሆነ ቦታ) ❖ ደም የቀላቀለ ተቅማጥ ❖ መለስተኛ የሰውነት ፈሳሽ ማነስ	በ2ኛው ቀን
❖ የአመጋገብ ችግር (feeding problem) ❖ የሰውነት ፈሳሽ ማነስ የሌለው ተቅማጥ ❖ ጉንፋን ወይም የሳንባ ምች የሌለው ❖ የቆየ ጆሮ ኢንፌክሽን	በ5ኛው ቀን
❖ ደም ማነስ	በ14ኛው ቀን
❖ መለስተኛ የምግብ እጥረት ❖ የእድገት ዉስንነት	በ30 ኛው ቀን
❖ ያልተወሳሰበ ከባድ ምግብ እጥረት	በየ7ኛው ቀን

ከዚህ በታች ያሉት ምልክቶች ህጻኑ ላይ ከታዩ በፍጥነት መመለስ እንዳለበት ማስተማር	
ማንኛውም የታመመ ሕጻን	❖ መጥባት ወይም ፈሳሽ መውሰድ ካቆመ ❖ ህመሙ ከባሰበት ❖ ትኩሳት ካመጣ
ጉንፋን ወይም የሳንባ ምች የሌለው/ሳል ያለው ህጻን	❖ ፈጣን አተነፋፈስ ❖ የመተንፈስ ችግር
ተቅማጥ ያለው ህጻን	❖ ተቅማጡ ደም ከቀላቀለ ❖ ፈሳሽ አወሳሰዱ ከቀነሰ ወይም መጠጣት ካቃተው

ማሳሰቢያ፡- በእያንዳንዱ ቀጠሮ ጊዜ ህፃኑን በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት የክትትል ህክምና ማድረግ ያስፈልጋል።

2.3. የሚሰጡ አገልግሎቶችና የሚሰጡባቸዉ ቦታዎች

2.3.1. በጤና ኬላ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር

- የእናቶችና ጨቅላ ሕፃናት ድህረ ወሊድ ሃያ አራት ሰአት፣ በሦስተኛው ቀን፣ በሰባተኛ ቀን ክትትል
- የሕፃናት ምርመራና ህክምና
- የቀዳማዩ ልጅነት እድገት ክብካቤ
- የክትባት አገልግሎት
- የምክር አገልግሎት (የወሊድ ዝግጅት፣የእናትና ሕጻናት አመጋገብ፣ አደገኛ ምልክቶች ወዘተ)
- ሰርቶ ማሳየት (ኦ አር ኤስ፣ የህጻናት ምግብ፣ በመድሃኒት የተነከረ አጎበር አጠቃቀም፤ወዘተ)
- የነፍሰጡሮች ውይይት/ኮንፈረንስ

2.3.2. በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር

- የክትባት አገልግሎት
- የልማት ቡድን ወይይት- ይህ ውይይት በጎጥ ደረጃ በልማት ቡድን መሪዋ የሚመራ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችንና ሌሎች ባለሙያዎችን ሊጋብዙ ይችላሉ
- ቀዳማዩ ልጅነት ክብካቤ

2.3.3. በቤት ለቤት ጉብኝት ወቅት የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር

- የእርጉዝ እናቶች ልየታ
- የምክር አገልግሎት (የቅድመ ወሊድ ምርመራ፤ የወሊድ ዝግጅት፣የእናትና ሕጻናት አመጋገብ፣ አደገኛ ምልክቶች ወዘተ)
- ሰርቶ ማሳየት (ኦ አር ኤስ፣ የህጻናት ምግብ፣ በመድሃኒት የተነከረ አጎበር አጠቃቀም፤ወዘተ)
- የእናቶችና ጨቅላ ሕፃናት ድህረ ወሊድ 24 ሰዓት፣ በሦስተኛው ቀን፣ በሰባተኛ ቀን ክትትል
- የሕፃናት ምርመራና ህክምና
- የህጻናት የአእምሮ እድግት እና መዳበር ዳሰሳ (developmental Assessment)
- ከክትትል የጠፉትን አሰሳ

2.4. አገልግሎቶቹን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

2.4.1. የስራ አጋዥ (Job Aids)

ሀ/ በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ (IMNC)፣ የተቀናጀ የህፃናት ህክምናና ክብካቤ (ICCM)/ ወይም የተቀናጀ የጨቅላ ህፃናት ህክምናና ክብካቤ (CBNC) ቻርት ቡክሌት፤ የአደገት ጳሰሳ እና ምክር መስጫ ካርድ/ፖስተር፡ ነፍስ መዝሪያ መከታተያ ቅጽ (Resuscitation flow chart)

ለ/ የክትባት ማኑዋል

ሐ/ የጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ መዝገብ (registration books – SYI, SC)

መ/ የእናቶች፣ የጨቅላና ህፃናት ጤና (MNCH) መዝገብ

ረ/ የመድኃኒት መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ

ሰ/ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ (modified DHIS2 reporting formats)

ሸ/ ወርሃዊ የግብዓት ሪፖርት መጠየቂያ ፎረም (Health Post Monthly Report and Resupply Request Form (HPMRR)

በ/ አደገኛ ምልክት ያለባቸውን ህጻናት ለምርመራና ህክምና ወደ ሌላ ጤና ተቋም መላኪያ ቅፅ

2.4.2. የህክምና ቁሳቁሶች

- የጨቅላና የህጻናት ክብደት መለኪያ ሚዛን
- አምቡ ባግና ማስክ
- ፔንጉዊን መምጠጫ (Penguin suction)
- የሠውነት ሙቀት መለኪያ (Thermometer)
- መርፌና ሲሪንጅ (1cc; 2cc)
- MUAC መለኪያ ቴፕ
- የእጅ ጓንት (Glove)
- የORT corner ማቴሪያል
- የህጻናት IV cannulaየወለድ እና ድህረ ወሊድ ክፍል ማሞቂያ (heater)
- አዲስ ለተወለደ ልጅ ማረፊያ (new born corner) እና ሰዓት
- የወባ መመርመሪያ (RDT for malaria)

- **መድሃኒቶች/Medicines and supplies፡**

  - ቴትራሳይክሊን የዓይን ቅባት/መድሃኒት
  - ቫይታሚን ኬ (በመርፌ የሚሰጥ)
  - ክሎርሄክሲዲን ቅባት
  - አሞክሳሲሊን መድሃኒት
  - ጀንታማይሲን ብልቃጥ (በመርፌ የሚሰጥ)
  - ኮትሪሞክሳዞል መድኃኒት
  - ሲፕሮፍሎክሳሲሊን መድኃኒት
  - ኦ አር ኤስ
  - ዚንክ እንክብል
  - ግሉኮስ 40%
  - በደም ስር የሚሰጥ ፈሳሽ (Ringer's lactate, Normal Saline)
  - ጀ ቪ (Gentian violet)
  - ቫይታሚን ኤ
  - ኮአርተም
  - ክሎሮክዊን ሽሮፕና እንክብል
  - አርተሱኔት በፊንጢጣ የሚሰጥ
  - አርተሜቴን (በመርፌ የሚሰጥ)
  - አልቤንዳዞል/ሜብንዳዞለ
  - ፕላምፒነት/(RUTF)
  - የክትባት መድኃኒቶች
  - አይረን ታብሌት
  - ፓራሴታሞል ሽሮፕ፣ እንክብልና በፊንጢጣ የሚሰጥ
  - ሳልቡታሞል ሽሮፕና እንክብል
  - አድሬናሊን
  - በመርፌ የሚሰጥ ዳያዜፓም
  - የጥጥ ጥቅል፣ጎዝ

- ጸረ ተዋሲያን (Disinfectant) -አልኮል፣ ክሎሬክሲዲን ወዘተ
- Quinolone Eardrops (Ciprofloxacin, Norfloxacin, or Ofloxacin ear drops)
- Gentamycine injection
- Ceftriaxone or IM/IV Ampicillin

2.5. የሚጠበቁ ውጤቶች

- በሕብረተሰቡ ውስጥ ጎልተው በሚታዩ የህፃናት ጤና ችግሮች ላዩ ያተኮረ የጤና አጠባበቅ ትምህርት በተለያዩ ዘዴዎች በመስጠት ሕብረተሰቡ የባህሪዩ ለውጥ እንዲያመጣ ይደረጋል፣
- ህብረተሰቡ ለእናቶችና ህፃናት የሚሰጡትን የጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች በሚገባ ያውቃል፣ የአገልግሎቶችም ተጠቃሚ ይሆናል፣
- ሕብረተሰቡን የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ በማስተማር በእናቶችና በህፃናት ላዩ የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ይቀንሳሉ፣
- የቅድመ ወሊድ አገልግሎት ተጠቃሚ ነፍሰጡር እናቶች ቁጥር ይጨምራል፣
- በሰለጠነ ባለሙያ በአቅራቢያው በሚገኙ የጤና ድርጅቶች የወሊድ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑ እናቶች ቁጥር ይጨምራል፣
- ለእናትና ለጨቅላ ህፃናት የሚደረግ የድህረ ወሊድ ክብካቤ ሽፋን ከፍ ይላል፣
- በሰለጠነ ባለሙያ የሚታከሙና ክብክቤ የሚደረግላቸቸው የታመሙ ጨቅላዎችና ህፃናት ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል፤
- እናቶችንና ሕፃናትን በወቅቱ ክትባታቸውን እንዲያገኙ በማድረግ የክትባት ሽፋን ከፍ ይላል፣በክትባት የምንከላከላቸው በሽታዎችም በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳሉ።
- የእናቶችና ሕፃናት ሕመምና ሞት ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል፣
- ህብረተሰቡን በህፃናት ላዩ ሲደርሱ ስለሚችሉ አደጋዎችና ቅድመ ጥንቃቄያቸው በማስተማር በህፃናት ላዩ ሲደርሱ የሚችሉ አደጋዎች ይቀንሳል።
- መሰረታዊ የጤና አገልግሎት መረጃዎች በትክክል ተመዝግበው ይያዛሉ፡ ለዕቅድ እና ግምገማና ምዘናም ይውላሉ።

2.6. ዋና ዋና መለኪያዎች

በጤና ኬላ የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች የተሰጠውን የጤና አገልግሎት ወጤታማነት ጠቋሚ መረጃዎች (Core Indicators) በመመስረት በየወቅቱ መገምገምና መመዘን ይኖርባቸዋል፡፡ ለግምገማና ለምዘና ከምንጠቀሙባቸው ዘዴዎችም ውስጥ የሚከተሉት ዋናዎቹ ናቸው፡፡

❖ በየወቅቱ በወረዳና በጤና ጣቢያ በሚደረግ የድጋፋዊ ክትትል ጉበኝት

❖ በየወሩ በሚደረግ የስራ ግምገማ

❖ በየወቅቱ በሚደረግ ሪፖርትና ግብረ መልስ (ወርሃዊ፤ሩብ፤ 6 ወርና ዓመታዊ ሪፖርቶቾ)

❖ በየወቅቱ በሚደረጉ ጥናቶች

2.7. ጠቋሚ መረጃዎች (Core Indicators)

❖ በህይወት ከተወለዱ ጨቀሳዎች ወስጥ የክሎሮሄክሳይን የእምብርት ቅባት ያገኑ ህዓናት፤

❖ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሳንባ ምች/ኒሞኒያ የያዛቸው ህዓናት ብዛት፣

❖ በሳንባ ምች/ኒሞኒያ ፀጠቃሱ ተብለው ከሚታሰቡ ህዓናት መካከል ህክምና ያገኑ ህዓናት፤

❖ በተወሰነ ጊዜ ወስጥ የተቅማጥ በሽታ የያዛቸው ልጆች ብዛት፣

❖ ተቅማጥ ይኖራቸዋል ተብሎ ከማታሰቡ ህዓናት መካከል ህክምና ያገኑ ህዓናት፤

❖ ዕድሜአቸው ከሁለት ዓመት በታች የሆኑና የእድገት ክትትል የሚደርግላቸው ሕዓናት፣

❖ በጣም ከባድ በሽታ (very severe disease) ፀጠቃሱ ተብለው ከሚታሰቡ ጨቅላዎች መከከል በጨቅላና ህጻናት ህክምናና ክብካቤ ቻርት ቡክሌት መሰረት ህክምናቸውን የጨረሱ ሽፋን

❖ ቫይታሚን ኤ በመከላከያ (supplementation) መልክ የተሰጣቸው ሕዓናት፣

❖ የአንጀት ትላትሎች መድሃኒት (deworming) የተሰጣቸው ሕዓናት፤

❖ በህይወት ከተወለዱ ጨቀሳዎች ወስጥ የልደት ምዝገባ የተደረገላቸው፣

❖ የቀዳማዩ ልጅነት እድገት እና መዳበር ምርመራ የተሰራላቸውሕዓናት በመቶኛ

ምዕራፍ 3
የክትባት አገልግሎት

3

3.1. በመሰረታዊና አጠቃላይ ጤና ኬላ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት (Activities/ interventions)

ሁሉም የክትባት አገልግሎቶች በአጠቃላዩና መሰረታዊ ጤና ኬላዎች በተመሳሳዩ ሁኔታ የሚሰጡ ዩሆናል።

የሚከናወኑ ተግባራት ዝርዝር
የዕቅድ ዝግጅት /Planning/
የተቀናጀ ዓመታዊ ዕቅድ /Integrated Annual Planning)
ለመደበኛ ክትባት የሚሰራ ማይክሮ ፕላን/Micro planning for Routine Immunization/
የክትባት ዘመቻ ዕቅድ ዝግጅት/SIAs Micro Planning /
የህብረተሰብ ንቅናቄ/Demand generation and Community mobilization/
ለመደበኛ ክትባት አገልግሎት/Routine Immunization/
ለPeriodic Intensified Routine Immunization/PIRI/
ለCatch Up Vaccination
ለክትባት ዘመቻ/Supplementary Immunization Activities/SIAs
የክትባት አገልግሎት አሰጣጥ/Service provision/
የጤና ትምህርትና የምክር አገልግሎት/Health education and Counseling (Immunization, AEFI etc.)
✓ BCG
✓ HepB birth dose
✓ Oral Polio Vaccine
✓ Pentavalent Vaccine (Diphtheria, Pertussis, Tetanus, HepB, Hib)
✓ Pneumococcal Conjugate vaccine/PCV/
✓ Rota Vaccine
✓ Inactivated Polio Vaccine/IPV/
✓ Measles Containing Vaccine/MCV/
✓ Tetanus Diphtheria Vaccine/Td/
✓ Human Papilloma Virus Vaccine/HPV/
✓ COVID 19 Vaccines (Primary & Booster doses)
በሚቀጥሉ ጊዜያት የሚጀመሩ የክትባት ዓይነቶች
✓ Yellow Fever Vaccine
✓ Meningitis A Vaccine
✓ Malaria Vaccine

የክትባት ግብዓት አስተዳደር/Vaccine Supply/ Logistics Management /
የክትባት ግብዓቶችን በወቅቱ መጠየቅና ማምጣት/Request the Vaccine antigens and collect on timely basis
የክትባት ግብዓቶች ቁጥጥር /Monitor the Vaccine supply stock status using ledger book /
የፍሪጅ ሙቀት በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ መከታተል ና ተገቢዉን ማስተካከየ እርምጃ መዉሰድ/Temperature Monitoring twice per day (Morning and Evening) and take corrective action accordingly and document properly
የቀዝቃዜ ሰንሰለት መቆጣጠሪያ እቃዎችን ቆጠራ ማድረግ/Conduct CCE Inventory on regular bases
የቀዝቃዜ ሰንሰለት መቆጣጠሪያ እቃዎች ቅደመ መከላከል ስራ መስራት/Conduct preventive maintenance for CCEs/
የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ/Performance monitoring and Evaluation/
የተሰጡትን አገልግሎት በአግባቡ መመዝገብ እና ማደራጀት/Documentation of the services provided/using Tally sheet, Register, CHIS, etc./
በየወሩ የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም መከታተልና /Monthly EPI performance monitoring using monitoring chart/
በየወቅቱ የሚሰሩ ስራዎች ሪፖርት በማዘጋጀት መላክ Submit Regular Report using standard reporting format
የክትባት መጠነ ማቋረጥ ክትትል ማድረግ/ Dropout monitoring using defaulter tracer box/ tickler box/
የክትባት መድሃኒቶች ብክነት ክትትል ማድረግ/Actual vaccine wastage monitoring/
ደጋፊዊ ክትትል እና ክለሳዊ ስብሰባ ማድረግ /Conduct regular Supportive supervision & review meeting
የተለዩትን ክፍተቶችን በመለየት አፈጻጸማቸዉን መከታተል/Follow up action points and track the implementation status/
በክትባት ልንከላከላቸዉ የምንችላቸዉ በሽታዎች ቅኝትና ምላሽ/Vaccine preventable Disease/VPD/ Surveillance and response /
✓ **Measles like rash case**
✓ **Acute Flaccid Paralysis /AFP/cases**
✓ **Tetanus**
✓ **AEFI case surveillance**
✓ **Other VPDs**
የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ /Waste Management /
ክትባት በሚሰጥበት ወቅት ትክክለኛውን የኢንፌክሽን መከላከልና መቆጣጠር ስልት መከተል
ትክክለኛ የቆሻሻ አወጋገድ መንገዶችን በመከተል ቆሻሻን ማስወገድ

3.1.1. የሁኔታ ትንተና እና ዕቅድ ዝግጅት (Sitautional Analysis and planning)

- ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት ያለፈዉን ዓመት አፈጻጸም በመገምገም የነበሩትን ጠንካራ ጎኖች፣ ድክመቶች፣ መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶችን መለየት፤
- በጤና ኬላው ስር ያሉትን ለመደበኛ ክትባት ታሳሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መረጃ መሰብሰብና በየስድስት ወሩ ወቅታዊ ማድረግ፤
- በጤና ኬላው ስር የሚገኙት መንደሮች/ጎጦች የህዝብ ብዛት፣የክትባት ታሳሚዎች ብዛት እና ክትባት የሚያገኙበት ሁኔታ (ቋሚ/static, ውሎ ገብ/outreach እና mobile/ተንቀሳቃሽ) ተለዩቶ በካርታ መቀመጥ ዩኖርበታል፤
- ለጤና ኬላው የክትባት ታሳሚዎች የሚበቃ መድኃኒት በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ትንበያ በማዘጋጀት በወር ምንያክል የክትባት መዳኃኒት እንደሚያስፈልግ በመለየት የክትባት መዳኃኒቶች የሚጠየቁበት የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት መመዝገብ፤
- እንደአስፈላጊነቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ወዩም በተወሰኑ ቦታዎች ለሚካሄድ ዘመቻ ለክትባቱ ታሳሚ የሆኑትን ህጻናት ወዩም ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች መረጃ መሰብሰብ/Real Microplanning/፤
- የፀደቀውን የዓመት ዕቅድ በሰምንት፣ በወር፣ በሩብ እና በግማሽ አመት በመከፋፈል ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ/ማድረስ፤
- በዕቅዱ ላይ ከማህበረሰብ እና ከመንግስት አደረጃጀቶች ጋር መወያየትና የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ መተማመን/መግባባት፤
- በጤና ኬላው ስር ከሚገኘው ህብረተሰብ ለክትባት አገልግሎት በቀላሉ ተደራሽ የማይሆኑ ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች መለየት፤
- ክትባት የሚሰጥባቸውን ቋሚ፣ ውሎ ገብ እና ተንቀሳቃሽ ቦታዎችን እና ስልቶችን (Vaccination service delivery points and strategies) ከህብረተሰቡ ጋር በመወያየት መለየትና አገልግሎቱ የሚሰጥበትን ፕሮግራም ማዘጋጀት፤
- በጤና ኬላው ስር በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸው በሽታዎች በቅርቡ ተከስተው እንደሆነ ለወደፊቱ ትግሩ ዳግም እንዳዩከሰት የቅኝትና ምላሽ ስራዎችን ማጠናከር፡፡
- የክትባት አገልግሎቱን ማግኘት ለሚገባቸው ታሳሚዎች ለማድረስ የማህበረሰቡ እና የመንግስት አደረጃጀቶች አቅም መጠቀም፡፡

3.1.2. ግንዛቤና ባለቤትነት ማሳደግ

3.1.2.1. ግንዛቤን ማሳደግ

በቀበሌው ያሉትን የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶችን አቅም በመገንባትና በመጠቀም ለህብረተሰቡ በቀላሉ የጤና መረጃ እንዲያደርሱ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

- የጤና ኬላ ባለሙያዎች በቀበሌው ያሉትን የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶችን አቅም መገንባትና በአገልገሎቱ ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጥ ዩጠበቅባቸዋል፣
- ለጎጥ ጤና መሪዎች፣ ለሴቶች ልማት ቡድንና ሌሎች የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶችን ማጠናከር፤ የተሻለ አፈጻፀም ያላቸውን ማበረታታት፤ ወደ ተግባር ያልገቡትን ወደ ተግባር ማስገባት፤ ድጋፍ ካስፈለገ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- ወርሃዊ ነፍሰጡር እናቶች ኮንፈረንስን በመጠቀም የእናቶችን፣ የአማቶችን፣ የባሎችን ግንዛቤ ማሳደግና በእናቶችና ህፃናት ጤና የሚኖራቸውን ሚና ማጎልበት፣
- በቀበሌው ያሉትን የኃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎችን እንዲሁም ተጽእኖ ፈጣሪዎችን በመለየት ማሰልጠንና ለማህበረሰብ ቅስቀሳ ብቁ ማድረግ፣
- በቀበሌው ያሉትን ሌሎች መዋቅሮችን ለምሳሌ አድር፣ ወዘተ..

3.1.2.2. ባለቤትነትን ማሳደግ

በክትባት ስለምንከላከላቸው በሽታዎች ግንዛቤ መኖር ብቻውን የአገልግሎት ተጠቃሚነትን ላያመለክት ይችላል። ስለሆነም ከእውቀት በተጨማሪ የህብረተሰቡን አመለካከት፣ ክህሎትና የመተግበር አቅም ማሳደግ ቁልፍ ተግባር ሊሆን ይገባል።

- አያንዳንዱ በቀበሌው ነዋሪ የሆነ ሰው በክትባት ዙሪያ ያለውን የዕውቀት፤ የአመለካከት፤ የባህሪ ክፍተት መለየት፣
- በተለዩ ክፍተቶች መሰረት ስለ ክትባት ጠቀሜታ፤ በክትባት መከላከል ስለምንችላቸው በሽታዎች፤ ክትባት ከወሰዱ በኋላ አልፎ አልፎ ሊከሰቱ ስለሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች ምን ማድረግ እንደሚገባ ወዘተ ማስረዳት፣
- በተለዩ ለጎጥ ጤና መሪዎችና ለሴቶች የልማት ቡድን መሪዎች የቤተሰብ ጤና መመሪያ ወይም ሌላ የክትባት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ግንዘቤያቸውን ማዳበር፣
- በክትባት ዙሪያ ወላጆች/አሳዳጊዎችና ሴሎች ተንከባካቢዎች፤ የጎጥ ጤና መሪዎችና የሴቶች ልማት ቡድን መሪዎች እንዲሁም የሴሎች አደረጃጀቶች መሪዎች ሚና ምን እንደሆነ በግልፅ ማስገንዘብ፣
- ማስከተብ የወላጆች/ተንከባካቢዎች ግዴታና ለህፃናት ደግሞ መከተብ መብታቸው እንደሆነ ግንዛቤ መፍጠር።

3.1.2.3. ለክትባት ታላሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉንም ክትባት መከተባቸውን ማረጋገጥ

- በቀበሌው ውስጥ በሁሉም መንደሮችና ጎጦች ያሉ ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በየጊዜው መዝግቦ መያዝ፤ ይህንንም በዋናነት የማህበረሰብ አደረጃጀቶችን በመጠቀም በየወቅቱ ምዝገባው ማካሄድ፤
- በቀበሌው ውስጥ ለክትባት አገልግሎት ተደራሽና ተደራሽ ያልሆኑትን አከባቢዎች እና ማህበረሰብ ክፍሎች መለየት፤ተደራሽ ያልሆኑበትን ምክንየት በዝርዝር በማስቀመጥ መፍታት፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው የክትባት ታላሚዎች ካሉ የክትባት አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤ ካለገኙ ምክንያቱን ማወቅና እንዲከተቡ ማድረግ፤
- ክትባት ጀምረዉ የቋረጡትን የክትባት ታላሚዎች በየጊዜው በመለየት ክትባታቸውን እንዳያጠናቅቁ ማድረግ፣

3.1.3. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እና በቅንጅት መስራት

- በቀበሌው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት (ለምሳሌ ትምህርት ቤቶች) ጋር በመተባበር ስለ ክትባት አገልግሎት ቁልፍ መልዕክቶችን በማስተላለፍ ሁሉም የክትባት ታላሚዎች ክትባት እንዲያገኙ ተቀናጅቶ መስራት፤
- አዲስ የተወለዱ ህፃናት የክትባት አገልግሎትና የልደት ሰርተፍኬት እንዲያገኙ በቀበሌው ከተመደቡ የወሳኝ ኩነቶች ሰራተኞች ጋር ተቀናጅቶ መስራት፣

3.2. የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት

ጥራቱን የጠበቀ የክትባት አገልግሎት ለመስጠት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንጻር ከዚህ በታች ለተመለከቱት ነጥቦች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት መተግበር ያስፈልጋል።

3.2.1. የክትባት አገልግሎት ለመስጠት የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች

- ለህብረተሰቡ የክትባት ታላሚዎች እድሜ፣ ክትባቱ የት እንደሚሰጥ እንዲሁም መቼ እንደሚሰጥ መረጃ በደንብ መተላለፍ ይኖርበታል፤
- የየእለቱን የክትባት ሥራ በተመለከተ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ተወካዮች ጋር በመሆን ሊከናወኑ የታቀዱ ተግባራትን በመለየት የሥራ ክፍፍል ማድረግ፤
- የክትባት አገልግሎት የሚሰጥባቸው ቦታዎች ዝግጁ መሆናቸዉን መረጋገጥ እና በተቻለ መጠን ክትባት ለመስጠት ምቹ በሆኑ ቦታዎች (ለምሳሌ፡- በቤት ውስጥ፣ በዛፍ ጥላ ስር ፣ ወዘተ) እንዲሆን ማዘጋጀት፤
- በየክትባት ዓይነቱ በቂ የክትባት መድሃኒቶች መኖራቸዉን ማረጋገጥ፤

- ❖ የክትባት መድኃኒቶች ቅዝቃዜ፣ ሙቀት እና ብርሃን በማይደረስበት ቦታ በአግባቡ ማስቀመጥ፤
- ❖ የክትባት መድሐኒቶች ያልተበለሹ መሆናቸውን (VVM፣ የመጠቀሚያ ጊዜ/expire date፣ shake test, ወዘተ) ማየትና ማረጋገጥ፤
- ❖ ለእለቱ የምንጠቀምባቸዉ ክትባቶች ስናወጣ ከዚህ ቀደም ተከፍቶ በጥሩ ሁኔታ (good condition) የተመለሱ፣ሳይከፈቱ የተመለሱ እና VMM stage II የደረሱ ክትባቶችን ቀድሚያ መጠቀም ተገቢ ነዉ (First Expiry First Use)፤
- ❖ የክትባት መድሃኒት መበጥበጫ ከመጠቀማችን ከ24 ሰዓት በፊት በፍሪጅ ዉስጥ መግባቱን ማረጋገጥ፤
- ❖ በቂ cool water packs መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፤
- ❖ ሌሎች ለክትባት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች (sysringe፣ መበጥበጫ፣ safet box፣vaccine carrier፣ foam pad፣ መመዝገቢያ ቅጻቅጾች፣ የክትባት ካርድ፣ ጥጥ ወዘተ) በሚፈለገው መጠንና ጥራት ለስራ ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና በተገቢው ሁኔታ ማስቀመጥ፤
- ❖ Adrenaline ከsyringe መኖሩን ማረጋገጥ



ስዕል-1 የክትባት አገልግሎት መስጫ ቦታ አዘገጃጀት ስዕላዊ መግለጫ

3.2.2. አገልግሎት መስጠት

- ❖ ለክትባት አገልግሎት የመጡ ተጠቃሚዎችን ስለክትባት ዓይነቶች፣ ጥቅም፣ ሊከሰቱ ስለሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች፣ወዘተ ላይ ትምህርት መስጠት እና ስለክትባቱ በቂ ግንዛቤ ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ፤
- ❖ ለክትባት የመጡትን ለክትባቱ ታለሚ መሆናቸዉን፣ ባለፈዉ የተሰጠ ክትባት አይነት እና አሁን የሚሰጠዉ ክትባት ምን እንደሆነ መለየት፤
- ❖ የተከታበውን ካርድ በመዉሰድ የተከተበዉንና የቀጠሮ ቀን መድረሱን ከተረጋገጠ በኋላ ተገቢዉን ክትባት መስጠት፤
- ❖ ክትባታቸውን ለወሰዱት ህፃናት የክትባት ካርድ ላይ ሙሉ መረጃ ከተመዘገበ በኋላ በቀጣዩ መቼ ማስከተብ/መከተብ እንዳለባቸው በማሳወቅ ካርዱን መስጠት፤
- ❖ አገልግሎቱን ያገኙ ተጠቃሚዎችን ታሊ በማድረግ በተገቢው መዝገብ ላይ በትክክል ማስፈር፤
- ❖ የክትባት አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት መድኃኒቶች ለሙቀት እንዳይጋለጡ መድኃኒቶቹን በfoam pad ላይ በማስቀመጥ በጥንቃቄ መጠቀም፤
- ❖ ክትባቱ የተሰጠበት መርፌና ሲሪንጅ በአግባቡ በsafety box ውስጥ መጨመሩንና ሌሎች ቆሻሻዎች በተገቢው መንገድ መወገዳቸውን ማረጋገጥ፤
- ❖ ክትባት የወሰዱት ግለሰቦች የተከታቢዉን ሁኔታ ለመቆጣጠር እንዳያመች ከ15-30 ደቂቃ ባለሙያዉ መከታተል በሚችልበት ቦታ ላይ በማስቀመጥ ክትትል ማድረግ፤

- ተከታቢዎች ወደ ቤታቸዉ ከሄዱ በኋላ የጎንዮሽ ችግር ካጋጠመ ወደ ጤና ተቋሙ እንዲመለሱ መልእክት ማስተላለፍ እና ከመጡ በኋላ አስፈላጊውን የህክምና እርዳታ መስጠት። ተጨማሪ የህክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ በአስቸኳይ ወደ ተሻለ ጤና ተቋም ማስተላለፍ፤
- በዕለቱ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተከተቡካሉ መቼና የት አገልግሎቱ እንደሚያገኙ መወሰን እና በአደረጃጀታቸው በኩል መልዕክት ማስተላለፍ፣
- ከተከፈቱ ለ28 ቀናት ጥቅም ላይ የሚውሉ የክትባት ዓይነቶች በዕለቱ ከተረፉ የተከፈቱበት ቀን ከተጻፈበት በኋላ የቅዝቃዜ ወሰን እንደተጠበቀ ወደ ፍሪጅ መመለስ እና በጥንቃቄ መያዝ፤
- ከተከፈቱ ስድስት ሰአት በላይ መቆየት የማይችሉ ክትባቶች (ለምሳሌ፡- BCG, Measles, ወዘተ) የተከፈቱበት ሰዓት ብልቃጡ ላይ መጻፍ እና ከተከፈቱ ከስድስት ሰዓት በኋላ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ እንዲሁም ወደ ፍሪጅ እንዳይመለሱ ለብቻቸው በማስቀመጥ የሚወገድበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ሪፖርት ማድረግ፤
- የእለቱ የክትባት ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከፍሉን/የክትባት መስጫ ቦታው፣ እቃዎችንና አካባቢውን በአግባቡ ማጽዳት

የክትባት አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰድ ይኖርበታል፡

- ክትባቱ ያልተበላሸ መሆኑን ማረጋገጥ / ለምሳሌ፡- VVM, Expire date, ወዘተ/፤
- የተከፈተዉ ክትባት፣ የክትባት መበጥበጫው፣ syringe እንዳይበላሽ (contaminated እንዳይሆን) መጠንቀቅ፤
- ክትባት በምንበጠብጥበት ወቅት መበጥበጫዉ በተገቢ የክትባት ቅዝቃዜ መጠበቂያ መሳሪያ መቀመጡን፣ ያልተበላሸ መሆኑን እና ተገቢ መበጥበጫ (ከክትባቱ ጋር ከአንድ ማምረቻ የተመረተ) መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ተከታቢዉ ትክክለኛ ታሳሚ መሆኑን እና ክትባቱ የማይሰጥበት የጤና ሁኔታ (Contra-ndication) አለመኖሩን ማረጋገጥ፤
- ክትባት ከፍሪጅ ካወጣን በvaccine carrier ዉስጥ እና በfoam pad ማስቀመጥ፤
- በIce-pack ላይ ባሉት ቀዳዳዎች ዉስጥ ክትባት ማስቀመጥ የተከለከለ ነዉ፤
- ክትባቱ በሚሰጥበት ወቅት ተገቢዉ ደዝ መሆኑን፣ ትክክለኛ አሰጣጥ (Correct injection site and route) ላይ መሰጠቱን ማረጋገጥ፤
- ተከታቢዉ ክትባት ከወሰደ በኃላ ለ15-30 ደቂቃ በቅርበት ክትትል ማድረግ፡፡

3.3. የቅዝቃዜ ሰንሰለት ቁሶች እና ቁልፍ መልዕክቶቻቸው

3.3.1. የቅዝቃዜ ሰንሰለትን መጠበቅና መከታተል

- የፍሪጅ አቀማመጥ ከግድግዳው ከ30—50 ሴንቲ ሜትር ርቀት፣ ከወለሉ ደግሞ ከ5—10 ሴንቲ ሜትር ከፍታ ላይ መቀመጡን ማረጋገጥና ንፅህናውን መጠበቅ፣
- ሁሉም የክትባት መድኃኒቶች ከ2 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ እስከ 8 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ (+20C እስከ +80C) መካከል መቀመጣቸውን በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ የሙቀት መጠኑን መመዝገብ አስፈላጊ ነዉ
- ድንገተኛ የፍሪጅ ብልሽት፣ የመብራት መቋረጥ ወይም የነዳጅ አቅርቦት ችግር ካጋጠመ የክትባት መድኃኒቶችን በvaccine carrier መያዣ የቅዝቃዜ መጠናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአቅራቢያው ወዳለው ጤና ተቋም ማስተላለፍና ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ችግሩን መቅረፍ፣
- የክትባት መድሃኒቶች ወደ ክትባት ጣቢያ ሲወሰዱ ትክክለኛ የቅዝቃዜ ሰንሰለታቸውን ጠብቆ ማጓጓዝና መጠቀም፣
- ክትባት ከመስጠታችን በፊት ውጭ የተቀመጠውን መበጥበጫ በፍሪጅ ውስጥ በማስገባት እንዲቀዘቅዝ ማድረግ፤ ሆኖም ግን መበጥበጫዎች ከፍሪጅ ውጭ እንደተቀመጡ እንስቶ ለክትባት መበጥበጫ መጠቀም ክትባቱን ስለሚጎዳው 24 ሰዓት ቀደም ብሎ ፍርጅ ውስጥ በማስገባት ለመበጥበጫነት መጠቀም፤

3.3.2. የክትባት መድኃኒቶች አቀማመጥ

የክትባት መድኃኒቶች በአጠቃላዩ መቀመጥ ያለባቸዉ የቅዝቀዜ መጠን ከ+2 ⁰C እስከ +8 ⁰C ነው፡፡ የክትባት መድሐኒቶች በፍሪጅ ዉስጥ በምናስቀምጥበት ወቅት አቀማመጣቸዉ ይለያያል፡፡ ይህም የክትባት መድኃኒት አቀማመጥ የሚወሰነዉ የክትባቱ መድሃኒት ዓይነትና የፍሪጅ ዓይነት ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡

በቅዝቃዜ (freeze sensitive) ቶሎ የሚበላሹ ክትባት ዓይነቶች Pentavalent,HPV,PCV,Td, IPV, Rota, ሲሆኑ በሙቀት ቶሎ የሚበላሹ (Heat Sensitive) ክትባት ዓይነቶች polio, Measles, BCG ናቸው፡፡

3.3.2.1. የፍሪጅ ዓይነቶችና የክትባት አቀማመጥ



ስዕል-2 ባለሁለት የክትባት መድኃኒቶች ማስቀመጫ ቅርጫት (ጎን ለጎን) ያለዉ ፍሪጅ ስዕላዊ መግለጫ



ስዕል-3 የክትባት መድኃኒቶች ማስቀመጫ ቅርጫት የሌለዉ ፍሪጅ ስዕላዊ መግለጫ

ከላይ በምስሉ ላይ እንደሚታየዉ የፍሪጅ ዓይነቶቹ የክትባት ማስቀመጫ **ቅርጫት** ያለዉና የቤለዉ ተብሎ ሲከፈል ይችላል። የፍሪጅ ማስቀመጫዉ ቅርጫት ያለዉ ሆኖ ሁለቱም ቅርጫቶቹ ጎን ለጎን ከሆነ በረዶዉ /Freezing Compartment/ ባለበት በኩል ያለዉ ቅርጫት ዉስጥ polio፣ BCG እና Measles ይቀመጣል። ከበረዶዉ/Freezing Compartment/ በተቃራኒዉ ባለዉ ቅርጫት ዉስጥ ደግሞ Pentavalent, HPV, PCV, Td, IPV እና Rota ክትባቶች ይቀመጣሉ።

አንዳንድ ፍሪጆች ቅርጫት የሌላቸው ስሆኑ በረዶዉ /Freezing Compartment/ ባለበት በኩል polio፣ BCG እና Measles ይቀመጣል። ከበረዶዉ/Freezing Compartment/ በተቃራኒዉ በኩል ደግሞ Pentavalent, HPV, PCV, Td, IPV እና Rota ክትባቶች ይቀመጣሉ።

ስዕል-4 ባለሁለት የክትባት መድኃኒቶች ማስቀመጫ ቅርጫት (ከላይና ከታች) ያለዉ ፍሪጅ ስዕላዊ መግለጫ

ከላይ በምሥሉ ላይ እንደሚታየዉ የተለያዩ የፍሪጅ ዓይነቶች ሆኖ ሁለት ቅርጫት ከላዩና ከታች ያለዉ ፍሪጅ ከሆነ ደግሞ የበረዶዉ ክፍል የሚገኘዉ ከታች በመሆኑ በቅዝቃዜ የማይበላሹት ማለትም polio፣ BCG እና Measles ክትባቶች ከስር ባለዉ ቅርጫት ዉስጥ ማስቀመጥ። ከላዩ ባለዉ ቅርጫት ዉስጥ ደግሞ በቅዝቃዜ ቶሎ ሲበላሹ የሚችሉትን የክትባት መድኃኒቶች ማለትም Pentavalent, HPV, PCV, Td, IPV እና Rota ክትባቶች ይቀመጣሉ።

ስዕል-5 ወደ ፊት ለፊት የሚከፈት የክትባት መድኃኒቶች ማስቀመጫ ፍሪጅ ስዕላዊ መግለጫ

ከላዩ በምስሉ ላይ እንደሚታየዉ ፍሪጁ ወደ ፊት ለፊት የሚከፈት ዓይነት ከሆነ ለፍሪጁ ቅዝቃዜ የሚረዳ Ice-packs ከላዩ በሚገኘዉ ክፍል ዉስጥ ስለሆነ polio፣ BCG እና Measles ክትባቶች በክትባት ማስቀመጫ compartment የላዩኛው መደርደሪያ ይቀመጣል። Pentavalent, HPV, PCV, Td, IPV እና Rota የክትባት መድኃኒቶች ቀጥሎ ባለዉ መደርደሪያ ይቀመጣሉ እንዲሁም የክትባት መበጥበጫዎች በመጨረሻው መደርደሪያ ላይ ይቀመጣሉ።



ስዕል-6 የክትባት መድኃኒቶች ማስቀመጫ cold box

Cold box የክትባት መድኃኒቶችን ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝና ፍሪጅ በሌለበት ወይም ፍሪጅ ባለበት ፍሪጁ ሲበላሽ እስከ 72 ሰዓት ሳይበላሹ ማቆየት የሚያስችል ነው። የዉስጡን ቀዝቀዜ መጠን ለመቆጣጠር የሚረዳ ፍሪጅ ታግ በዉስጡ ማስቀመጥና ሙቀቱንም ጠዋትና ማታ መመዝገብ ያስፈልጋል።

የክትባት መድኃኒቶች ማስቀመጫ

Vaccine carrier በአግባቡ በደንብ በIce-packs በበቂ ሁኔታ በአራቱም ማእዘኖች የውስጥ ክፍሉ ከተሞላ የክትባት መድኃኒቶችን ለ24 ሰዓት ማቆየት ያስችላል። ክትባቶች የሚፈልጉት የቅዝቃዜ መጠን እንደ ክትባቱ አይነት ስለሚለያይ እንደ Pentalent እና Td ክትባቶች በረዶ በሰራ Ice-packs ቢጓጓዙ ስለሚበላሹ በቀዝቃዛ Ice-packs መጓጓዝ አለባቸው። ስለሆነም የክትባት መድኃኒቶች ከጤና ኬላ ውጪ ሲጓጓዙ የውስጡን የቅዝቃዜ መጠን ለመቆጣጠር የሚረዳ ቴርሞ ሜትር ወይም Fridge Tag በውስጡ ማስቀመጥ ይገባል።

በCold box, Vaccine carrier እና Ice-packs አጠቃቀምና የክትባት መድኃኒቶች አያያዝ

በአጠቃላዩ የክትባት መድኃኒቶችን በ**Cold box እና Vaccine carrier** ስናስቀምጥ መደረግ የሚገባቸዉ ነጥቦች፡-

- በረዶ የሰሩትን **Ice-packs ከ**ፍሪጅ ውስጥ ማውጣትና በመጠኑ ማቅለጥ፤
- በመጠኑ የቀለጡትን **Ice-packs** በአራቱም አቅጣጫና ከታች ማስቀመጥ
- የክትባት መድኃኒቱንና መበጥበጫውን መሀል ላይ ማስቀመጥ
- የቅዝቃዜ መለኪያ Fridge Tag የክትባት መድኃኒቶቹ ላይ ማስቀመጥ፤
- ለ**Cold box** የቀለጠ Ice-pack በመድኃኒቱ ላይ ማድረግ፤
- ለvaccine carrier መሸፈኛ ስፖንጅ/Foam Pad/ ከላዩ በማድረግ ክዳኑን በትክክል መግጠም።

3.4. ፍሪጅ እንዳይበላሽ መደረግ የሚገባቸዉ የቅድመ መከላከል/Preventive Maintenance/ ስራዎች፡-

በየቀኑ

- ✓ የፍሪጁን የሙቀት መጠን መከታተልና በሚፈለገዉ የሙቀት ደረጃ ላይ መሆኑን ማረጋገጥ

በየሳምንቱ

- ✓ ፍሪጁን ዉስጡንና በሮቹን መወልወልና ማጽዳት
- ✓ የበረዶ ግግር የሰራ እንደሆነ በረዶዉን ማቅለጥና ማጽዳት
- ✓ የSolar panel ጠዋት ወይም ማታ አቧራ እንዳወለወል መከታተል

በየወሩ

- ✓ የኤሌክትሪክ ገመዱ ያልተበላሸ እና በትክክል እየሰራ መሆኑን ማረጋገጥ
- ✓ በግድግዳ ላይ ያለዉ ሶኬት እየሰራ መሆኑንና የፍሪጁ ገመድ በሶኬቱ ላይ መሰካቱን ማረጋገጥ

3.5. የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ

የክትባት አገልግሎት ፕሮግራም አፈጻጸም ላይ በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ማካሄድ ለአገልግሎት ሽፋን፣ ተጠቃሚነት፣ ፍትሐዊነት እና ጥራት መሻሻል አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የክትባት አገልግሎት አፈዓፀም ለማሻሻል የሚከተሉት ተግባራት ሊከናወኑ ይገባል፡-

3.5.1. የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም ክትትል

- ❖ ከቀበሌ አስተዳደር ተወካዮች፣ ከጤና ጣቢያ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች፣ ከጎጥ ጤና መሪዎች፣ ሴቶች የጤና ልማት ቡድን አባላት እና ከሌሎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮች ጋር በጋራ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- ❖ ተጨባጭ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ መተንተን፣ በአግባቡ ማደራጀትና ለውሳኔ መጠቀም፤
- ❖ የቀበሌውን የክትባት ሽፋን መከታተያ ቻርት በየወቅቱ በአግባቡ መሙላትና ወቅታዊ ማድረግ፤
- ❖ ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ወቅቱን ጠብቆ በመርሐ ግብራቸው መሰረት የክትባት አገልግሎት እያገኙ መሆናቸውን መከታተል፤
- ❖ ፍሪጅ በትክክለኛው የሙቀት መጠን ወሰን (ከ +2 እስከ +8 ዲግሪ ሴንተ ግሬድ) ውስጥ መሆኑን መከታተልና የሙቀት መጠኑን በቀን ሁለት ጊዜ መመዝገብ፤
- ❖ ሁሉንም ለክትባት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በበቂ መጠን መኖራቸውን በየጊዜው መከታተል፤
- ❖ የክትባት መድኃኒቶች ለወር በቂ መሆናቸውን የክትባት ክምችት ምጣኔ (stock Balance) በመስራት፣ ጥቅም ላይ የዋለና የባከነ የክትባት መድኃኒት መጠንን በማስላት ከትክክለኛ መስፈርቱ ጋር በማነፃፀር መከታተል፤
- ❖ ለክትትሉ ዋና ዋና አመለካቾችን ወይም ጠቋሚዎችን በጤና መረጃ ስርዓት መሰረት ከሚሰበሰበት ውስጥ መምረጥና መከታተል፤
- ❖ የክትባት አገልግሎት ተጠቃሚዎችን አስተያየት በመጠየቅና የሚሰጡትን ግብረ መልስ ለስራ ማሻሻያ በግብዓትነት መጠቀም፤
- ❖ የተጠናቀረ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለውሳኔ መጠቀም።

3.5.2. የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም ግምገማ

- ❖ ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ተጠቃሚዎች ስለክትባቱ ያላቸውን እውቀት፤አመለካከትና ተግባር መዳሰስ፣
- ❖ የክትባት አገልግሎት አፈዓፀም ከዕቅድ አንፃር መፈተሽና አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣
- ❖ በየጊዜው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የክትባት አገልግሎት አሰጣጥን መገምገም ከህብረተሰቡ ግብረ መልስ መውሰድ፣
- ❖ በግምገማው ወቅት ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መለየት፣ ለወደፊቱ ዘላቂና ቀጣይ ለማድረግ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ የድርጊት መርሐ ግብር መንደፍና ከባለድርሻ አካላት ጋር ስራ ተከፋፍሎ መስራት።

3.5.3. በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸው በሽታዎች ቅኝትና ዳሰሳ ማካሄድ

በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸውን በሽታዎች ቅኝት በማድረግ መረጃን መሰብሰብ፤ መተንተን፤ መተርጎምና፣ መጠቀም እንዲሁም ለሚመለከተው አካል ለውሳኔና ለእርምጃ ማስተላለፍን ያጠቃልላል።

በክትባት የምንከላከላቸው በሽታዎች አልፎ አልፎ በወረርሽኝ መልክ ሲከሰቱ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በተለይም እንደ ኩፍኝ፤ ፖሊዮ፤ ትክትክ እና ማጅራት ገትር በሽታዎች ሲከሰቱ ይችላሉ።

ስለዚህም የበሽታዎች ቅኝትና ዳሰሳ ሲካሔድ፡-

- ❖ የበሽታዎች ቅኝትና ዳሰሳ መመሪያውን በአግባቡ መጠቀም፣
- ❖ በየመንደሩና በየጎጡ ያሉ የጎጥ የጤና መሪዎች፣ ልማት ቡድን አባላት እና ሌሎች አደረጃጀቶች ማንኛዉንም የበሽታ ክስተት ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- ❖ የበሽታዎች ጭምጭምታ (Rumor) ካለ በጭምጭምታ መመዝገብ መዝግቦ ማጣራት፣
- ❖ በሽታዉ ከተከሰተ የማህበረሰብ የበሽታ መግለጫ (community case definition) በመጠቀም መረጃዎችን መሰብሰብ፤ መተንተን፣መጠቀም፣ ግብረ-መልስ መስጠትና መቀበል እንዲሁም በአስቸኳይ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፣

3.6. አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

የክትባት አገልግሎት ለመስጠት በጤና ኬላ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች የሚከተሉት ናቸው።

3.6.1. መዛግብትና የሪፖርት ቅፃቅፆች

የቤተሰብ የጤና መረጃ መሰብሰቢያ፣ የክትባት መዝገብ፣ Tally Sheet፣ የTickler Box፣ የክትባት አፈጻጸም መከታተያ ቻርት፣ የክትባት ካርድ፣ ቻርት፣የክትባት መድኃኒት መጠየቂያ ቅጽ (Vaccine requisition form – VRF) ፣ የክትባት ሙቀት መመዝገቢያ መዝገብ (pad) ፣የክትባት ገቢና ወጪ መመዝገብያ መዝገብ፣ የሪፖርት መላኪያና መቀበያ ቅፆች እና ሌሎች መመዝገቢያ እና ሪፖሪት ማድረጊያ ቅጻቅጾች አስፈላጊ ስለሆኑ በተሟላ መልኩ አደራጅቶ መያዝ፡

3.6.2. የክትባት ትምህርትና የመግባቢያ መርጃ መሳሪያዎች

የቤተሰብ ጤና መመሪያ፣ የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም መመሪያ፤ የክትባት የጎንዮሽ ትግር መከታተያ መመሪያ (Adverse Event Following Immunization Guideline)፤ የክትባት ማኑዋሎች፣ የክትባት አገልግሎት ፓኬጅ፤ የተቀናጀ የክትባት ማሰልጠኛ ሞዱል/ EPI IRT module/፤ የኩፍኝ፣ የማጅራት ገትር፣ የፖሊዮና ሌሎች መመሪያዎች፣ የክትባት ፖስተሮች ፤ የክትባት ፍሊፕ ቻርቶች፤ በራሪ ወረቀቶች ወዘተ…

3.6.3. የቅዝቃዜ ሰንሰለት ለማስጠበቅ የሚረዱ ግብአቶች

- ❖ ፍሪጆች (Refridgerators)
- ❖ Cold box
- ❖ Vaccine Carrier
- ❖ Ice-packs
- ❖ Foam Pad
- ❖ Thermometer
- ❖ Fridge Tag

3.6.4. የክትባት መድኃኒቶች እና ሌሎች ቁሳቁሶች

- ❖ በአፍ የሚሰጥ የፖሊዮ ክትባት እና Dropper
- ❖ የኩፍኝ ክትባት፣መበጥበጫ፣ የክትባትና የመበጥበጫ Syringe
- ❖ BCG ክትባት፤መበጥበጫ፣ የክትባትና የመበጥበጫ ስሪንጅ
- ❖ Pentavalent ክትባት እና AD Syringe PCV ክትባት እና AD Syringe፣
- ❖ የማህፀን በር ካንሰር መከላከያ ክትባትና AD Syringe

- Rota ክትባት
- Td ክትባት እና AD Syringe
- በመርፌ የሚሰጠው የፖሊዮ ክትባት እና AD Syringe
- የኮቪድ 19 ክትባት እና AD Syringe
- Adrenaline እና Syringe
- Safety Box
- ጥጥ
- አልኮሆል፣ በረኪና
- የክትባት እቃዎች መያዣ ቦርሳ
- ሚዛን
- ጠረጴዛ እና ወንበር
- ወዘተ

3.6.5. የእጅ መታጠቢያ ግብዓቶች

- ውሃ
- Sanitizer
- ሣሙና
- ፎጣ

3.7. ከክትባት አገልግሎቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በክትባት በምንከላከላቸው በሽታዎች እና በክትባት ጠቀሜታ ዙሪያ የህብረተሰቡ ግንዛቤ፤ተሳትፎና ባለቤትነት ያድጋል፣
- ሁሉም ህጻናትና ሁሉንም ክትባት መዉሰድ የሚጠበቅባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የክትባት አገልግሎት ተደራሽነት፣ ተጠቃሚነት፣ ፍትሐዊነት እና ጥራት ይሻሻላል፤
- በክትባት የምንከላከላቸው በሽታዎች ሲከሰቱ የሚችሉትን ህመም፣ የአካል ጉዳት እና ሞትን ይቀነሳል
- የልጅነት ልምሻ በሽታ ይወገዳል (Eradication)፤
- የኩፍኝ፣የማጅራት ገትርና የአናቶችና የጨቅላ ህፃናት መንጋጋ ቆልፍ በሽታዎች ይጠፋሉ (Elimination)።

3.8. የአገልግሎቱ ዋና ዋና ጠቋሚዎች

- በቀበሌው ከሚገኙ ከአንድ ዓመት በታች ህፃናት የፔንታ 1፣ በአፍ የሚሰጥ ፖሊዮ 1፣ ፒሲቪ 1፣ ሮታ 1 ክትባት የወሰዱ ሽፋን
- በቀበሌው ከሚገኙ ከአንድ ዓመት በታች ህፃናት የፔንታ 3፣ፖሊዮ 3፣ በመርፌ የሚሰጥ ፖሊዮ፣ ፒሲቪ 3 ክትባት የወሰዱ ሽፋን፣
- በቀበሌው ከሚገኙ ከአንድ ዓመት በታች ህፃናት የመጀመሪውን የኩፍኝ ዶዝ የወሰዱ ሽፋን፣
- በቀበሌው ከሚገኙ ከአንድ ዓመት በታች ህፃናት ሁሉንም የክትባት ዓይነቶች ወስደው የጨረሱ፣
- በቀበሌው ከሚገኙ ከሁለት ዓመት በታች ህፃናት ሁለተኛዉን የኩፍኝ ክትባት የወሰዱ፣
- በቀበሌው ክትባት ጀምረው ያቋረጡ ህጻናት እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች
- በጤና ኬላው የክትባት ብክነት መጠን፣
- በቀበሌው ምንም ክትባት ያልወሰዱ ህጻናት፣
- የሚላኩ ሪፖርቶች ወቅታዊነትና ሙሉነት፣

አባሪዎች

አባሪ-1 የመደበኛ ክትባት አሰጣጥ መርሃ ግብር

ተ.ቁ	የክትባት ዓይነቶች	ክትባቱ የሚሰጥበት ዕድሜ	የክትባቱ አሰጣጥ/Injection Site & Route of Administration
1	ህጻን እንደተወለደ የሚሰጥ የሄፒታይተስ ቢ ክትባት (HepB Vaccine Birth dose)	ይህ ክትባት ህጻኑ እንደ ተወለደ ወይም ተወልዶ በ 24 ሰዓት ዉስጥ ይሰጣል።ህጻኑ የተወለደዉ ከጤና ተቋም ዉጭ/ በቤት ዉስጥ የተወለዳ ከሆነ ክትባቱን እስከ 14 ቀን ድረስ ይከተባል።	በግራ እግር የዉጭኛዉ ታፋ 90 ድግሪ / IM, left anterolateral Thigh /
2	በሰጂ ክትባት (BCG)	ይህ ክትባት ህጻኑ እንደ ተወለደ ይሰጣል	በቀኝ እጅ ክንድ ላዩ በቆዳ ስር/ Intradermal(ID) right deltoid/
3	የሳምባ ምች መከላከያ ክትባት/ Pneumococcal Conjugate Vaccine-PCV/	ይህ ክትባት በ6,10 እና 14ኛዉ ሳምንት ላዩ ይሰጣል	በቀኝ እግር ዉጭኛዉ ታፋ ላዩ 90 ድግሪ /Intramascular (IM), Right anterolateral thigh/
4	የልጅነት ልምሻ/ፖሊዮ/ መከላከያ ክትባት /OPV/	ይህ ክትባት የመጀመሪያዉ ዶዝ (OPV0) ህጻኑ እንደ ተወለደ ይሰጣል የዚህ ክትባት ቀጣዩ ዶዞች (OPV1፣2፣3) በ6,10 እና 14ኛዉ ሳምንት ላዩ ይሰጣል	ሁለት ጠብታ በአፍ የሚሰጥ /Oral drops/
5	በመርፌ የሚሰጥ የልጅነት ልምሻ መከላከያ ክትባት /IPV/	ይህ ክትባት አንደኛዉ ዶዝ በ14ኛዉ ሳምንት እና ሁለተኛዉ ዶዝ በ9ነኛዉ ወር ላዩ ይሰጣል	በቀኝ እግር ዉጭኛዉ ታፋ ላዩ 90 ድግሪ የሳምባ ምች ክትባት ከተሰጠበት ቦታ ላዩ 2.5 ሴ.ሜትር ዘቅ ብሎ ይሰጣል/ IM, Right anterolateral thigh 2.5 cm apart from the injection site of PCV/
6	ፔንታ ቫለንት /DPT-Hib-HepB/	ይህ ክትባት በ6,10 እና 14ኛዉ ሳምንት ላዩ ይሰጣል	በግራ እግር ዉጭኛዉ ታፋ ላዩ 90 ድግሪ / IM, Left anterolateral thigh /
7	የኩፍኝ መከላከያ ክትባት/ Measles Containing Vaccine-MCV/	ይህ ክተባትየመጀመሪያዉ ዶዝ በ9 ወር እና የሁለተኛዉ ዶዝ 15ኛዉ ወር ላዩ ይሰጣል	በግራ እጅ ክንድ ላዩ 45 ድግሪ / Subcutaneous (SC),Left deltoid/
8	ሮታ ክትባት/Rota virus vaccine/	ይህ ክትባትየመጀመሪያዉ ዶዝ በ6ኛዉ ሳምንት እና ሁለተኛዉ ዶዝ 10ኛዉ ሳምንት ላዩ ይሰጣል	በአፍ የሚሰጥ
9	የማህጸን በር ጫፍ ካንሰር መከላከያ ክትባት/Human Papilloma Virus Vaccine-HPV	ይህ ክትባት ዕድሜቻዉ14 ዓመት የሞላቸዉ ልጃገረዶች የሚሰጥ ሆኖ ሁለተኛዉ ዶዝ የመጀመሪያዉን ከወሰዱ ከ6 ወር በኋላ ይሰጣል /First dose at first conctact for 14 years old girls and 2nd dose after 6 months of 1st dose/	IM, Left Deltoid muscle of upper arm
10	የመንጋጋ ቆልፍና ዘጊ እናዳ በሽታ መከላከያ ክትባት/Td/		በግራ ክንድ ላዩ 90 ድግሪ /IM, right deltoid Muscle/

አባሪ-2 የኩፍኝ መከላከያ ክትባት አሰጣጥ መርሃ ግብር

የህጻኑ ዕድሜ	የመጀመሪያዉ ዶዝ/ MCV 1/	የሁለተኛዉ ዶዝ /MCV 2/	ምርመራ
9-11 ወር ምንም ያልወሰደ ከሆነ	MCV1 ይወስዳል	አይወስድም	እናት የህጻኑ እድሜ15 ወራት ሲሞላ ተመልሳ ሁለተኛዉን የኩፍኝ ክትባት እንድት ወስድመምከር/ Advise the mother to return at 15 Months for MCV2
የህጻኑ እድሜ ከ12-14 ወር ሆኖ የመጀመሪያዉ ዶዝ/MCV1/ ወስዶ ከሆነ	አይወስድም	የህጻኑ እድሜ 15 ወር ከሞላ እንዲመመጣ ይቀጠራል	እናት የህጻኑ እድሜ 15 ወራት ሲሞላ ተመልሳ ሁለተኛዉን የኩፍኝ ክትባት እንድታስከትብ መምከር/Advise mother to return when child is 15-month-old
የህጻኑ እድሜ ከ12-14 ወር ሆኖ የመጀመሪያዉ ዶዝ /MCV1/ ያልወሰደ ከሆነ	የመጀመሪያዉን ዶዝ/ MCV1/ በመጣበት ዕለት ይሰጠዋል	የሁለተኛዉን ዉን ዶዝ/MCV2/ አድሜዉ 15 ወር ስሞላ ይሰጠዋል	የመጀመሪያዉን ዶዝ/MCV1/ በመስጠት እና ለሁለተኛዉ ዶዝ የህጻኑ እድሜ 15 ወር ሲሞላ እንዲከተብ መምከር/Give MCV1 and advise mother to return for MCV2 at 15 months
የህጻኑ እድሜ ከ15-23 ወር ሆኖ የመጀመሪያዉ ዶዝ /MCV1/ ያልወሰደ ከሆነ	የመጀመሪያዉን ዶዝ/ MCV1/ በመጣበት ዕለት ይሰጠዋል	የሁለተኛዉን ዉን ዶዝ/MCV2/ የሚወስደዉ የመጀመሪያዉን ዶዝ/MCV1/ ከወሰዳ በሄንስ ከአንድ ወር በኋላ ይየሆናል	የመጀመሪያዉን ዶዝ/MCV1/ በወሰደበት በ1 ወር ጊዜ ዉስጥ ሁለተኛዉን ዶዝ እንዲከተብ መምከር /Give MCV1 and record as MCV1 and advise mother to return in 1-month time for MCV2
የህጻኑ እድሜ ከ15-23 ወር ሆኖ የመጀመሪያዉ ዶዝ /MCV1/ ወስዶ ሁለተኛዉን ዶዝ/MCV2/ ያልወሰደ ከሆነ	አይወስድም	የሁለተኛዉን ዉን ዶዝ/MCV2/ የሚወስደዉ የመጀመሪያዉን ዶዝ/MCV1/ ከወሰዳ በሄንስ አንድ ወር መሙላቱ ከተረጋገጠ በኋላ ወይም የመጣበት እለት ይሰጣል	የሁለተኛዉን ዉን ዶዝ/MCV2/ መስጠት/ Give MCV2 and record as MCV2

አባሪ-3 የቲዲ ክትባት አሰጣጥ መርሃ ግብር

Dose	Schedule	በሽታ የመከላከል ደረጃ
የመጀመሪያ ዶዝ /Td- 1/	ለመጀመሪያ ጊዜ እንደመጡ ወይም የመጀመሪያ የእርግዝና ወራት	የለዉም
የሁለተና ዶዝ/Td-2/	የመጀመሪያ ዶዝ /Td- 1/ከተወሰደ በሄንስ ከ4 ሳምንት በኋላ	ከ1-3 ዓመት
የሶስተኛ ዶዝ/Td-3/	የሁለተኛ ዶዝ/Td-2/ ከተወሰደ በሄንስ ከ6 ወር በኋላ	5 ዓመት
የአራተኛ ዶዝ/Td-4/	የሶስተኛ ዶዝ/Td-3/ ከተወሰደ በሄንስ ከ1ዓመት በኋላ	10 ዓመት
የአምስተኛ ዶዝ/Td-5/	የአራተኛዉ ዶዝ/Td-4/ ከተወሰደ በሄንስ ከ1ዓመት በኋላ	ሙሉዉን የልጅ መመለጃ እድሜ ደረስ/All child bearing years/

አባሪ-4 የክትባት አገልግሎትን ዘግይቶ የጀመሩ ህጻናት ለመከተብ የወጣ መርሃ ግብር

መድኀኒት ዓይነት	ዶዝ ብዛት	የመጀመሪያዉን ዶዝ ለመዉሰድ ትንሹ የእድሜ ገደብ / Minimum age for dose1	በዶዞች መካከል ያለዉ ዝቅተኛ የጊዜ ገደብ /Minimum interval between doses	ክትባቱን ለመዉሰድ የላይኛዉ የእድሜ ገደብ/Upper age limit/
BCG	1	አንደ ተወለደ	የለዉም	እስከ 1 ዓመት
OPV	4	አንደ ተወለደ	OPV0-OPV1 መካከል 6 ሳምንት ሲሆን በቀጣዮቹ ዶዞች 4 ሳምንት	OPV0- ህጻኑ ተወልዶ እስከ 2 ሳምንት ድረስ ይሰጣል ሌሎቹ ቀጣዩ ዶዞች እስካ 59 ወር
Rota	2	6ኛዉ ሳምንት	4 ሳምንት	እስካ 24 ወር
PCV	3	6ኛዉ ሳምንት	4 ሳምንት	እስካ 24 ወር
Pentavalent	3	6ኛዉ ሳምንት	4 ሳምንት	እስካ 24 ወር
IPV	2	14 ኛዉ ሳምንት	ሁለተኛዉ ዶዝ በ9ኛዉ ወር፣ የመጀመሪያዉን ዶዝ ዘግዩቶ ከወሰደ፣ በመጀመሪያዉና በሁለተኛዉ ዶዝ መካከል ቢያንስ 4 ሳምንት መኖር አለበት	እስካ 24 ወር
Measles	2	9ኛዉ ወር	ሁለተኛዉ ዶዝ በ15ኛዉ ወር፣ የመጀመሪያዉን ዶዝ ዘግዩቶ ከወሰደ፣ በመጀመሪያዉና በሁለተኛዉ ዶዝ መካከል ቢያንስ 4 ሳምንት መኖር አለበት	እስካ 59 ወር

ምዕራፍ 4
የእናቶች ጤና አገልግሎት

4

4.1. በመሰረታዊና አጠቃላይ ጤና ኬላዎች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

ተግባራት	መሰረታዊ ጤና ኬላ	አጠቃላይ ጤና ኬላ
1. ለእናቶችና ጨቅላ ህጻናት የጤና አገልግሎት ለመስጠት የቀበሌውን ሁኔታ ያገናዘበ ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈጸም	√	√
2. የማህበረሰብ ንቅናቄ ማካሄድ	√	√
3. የሚሰጡ አገልግሎቶች		
3.1 **የቅድመ እርግዝና አገልግሎት**		
3.1.1 የቅድመ እርግዝና የምክክር አገልግሎት	√	√
3.1.2 የቅድመ እርግዝና አገልግሎት ለሚፈልጉ ሪፈር ማድረግ	√	√
3.2 የቅድመወሊድ አገልግሎት		
3.2.1.የቅድመወሊድ አገልግሎት ከ12 ሳምንት በፊት ማስጀመር	√	√
3.2.2. ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድና ከወሊድ ጋር በተያዘ ሲከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮችን አስቀድሞ ለእናትና ለቤተሰብ ማስገንዘብ	√	√
3.2.3. የቅድመወሊድ አገልግሎት 2ተኛ፣ 3ተኛ፣ 5ተኛ እና 7ተኛ መስጠት	√	√
3.2.4. የቅድመወሊድ አገልግሎት 1ኛ፣4ተኛ እና 8ተኛ መስጠት	X	√
3.2.5 የነፍሰጡር እናቶች ኮንፍረንስ ማካሄድ	√	√
3.2.6 በእርግዝና ወቅት ሲከሰቱ የሚችሉ ዋና ዋና አደገኛ ምልክቶች ማሳወቅ	√	√
3.2.7 የነፍሰጡር እናቶች ማቆያ ቤት እንዲጠቀሙ ማድረግ	√	√
3.2.8. በጤና ተቋም እንዲወልዱ የምክክር አገልግሎት መስጠት	√	√
3.2.9. በድህረ ወሊድ ክብካቤ ላይ ምክክር ማድረግ	√	√
3.2.10.የድህረ ወሊድ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ላይ ምክክር ማድረግ	√	√
3.2.11. ጡት ማጥባት ላይ የምክክር አገልግሎት መስጠት	√	√
3.3 **የወሊድ አገልግሎት**		
3.3.1 በምጥ ጊዜ የሚደረግ ህክምናና የአምቡላንስ አገልግሎት	√	√
3.3.2 መሰረታዊ የድንገተኛ የምጥና የጨቅላ ሕፃናት ክብካቤ መስጠት	X	√
3.3.3 የ3ኛ ደረጃ ምጥ/Active 3rd stage labor/ አገልግሎት መስጠት	X	√
3.3.4 ለተወሳሰበ ምጥ የቅድመ ሪፈራል ህክምና አገልግሎት መስጠት	√	√
3.4 **የድህረ ወሊድ ክትትልና ክብካቤ**	√	√
3.4.1 ለእናቶችና ጨቅላ ህዓናት በጤና ተቋም የድህረ ወሊድ አገልግሎት መስጠት	X	√
3.4.2 ለእናቶችና ለጨቅላ ህዓናት የቤት ለቤት የድህረ ወሊድ ጉብኝት አገልግሎት መስጠት	√	√
3.4.3 እናትየዋ መመረዝ (Infection) ካለት ማከም	X	√
3.4.4 እናትየዋ የጡት መመረዝ (Mastitis) ካለት ማከም	√	√
3.4.5 ድህረወሊድ ላይ የሚከሰት ከፍተኛ የደም መፍሰስ ማከም	X	√
3.4.6 ድህረወሊድ ላይ የሚከሰት ከፍተኛ የደም መፍሰስ ቅድመ-ሪፈራል ህክምና	X	√
3.5 ደህንነቱን የጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት		

3.5.1 ደህንነቱን የጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት መስጠት	X	√
1.6 **ቅኝትና ምላሽ**		
3.6.1 የእናቶችና የጨቅላ ሕጻናት ሞት ቅኝትና ምላሽ	√	√
3.6.2 ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላ እንዳይከሰት መከላከል	√	√
3.6.3 ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላና የማህፀን መውጣት ልየታና (identification) ሪፈራል	√	√
3.6.4 ከወሊድ ጋር የተያያዘ የማህፀን መውጣት ምርመራና (diagnosis) ሪፈራል	X	√

4.1.1. ለእናቶችና ጨቅላ ህጻናት የጤና አገልግሎት ለመስጠት የቀበሌውን ሁኔታ ያገናዘበ ዕቅድ ማዘጋጀትና መፈጸም

- ❖ በማህበረሰብ ደረጃ የእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎትን በተመለከተ ለማቀድና አፈጻፀሙን ለመከታተል የሚረዱ መረጃዎችን እንደ በመውለድ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሴቶች፣ ነፍሰጡር ሴቶች፣ የወለዱ እናቶችና የመሳሰሉትን ማሰባሰብ፤ ማደራጀትና መተንተን እንዲሁም በየጊዜው ማስተካከል፤
- ❖ የግብዓት አቅርቦት መረጃ ማሠባሠብና መተንተን፤ ውጤቱንም ለዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት መጠቀም፤
- ❖ በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በቀበሌው ያሉ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ፣
- ❖ የመረጃ ትንተና ውጤትን መሠረት በማድረግ ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- ❖ ዕቅዱን መፈፀም፤ አፈጻፀሙን መከታተልና መገምገም፤

4.1.2. በቅድመ-እርግዝና፣ በቅድመ ወሊድ፣ ወሊድ፣ ድህረ ወሊድና የጨቅላ ህፃናት ጤናን ለማሻሻል የባህሪ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ትምህርት መስጠት

4.1.2.1. ከጎጥ ጤና መሪዎች፣ ሴቶች ልማት ቡድንና ከሌሎች የማህበረሰብ ተሳትፎ አደረጃጀቶች ጋር አብሮ መስራት

- ❖ በቅድመ-እርግዝና፣ ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድ፣ ድህረ ወሊድና የጨቅላ ህፃናት ጤና ክብካቤ ላይ የልማት ቡድን መሪዎችን ማሰልጠን፣
- ❖ የጎጥ ጤና መሪዎችና የልማት ቡድን መሪዎች በሰለጠኑት መሠረት በስራቸው የሚገኙ ነፍሰጡር እናቶችንና ቤተሰቦቻቸውን (ባል፣ አማቶች፣ ልጆች፣ ወንድም፣እህት፣ አያቶች) እንዳለዩና እንዳያስተምሩ ማድረግ፣
- ❖ የጎጥ ጤና መሪዎችና የልማት ቡድን መሪዎች ሁሉም ነፍሰ ጡር እናቶች ከ3 ወር በፊት የቅድመ ወሊድ ክትትል እንዲጀምሩ ህብረተሰቡን ማሳወቅ
- ❖ የተለዩትን ነፍሰጡር እናቶች የቅድመ ወሊድ፣ ወሊድ፣ ድህረ ወሊድና የጨቅላ ህፃናት ክብካቤ አገልግሎት እንዲያገኙ ወደ ጤና ድርጅት መሄዳቸውን መከታተል፣
- ❖ ሁሉም ነፍሰ ጡር እናቶች በጤና ተቋም እንዲወልዱ እንዲሁም በጤና ተቋም መውለድ ለእናቶችና ለጨቅላ ህፃን ያለውን ጠቀሜታ መስተማር
- ❖ ሁሉም የወለዱ እናቶች 24 ሰዓት በጤና ተቋም መቆየትና ክብካቤ ማግኘት እንዳለባቸው መረጃ መስጠት

❖ ቤታቸው ከጤና ተቋም ሩቅና የጤና ችግር ያለባቸው ነፍሰጡር እናቶች የመውለጃ ጊዜያቸው ሲቃረብ (38 ሳምንት) የእናቶች መቆያ ቤቶችን እንዲጠቀሙ ማስተማር

4.1.2.2. የነፍሰጡር እናቶች ኮንፍረንስ ማካሄድ

❖ ኮንፈረንስ የሚካሄድበትን ቦታና ጊዜ መለየት/መወሰን

❖ በጎጥ ጤና መሪዎችና በልማት ቡድን መሪዎች አማካይነት ተለይተው የተመዘገቡ ነፍሰጡር እናቶችና ቤሎች የሚመለከታቸውን አካላት ለኮንፈረንሱ መጋበዝ

❖ በየኮንፈረንሱ ቀናት ውይይት የሚደረግበት ነጥብ ላይ በደንብ መዘጋጀትና አጋዥ የሆኑ መመሪያዎችን/መፅሐፍቶችን መጠቀም (ለምሳሌ፡ የቤተሰብ ጤና መመሪያ)

❖ የነፍሰጡር እናቶች ኮንፈረንስ ለማካሄድ በተዘጋጀዉ ሰነድ መሰረት ስለ እርግዝና ምልክቶች፣ ስለ ቅድመ ወሊድ ክትትል፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ የወሊድ ዝግጅት፣ ከእርግዝና ጋር ተያይዞ ስለሚከሰቱ አደገኛ ምልክቶች፣ የተመጣጠነ ምግብ አዘገጃጀት፣ በእርግዝና ጊዜ ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ፣አለባበስ፣እረፍትና መዝናናት፣ ለጨቅላ ህፃናት ስለሚደረግ ክብካቤ፣ የእናት ጡት ወተት ጥቅም፣ በቅድመ ወሊድ ወቅት የሚሰጡ መድሃኒቶችና ክትባት (አይረን ፎሌት፣ ፎሊክ አሲድ፣ ቲቲ ክትባት) እንዲሁም እናቶች የቅድመ-እርግዝና አገልግሎትና በመሳሰሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለነፍሰጡር እናቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፣

❖ የአባለዘር በሽታ ኤች አይ ቪን ጨምሮ ከእርግዝና በፊት እንዲሁም በእርግዝና ወቅት ምርመራ የማድረግ አስፈላጊነትን እንዲሁም ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ጽንስ/ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል ወይም ጠርሶ ማስቆም ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት

4.1.2.3. ለሃይማኖት መሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት

❖ ነፍሰጡር እናቶች ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ የቅድመ ወሊድ እና ቤሎች የጤና አገልግሎቶችን እንዳይጠቀሙ የሚያደርጉ ጉዳዮችን መለየት፣

❖ በቀበሌው ውስጥ ለሚገኙ የተለያዩ የሃይማኖት አባቶች/መሪዎች በእናቶችና ጨቅላ ህፃናት ጤና አገልግሎቶች ዙሪያ ለማወያየት የሚጠቅሙ ነጥቦችን በማዘጋጀት በማወያየት ትምህርት መስጠትና የቅስቀሳ ስራዎችን መስራት፤

❖ የሃይማኖት አባቶች/መሪዎች ከውይይቱ በኋላ ምን ምን ስራዎችን እንደሚሰሩ ለይተው እንዲያቅዱ በማድረግ ተግባራዊነቱንም በመከታተል ግብረ መልስ መስጠት፣

4.2. ቅድመ ወሊድ አገልግሎት መስጠት

❖ የጤና ኬላ ባለሙያዎች ምንም ዓይነት የጤና ችግር ለሌለባት ነፍሰጡር እናት የቅድመ ወሊድ አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ የሚከተሉትን ስምንት ኮንታክት መርሃ ግብሮች መሰረት በማድረግ ይሆናል፡-

ኮንታክት	የእርግዝናው እድሜ በሳምንት	የቀጠሮ ጊዜ
የመጀመሪያ	ከ12 ሳምንታት በፊት (3 ወር)	ከ8 ሳምንት በኋላ
ሁለተኛ	20 ሳምንት	ከ6 ሳምንት በኋላ
ሦስተኛ	26 ሳምንት	ከ4 ሳምንት በኋላ
አራተኛ	30 ሳምንት	ከ4 ሳምንት በኋላ
አምስተኛ	34 ሳምንት	ከ4 ሳምንት በኋላ
ስድስተኛ	36 ሳምንት	ከ2 ሳምንት በኋላ
ሰባተኛ	38 ሳምንት	ከ2 ሳምንት በኋላ
ስምንተኛ	40 ሳምንት	

4.2.1. በመጀመሪያ የቅድመ-መወሊድ ኮንታክት/ጉብኝት የሚከናወኑ ተግባራትና የሚሰጡ አገልግሎቶች

❖ አስፈላጊ መረጃዎችን መሙላት

- ✓ የመጨረሻ የወር አበባ ያየችበትን ቀን
- ✓ ከዚህ በፊት ስንት ጊዜ እርግዝናና ወሊድ እንደነበረ
- ✓ በባለፉት እርግዝናዎች እና ወሊድ ወቅት ችግር አጋጥሟት ከነበረ፣ የከፍተኛ ህክምና አገልግሎት (previous obstetric complications, Cesarean section) ተደርጎላት ከሆነ

❖ የመሰረታዊ የሰውነት ጤና ጠቋሚ ምርመራ (vital signs)፣ ክብደትና ቁመት መለካትና መመዝገብ

❖ ሙሉ የአካል ምርመራ (physical examination) ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ በተለይም የአይንን እና መዳፍ አለመገርጣቱን ማጣራት፣የእንቅርት፣ጡት ላይ ያበጠ ነገር መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ

❖ መሰረታዊ የላቦራቶሪ ምርመራ (RPR, Blood group and Rh, HepatitisB (HBsAg), Heamoglobin, UA & microscopy HCG) አገልግሎቶችን መስራት

❖ የስኳር፣ የተቢ እንዲሁም የGroup B streptococcus ልየታና ምርመራ

❖ የኤች አይ ቪ ምርመራና የምክር አገልግሎት በግል ወይም በጥንድ መስጠት

❖ የመንጋጋ ቆልፍ መከላከያ ክትባት (TD) መስጠት

❖ የብረት እንክብል በየቀኑ አንድ ፍሬ ለስድስት ወር በተከታታይ እንዲወስዱ ያደርጋሉ

የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ስለ ጡት ማጥባት፣ የግል ንጽህና፣ የመኝታ አጎበር አጠቃቀም፣ የእርግዝና ጊዜ አደገኛ ምልክቶች፣ ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍን፣ የወሊድ ቅድመ ዝግጅት፣ በጤና ተቋም እንዲወለዱ የምክክር አገልግሎት መስጠትና የድህረ ወሊድ የቤተሰብ ዕቀድ አገልግሎት ላይ ምክክር ማድረግ በተመለከተ ያስተምራሉ፤

❖ በአቅራቢያቸው ወደ ሚገኘው ጤና ጣቢያ በመሄድ ተጨማሪ እንክብካቤ እንዳያገኙ ማበረታታት

❖ አደገኛ ምልክቶች መኖር አለመኖሩን ማጣራትና ከምልክቶቹ አንዱ እንኳን ካለት ወዲያውኑ ወደ ከፍተኛ ህክምና ተቋም መላክ

<u>አደገኛ ምልክቶች</u>

✓ ከማህጸን ደም መፍሰስ

✓ በታችኛው የሆድ ክፍል ላይ የሚሰማ ከባድ ህመም

✓ ትኩሳት፣ራስ ምታት፣ ማዞር ፣ ወይም ብዥ ያለ እይታ

✓ መንዘፍዘፍ ወይም ራስን መሳት

✓ የእጅችና የፊት እብጠት ካለ በአፋጣኝ ወደ አቅራቢያ ጤና ተቋም ሪፈር ማድረግ፤

4.2.2. በሁለተኛው ኮንታክት የሚከናወኑ ተግባራት

❖ በመጀመሪያው ኮንታክት የነበሩ የእናትየዋን ሙሉ የአካል ምርመራ፣ ታሪክና የላብራቶሪ ውጤቶችን መገምገም

❖ ስለ ፅንሱ እንቅስቃሴ መጠየቅ

❖ የእናቲቱ የጤና ሁኔታ መጠየቅ

❖ የእርግዝና እድሜውን (gestational age) ማስላት

❖ የእናትየዋን አጠቃላዩ ገጽታ (general appearance) መመልከት

❖ የእናትየዋን ክብደት መለካትና መጨመሩን መከታተል

❖ የአይንን እና መዳፍ አለመገርጣቱን ማጣራት

❖ MUAC በመጠቀም ለከፍተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ምርመራ ማድረግ

❖ የማህፀን ቁመት መለካት

❖ የፅንሱን የልብ ምት ያዳምጡ

❖ ለአልትራሳውንድ ስካን መላክ/ማሰራት

❖ የብረት እንክብል (Iron folate) መውሰዷን መከታተልና እንደትቀጥል ማድረግ፣

❖ የአንጀት ጥገኛ ትላትል ህክምና

❖ ሴሎች በቅድመ ወሊድ ጊዜ ሲከሰቱ የሚችሉ አደገኛ ምልክቶችን አለመኖራቸውን ያረጋግጡ

- ስለአመጋገብና ሌሎች በእርግዝና ጊዜ መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች በተመለከተ ምክር መስጠት
- የአእምሮ ጤና እና የቅርብ አጋር ጥቃትን መገምገም

4.2.3. በሶስተኛው ኮንታክት የሚከናወኑ ተግባራት

- በሁለተኛው ኮንታክት የተሰሩ ሁሉንም ተግባራቶችን፣ ከአልትራሳውንድ ምርመራ በስተቀር፣ መስራት
- የሽንት ምርመራ ማድረግ proteinuria and urine gramstain
- በእርግዝና ጊዜ የሚከሰት የስኳር ህመምን መመርመር

4.2.4. በአራተኛው ኮንታክት የሚከናወኑ ተግባራት

- በሶስተኛው ኮንታክት የተሰሩ ሁሉንም ተግባራቶችን መስራት
- ኤች አይ ቪ እና የቂጥኝ ምርመራን በድጋሚ መስራት
- የፅንሱን ደህንነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ምርመራዎችን ማድረግ
- በእርግዝና ጊዜ ሲከሰቱ የሚችሉ አደገኛ ምልክቶችን እንዲሁም የወሊድ ዝግጅት በተመለከተ የምክክር አገልግሎት
- ጡት ማጥባትን በተመለከተ የምክክር አገልግሎት

4.2.5. በአምስተኛው ኮንታክት የሚከናወኑ ተግባራት

- በአራተኛው ኮንታክት የተሰሩ ሁሉንም ተግባራቶችን መስራት
- በ30 ሳምንት ላይ የተሰራውን የኤች አይ ቪ እና የቂጥኝ ምርመራን በድጋሚ መስራት
- የፅንሱን አቀማመጥ ማረጋገጥ
- አስጊ የጤና ችግር ላለባቸው እናቶች የሽንት ምርመራ ማድረግ
- ጡት ማጥባትን እንዲሁም ክትባትን በተመለከተ የምክክር አገልግሎት
- ቀዳማዩ የልጅነት እድገትና መዳበር ላይ የምክክር አገልግሎት

4.2.6. በስድስተኛው ኮንታክት የሚከናወኑ ተግባራት

- በ 34 ሳምንት ላይ የተሰሩትን ሁሉንም ተግባራት መድገም
- ስነ-አዕምሮ ጤና መመርመር

4.2.7. በሰባተኛው ኮንታክት የሚከናወኑ ተግባራት

- በ36 ሳምንት ላይ የተሰሩትን ሁሉንም ተግባራት መድገም
- ስለ ወሊድ ጊዜ ፍርሃት፤ ስጋት፤ እና እሱታን መጠየቅ/መመርመር
- የቀይ-ደም ሴል ምርመራ /Hb test/ መድገም
- ስለ ፅንሱ እንቅስቃሴ ነፍሰጡሯን መምከር

4.2.8. በስምንተኛው ኮንታክት የሚከናወኑ ተግባራት

- በ38 ሳምንት ላይ የተሰሩትን ሁሉንም ተግባራት መድገም
- ስለ ፅንሱ እንቅስቃሴ አቆጣጠር መጠየቅ እና ማስረዳት
- ስለ ፅንሱ ሁኔታ አልትራሳዉንድ ማሰራት

4.3. የማዋለድ አገልግሎትና የጨቅላ ህጻናት ክብካቤ

4.3.1. በምጥና በወሊድ ጊዜ የሚደረግ ክብካቤ

- የነፍሰ-ጡሯን ካርድ በጥንቃቄ ማየትና ስለነፍሰ-ጡሯ አጠቃላዩ የጤና ሁኔታ ግንዛቤ መያዝ
- ፓርቶግራፍ በመጠቀም የምጡን ሁኔታ መከታተል (የነፍሰጡሯን አጠቃላዩ መረጃ፡- ስም ፣የእርግዝና ቁጥር (gravida)፣ የወሊድ ቁጥር (para)፣ የቤተሰብ ማህደር ቁጥር ፣ የገባችበት ቀንና ሰዓት፣ እንሽርት ውሃ የፈሰሰበት ጊዜ የያዘ የመረጃ መሙያ ቅፅን በጥንቃቄ መሙላት
- ምጡን በተመለከተ ነፍሰጡሯን አስፈላጊውን ጥያቄ በመጠየቅ ቅፆችን መሙላት
- ሙሉ የአካል ምርመራ (physical examination) ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ ማድረግ
- መሰረታዊ የሰውነት ጤና ጠቋሚ ምርመራ (vital signs) በመለካትና መመዝገብ፣የጸንሱ አቀማመጥ ትክክለኛው (cephalic presentation) መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የጸንሱ አመጣጥ መቀመጫ መር (breech presentation) ከሆነ፣ቀኑ ሳይደርስ ከተወለደ (preterm Delivery) በአፋጣኝ በአቅራቢያ ወዳለ ከፍተኛ የጤና ተቋም ሪፈር ማድረግ፣
- የእንሽርት ውሃ ፈሶ ከሆነ አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት
- ከወሊድ ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮች/ አደገኛ ምልክቶችን ለይቶ ማስገንዘብ
- ከወሊድ ጋር በተያየዘ ሞት እንዳይከሰት ከፍተኛ ጥናቃቄ ማድረግ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ከፍተኛ የጤና ተቋም ሪፈር ማድረግ፣
- የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት መድኃኒቶችና መሳሪያዎችን በበቂ መጠንና ዓይነት ማዘጋጀት፣

❖ በምጥ ግዜ የነፍሰጡሯን የጤና ሁኔታ መከተታል፣ መመዝገብ

- ✓ የልብ ምት (PR)፣የሙቀት መጠን(Temperature)፣ደም ግፊት(BP)፣ የአስተንፋስ መጠን(RR) በጥናቃቄ መለካትና መመዝገብ
- ✓ የሽንት መጠን፣ የሽንት ውስጥ ኬቶን፣ የሽንት ውስጥ ፕሮቲን ምርመራ እንድታገኝ ማመቻቸት

4.3.2. የመጀመሪያ የምጥ ደረጃ (First Stage of labour)

- ✓ ሽንት እንደመጣ ወዲያውኑ መሽናት እንዳለባት ማስተማር
- ✓ ነፍሰጡሯ ለምትጠዩቃቸው ጥያቄዎች የፈለገችውን ያህል የጤና መረጃ መስጠት
- ✓ ለነፍሰጡሯ ምቾትና እምነት በሚያሳድር መልኩ የምጥና የወሊድ እንክብካቤ ማድረግ
- ✓ ተከታታዩ የሆነ የሚያስፈልጋትን ድጋፍና እርዳታ ሁሉ መስጠት
- ✓ በቅድመ ወሊድ ክትትል ወቅት የኤች አይ ቪ ምርመራ ያላደረገች ከሆነ የምክር አገልግሎት መስጠትና የኤች አይ ቪ ምርመራ ማድረግ፣
- ✓ የማህፀን በር ክፍተት መጠን (cervical dilatation) መለካት
- ✓ በምጥ ወቅት ፈሳሽ እንድትወስድ ማድረግ
- ✓ ተደጋጋሚ የብልት ምርመራን መቀነስ (reduce repeated **PV** examination)
- ✓ ምጥ መጀመሩን የሚያሳየው የማህፀን በር ክፍተት (cervical dilatation) ሲጀምር የሚወጣ ለሃጭ/ ንፍጥ መሰል ደም የቀላቀለ ፈሳሽን (show) እና ከወሊድ በፊት ሊከሰት የሚችል የደም መፍሰስ (**APH**= Ante partum Haemorrhage) መለየት፣
- ✓ ፓርቶግራፍ በመጠቀም የምጥ ሂደቱን መከተታል
- ✓ በማህፀን ውስጥ ያለው መሪ አካል መውረዱን መከተታል
- ✓ የማህፀን ጡንቻ መኮማተር (contraction) ጊዜና ድግግሞሽን ክትትል በማድረግ መመዝገብ
- ✓ የማህፀን ጡንቻ በሚኮማተርበት (contraction) ወቅት የአተነፋፈስ ስርዓትን መከተታል
- ✓ በየግማሽ ሰዓቱ የሽሉ/የጽንሱን የልብ ምትና ሌሎችንም በፓርቶግራፍ ላዩ መመዝገብ
- ✓ የእንሽርት ውሃ (Aminotic fluid) መፍሰስ አለመፍሰሱን መከተታል
- ✓ የእንሽርት ውሃን መልክ የብልት ምርመራ በሚደረግበት ወቅት መለየት
    - **I** - የእንሽርት ውሃ ካልፈሰሰ ወይም ሽፋኑ ካልተቀደደ (membrane Intact)
    - **C** - የእንሽርት ውሃ ሽፋኑ ከተቀደደ (membrane ruptured)
    - **M** - የልጅ ዓይነ ምድር ካለው (meconium stained)
    - **B** - ደም የተነከረ (Blood stained) በሚል ቀጹን መሙላት

✓ ሞልዲንግ (Molding)፣የሸሉ ጭንቅላት መገጣጠሚያ አጥንቶች መሀከል ክፍተት ሲኖር (Molding 0)፣የሸሉ ጭቅላት መገጣጠሚያ አጥንቶች ሲቀራረቡ (Molding +1)፣የሸሉ የጭንቅላት አጥንቶች በአነስተኛ ደረጃ ሲተባበሩ (Molding +2)፣የማይለቅ የሽል ጭንቅላት አጥንቶች ሲተባበሩ (Molding +3) መሆኑን መለየት

✓ ነፍሰጡሯ ወደታች የመግፋት ስሜት ሳይኖራትና የማህፀን በር በበቂ ሁኔታ ሳይከፈት እንዳትገፋ ማድረግ

✓ በየአራት ሰዓት የማህፀን በር መከፈቱን በጥንቃቄ መመርመርና በፓርቶግራፍ ላዩ የ"**X**" ምልክት በማስቀመጥ መከተታል፣

✓ በየግማሽ ሰዓቱ የማህጸን መኮማተር (contraction) ቁጥር በ**10 ደቂቃ ውስጥ** ስንት መኮማተር (contraction) እና ቆይታው ለምን ያህል ጊዜ እንደደሆነ በሴኮንድ መመዝገብ

✓ ከ20 ሴኮንድ በታች ከሆነ ፓርቶግራፍ ላዩ «  » በመጠቀም ምልክት ያደርጋሉ

✓ ከ20 – 40 ሰኮንድ የሚቆዩ የመኮማተር መጠን ካለት ዩሄን ምልክት « » ያደርጋሉ

✓ ከ40 ሰኮንድ በላዩ ከሆነ ዩሄን ምልክት « » ያደርጋሉ

✓ ተጨማሪ መድኃኒት መስጠት፤መመዝገብ

✓ በየ 2 ሰዓቱ የሰውነት ሙቀት በመለካት መመዝገብ

✓ በየ 30 ደቂቃው የፅንሱን የልብ ምት በመቁጠር ፣ ነጥብ የ« ● » ምልክት ፓርቶግራፍ ላዩ ምልክት ማድረግ።

✓ በየ4 ሰዓቱ የደም ግፊት በመለካት መመዝገብ

✓ ሽንት በሸናችበት ጊዜ የኘሮቲን እና የሽንት መጠን በማየት መመዝገብ

✓ ነፍሰጡሯን ለማዋለድና ጨቅላ ህጻኑን ለመቀበል ዝግጅት ታደርጋለች

❖ **ሁለተኛ የምጥ ደረጃ (Second Stage of labour)**

✓ በምጥ ግዜ ለመውለድ በሚረዳ አኳኋን (Position) በመጠቀም እንድትወልድ ድጋፍ ማድረግ

✓ ኢንፌክሽንን የመከላከል ልምዶችን በመከተል አገልግሎት መስጠት

✓ በምጥ ግዜ የእናት ወዳጅ ወይም ቤተሰብ ሲኖር በማዋለጃ ክፍል በማስገባት ወላጂን እንዲያበረታቱት ማድረግ

✓ ነፍሰጡሯ ወደታች እንድትገፋ ማበረታታት

✓ የብልት መቅደድ (episiotomy) በተቻለ መጠን ማስወገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ በጥንቃቄ መስራት

✓ የማዋለድ አገልግሎት ማከናወን

❖ **ሦስተኛ የምጥ ደረጃ /Third stage of labour/**

✓ ሁለተኛ ልጅ አለመኖሩን ማረጋገጥ

✓ ኦክሲቶሲን መስጠት

✓ የእንግዴ ልጁ ማህጸኗን ወደ ታች እንዳያወጣው የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን፡

- የእትብት ስበትን መቆጣጠር፣
- ማህፀን ወደ ቦታው እንዲመለስ ማህፀኗን ማሸት፣
- የእንግዴ ልጅ ሽፋኑን በደምብ ማየት (መመርመር)፣
- የብልት ቀዳዳና ፔሪኒየም አካባቢ ጉዳት ካለ ማረጋገጥ እና በጥንቃቄ መስፋት
- የእንግዴ ልጁን ማዋሰድ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ መውጣቱን ማረጋገጥ
- ከ1 ሰዓት በኃላ እናትየዋን ወደ ድህረ ወሊድ ክፍል መውሰድ

4.4. የጨቅላ ሕፃናት እንክብካቤ

4.4.1. በህብረተሰቡ ውስጥ የሚሰሩ ዝርዝር ተግባራት

❖ ጨቅላ ሕፃናትን የሚመለከቱ ተግባራትን እና መልዕክቶችን ማስተላለፍ

❖ ለጨቅላ ሕፃናት መደረግ የሚገባውን ተጨማሪ እክብካቤ ማስተማር

❖ የጨቅላ ሕፃናትን የጡት ማጥባት ባህርያት ማስተማር

❖ የጨቅላ ሕፃናትን አደገኛ የህመም ምልክቶችን እንዲለዩ ማድረግ

❖ በጨቅላ ሕፃናት ላይ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን (ለሕፃኑ ቅቤ ማዋጥ ወይም ዘይት መስጠት)፣ በአራስነቷ ጊዜ በጨለማ ቤት ውስጥ መተኛት፣ እንገር አለማጥባት እና ስኳር በመበጥበጥ ፈሳሽ ውሃ ለጨቅላ ሕፃናት መስጠትን እንዳያስወግዱ ማስተማር

❖ በቻርት ቡክሌቱ መሰረት የታመሙ ጨቅላ ሕጻናትን መለየት፣ማሳየትና፤ማከም

❖ ለእናትየዋ ስለ ቤት ውስጥ የጨቅላ ሕፃናት ሕክምና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ በቀጠሮ የሚመለሱበትን ጊዜ መንገር

❖ በተጨማሪም በማንኛውም ጊዜ በጨቅላ ሕፃናት ላይ የሕመም ምልክት ሲያዩ ወደ ጤና ኬላው እንዲያመጡ የምክር አገልግሎት መስጠት

4.4.2. ለሁሉም አዲስ ጨቅላ ሕፃናት አስፈላጊ ክብካቤ (Essential Newborn Care)

የጨቅላ ሕፃኑ ልክ ከማህፀን እንደወጣ የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል መፈጸም፡-

❖ ሕፃኑን እንደተወለደ በእናቱ ሆድ ላይ ማስቀመጥ

❖ ሕጻኑን በንፁህ ፎጣ ከጭንቅላት ጀምሮ ማድረቅና በሌላ ንፁህና ደረቅ ፎጣ ከጭንቅላቱ ጀምሮ ሰውነቱን መጠቅለል

❖ የሕፃኑን አተነፋፈስና ቀለሙን መመርመር

❖ እትብቱ ሳይቋጠር ለ3 ደቂቃ ማዘግየት ከዚያም እትብቱን ቋጥሮ በአግባቡ መቁረጥ

❖ ሕፃኑ ከእናቱ ጋር ገላ ለገላ እንዲነካካ (እንዲተቃቀፍ) ማድረግ

❖ እናትየዋ ወዲያውኑ ጡት ማጥባት እንድትጀምር ማድረግ

- ❖ በአንደኛው እና በአምስተኛው ደቂቃዎች (APGAR score) መለካት፤ውሳኔ መስጠት (need of further Treatment)
- ❖ ለጨቅላው ህፃን በሁለቱም ዓይኑ 1% ቴትራ ሳይክሊን የዓይን ቅባት (TTC 1% eye ointment) መቀባት፣
- ❖ በጨቅላ ህፃኑ እትብት ላይ ክሎርሄክሲዲን (Chloerhexidine) በቀን አንድ ጊዜ ለ7 ቀን በተከታታይ እንደትቀባ ማስተማርና ማሳየት
- ❖ ጭኑ መሃል ላይ (በፊት ለፊት በኩል) 1ሚ.ግ ቫይታሚን ኬ (1mg Vitamin K injection) መስጠት
- ❖ ክብደቱን፣ቁመቱንና የጭንቅላቱን ዙሪያ (head circumference) መለካት
- ❖ ውጤቱን መመዝገብ እና ሪፖርት ፎርም ላይ መሙላት

4.4.3. በተጨማሪ ለእናትየዋ መሰጠት ያለበት ምክር

- ❖ የህፃኑ ገላ መታጠብ ያለበት ከተወለደ ከ24 ሰዓት በኋላ መሆኑን በሚገባ ማስተማር
- ❖ በህፃኑ ላይ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳይፈጸምበት ለእናትየዋና ለቤተሰብ አባላት ማስረዳት
- ❖ ጨቅላ ህፃን ሲታመም ፈጥኖ ወደ ጤና ድርጅት የሚያስኬዱ ሁኔታዎችን ማስተማርና ሲያጋጥምም ወዲያውኑ ወደ ከፍተኛ የህክምና ተቋም ሪፈር ማድረግ
  - ✓ ጡት መጥባት አለመቻል ወይም በትንሹ ብቻ መጥባት
  - ✓ መንዘፍዘፍ (ኮንቨልሽን) Convulsion
  - ✓ መዝለፍለፍ ወይም ራስን መሳት
  - ✓ ፈጣን አተነፋፈስ
  - ✓ በሚተነፍስበት ጊዜ የደረት መሰርጎድ መኖር
  - ✓ የሰውነት መቀዝቀዝ ወይም ትኩሳት
  - ✓ የሰውነት ቢጫ መሆን (የእጅ መዳፍ ፣የእግር መጫሚያ)
  - ✓ የዓይን ቀብ ማበጥና (የዓይን እር) መኖር
  - ✓ ቆዳ ላይ መግል የቋጠረ ሽፍታ መኖር

4.4.4. የጨቅላ ሕፃናትን በተመለከተ በቤት ለቤት ጉብኝት ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት

- ❖ አደገኛ ምልክት መኖር አለመኖራቸውን መለየት
- ❖ ለእናትየዋ በጨቅላ ሕፃኑ ላይ የሚታዩ አደገኛ የህመም ምልክቶችን ማሳወቅ፣ ሲታዩም በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም እንድትወስድ ማስገንዘብ
- ❖ የጨቅላ ሕፃንን አተነፋፈስ በመቁጠር ፣ የሰውነት ሙቀትና ክብደት በመለካት መመዝገብ
- ❖ የጨቅላ ሕፃኑን የሰውነት ሙቀት በአግባቡ እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል ማሳየትና ማስገንዘብ

- ስለጡት ማጥባት ክህሎት ማስተማር ፣ማሳየት
- የጨቅላ ሕፃን አትብት ምንም ሳይቀባ በንጽህና መያዝ እንደሚገባ ማሳየት፣ማስተማር፤
- የእናት ጡትን ለ6 ወራት ያለ ምንም ተጨማሪ ምግብ ማጥባት ለህፃኑ በቂና ተመጣጣኝ ምግብ መሆኑን በደንብ ማስረዳት
- ህፃኑ በበቂ ሁኔታ የእናት ጡት ወተት እንዲያገኝ እናትየዋ የተመጣጠነ ምግብ መመገብ እንዳለባት ማስተማር
- በተከታታይ ስለሚሰጡ የክትባት አይነቶች እና ጥቅማቸውን ማስተማር፤አገልግሎቱንም መስጠት
- የወባ ትንኝ ንክሻን ለመከላከል የመኝታ አጎበር መጠቀማቸውን ማረጋገጥ
- የህፃኑን እድገት ዳሰሳ መስራትና በቻርት ቡክሌቱ መሰረት ማከም
- ለእናየዋ ስለቀዳሚዩ ልጅነት ክብካቤ የምክክር አገልግሎት መስጠት
- የልደት ሰርተፍኬት መስጠት

4.5. የድህረ ወሊድ ክብካቤ

- ከወሊድ በኋላ በ24 ሰዓት ውስጥ፣ በሶስተኛው ቀንና በሰባተኛው ቀን እንዲሁም በ6ኛው ሳምንት ለእናትየዋና ለሕፃኑ/ኗ በጤና ኬላ እንዲሁም በቤት ለቤት ጉብኝት የድህረ ወሊድ አገልግሎት መስጠት፣
- አጠቃላዩ የእናትየዋንና የጨቅላ ሕፃኑን የጤና ሁኔታን በተመለከተ ምርመራ ማድረግና የጤና ትምህርት መስጠት

የ24 ሰዓት የድህረ-ወሊድ ቆይታና ክብካቤ

በጉብኝት ወቅት ሲደረጉ የሚገባቸው እንክብካቤዎች	**ለእናት** 1. እናትየዋ ምን ችግር እንዳለባት መጠየቅ። ደም ከማህጸኗ አየፈሰሰ እንደሆነ እንዲሁም ሌሎች ከወሊድ በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉ አደገኛ ምልክቶች እንዳሉባት መጠየቅ፣ምልከታም ማድረግ፤ 2. የትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም ከወሊድ በኋላ ሊከሰቱ ስለሚችሉ አደገኛ ምልክቶች ማስተማር እንዲሁም ከተከሰቱ በአፋጣኝ ወደ ከፍተኛ የጤና ተቋም መላክ፤ 3. የሰውነት ሙቀትን መለካት **38 ዲ.ሴ** እና በላይ ከሆነ ወደ ከፍተኛ የጤና ተቋም ሪፈር ማድረግ፤ 4. እንደ አስፈላጊነቱ የመንጋጋ ቆልፍ መከላከያ ክትባት (TD) መስጠት፤የአዩረን እንክብል ወስዳ ካልጨረሰች እንድትቀጥል መምከር፤ 5. የትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም ስለ አመጋገብ ሁኔታ፣ ንጽህና አጠባበቅ፣ ጤናማ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ማስተማር እንዲሁም ስለ ቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ምክር መስጠትና የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን እንደ ምርጫዋ መስጠት፤ የቅድመ-እርግዝና የምክክር አገልግሎት መስጠት 6. በፀረ ወባ ትንኝ መድሃኒት የተነከረ አጎበር ስለመጠቀም አስፈላጊነት ማስተማርና እንድትጠቀም ማበረታታት፤ 7. በእርግዝና ጊዜ ወይም በወሊድ ወቅት የኤችአቪ ምርመራ ካላደረገች የምርመራ አገልግሎት መስጠት፣ 8. ህፃኑን የጡት ወተት ብቻ እንድትመግብ ማስተማር፣ማስገንዘብ፤	**ለህፃን** 1. በቤትም ሆነ በጤና ኬላ የጨቅላ ህፃን ሴፕሲስን (Neo-natalSepsis) በGentamycin ማከም፣ 2. የጨቅላ ሕፃኑ አደገኛ የህመም ምልክት እንዳለው/እንደሌለው ማጣራት ከተከሰተ በአፋጣኝ ወደ ከፍተኛ የህክምና ተቋም መላክ፤ 3. የሰውነት ሙቀት መጠን እና የህፃኑን ክብደት መለካት፤ 4. የአይን ቅባት (TTC eye ointment) መቀባት 5. የቆዳ ሽፋታ ካለ፣ከእምብርቱ ላይ ፈሳሽ ከመጣ በአፋጣኝ ወደ ከፍተኛ የህክምና ተቋም መላክ፤ 6. ሕጻኑ ወዳያው እንዳይታጠብ ምክር ይሰጣሉ፤ (ሕጻኑ ከተወለደ በኋላ ለመታጠብ ቢያንስ አንድ ቀን መቆየት ይኖርበታል) 7. ሕፃኑ ከእናቱ ጋር ገላ ለገላ መተቃቀፍን፣ ጭንቅላቱንና እግሩን ጨምሮ በአግባቡ ልብስ መልበሱን/መጠቅለሉን ያረጋግጣሉ፤ 8. ለህፃኑ የፖልዮ (Polio)፣ እና ቢ.ሲ.ጂ (BCG) ክትባት መስጠት፤ 9. የትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ ትምህርት ይሰጣሉ፡- ✓ ጡት ማጥባት፣ ክትባት፣ለክትባት የሚደረግ ጥንቃቄ ✓ የሙቀት አጠባበቅ፡ ጨቅላ ሕፃን ላይ የሚከሰቱ አደገኛ ምልክቶች፡ ✓ ንጽህና አጠባበቅ ✓ ክትባት ጥቅም፤ ✓ በህፃኑ ላይ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ እናትንና ቤተሰብን ማስተማር፤ ✓ ስለቅዳማይ ልጅነት ትምህርት መስጠት

ተከታታይ ጉብኝት፤ እናት በወለደች በሦስተኛ፣ ሰባተኛ ቀናት እና ስድስተኛ ሳምንት መደረግ ያለበት ክብካቤና የሚከናወኑ ተግባራት

በጉብኝት ወቅት ሲደረጉ የሚገባቸው እንክብካቤዎች	**ለእናት** 1. እናትየዋ ከወሊድ በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉ አደገኛ የሕመም ምልክቶች ካሉ ምርመራ ማካሄድ፣ ከተከሰቱ ደግሞ ወዲያውኑ ወደ ከፍተኛ የህክምና ተቋም መላክ፤ 2. የትምህርት መርጃ መሳሪያ በመጠቀም ስለ ቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት፣ የግል ንጽህና፣ የአመጋገብ ሥርዓት፣ በድህረ ወሊድ ጊዜ/ከወሊድ በኋላ ሊከሰቱ ሰለሚችሉ አደገኛ ምልክቶች ትምህርት ትምህርት መስጠት፤ 3. ከጡት ማጥባት ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮች ካሉ በመጠየቅ የእናትየዋን ችግር መፍታት ፤በእናትየዋ ላይ የመመረዝ (Infection) ምልክቶች (ትኩሳት፣ ማንቀጥቀጥ፣ ሽታ ያለው ፈሳሽ ከማህፀን መውጣት እና የመሳሰሉት) ካሉባት በአፋጣኝ ወደ ከፍተኛ የህክምና ተቋም መላክ፤ 4. የቅድመ-እርግዝና የምክክር አገልግሎት መስጠት	**ለሕፃን** 1. ሕፃኑን የጡት ወተት ብቻ እንደትመግበው ማስተማር።የሕፃኑን ሙቀት በአግባቡ እንድትጠብቅ፣ ጭንቅላቱን፣ እጁን እና እግሩን እንድታለብሰው/እንድትጠቀልለው እንዲሁም ከእርሷ ጋር ገላ ለገላ እንዲተቃቀፍ ማድረግ፤ 2. በጨቅላ ሕፃናት ላይ ሊከሰቱ ከሚችሉ አደገኛ ምልክቶች ውስጥ አንዱ እንኳን ከተከሰተ በአፋጣኝ ወደ ከፍተኛ ጤና ተቋም መላክ፤ 3. ሕፃናትን በሚነካኩበት ወይም በሚንከባከቡበት ወቅት እጃቸውን መታጠብ እንዳለባቸው እንዲሁም የሕፃኑን ንጽህና መጠበቅ እንደሚገባ ማስተማር፤ 4. የሕፃኑ ክብደት እየጨመረ መሆኑን እና እትብቱ በንጽህና መጠበቁን በመመልከት ማረጋገጥና ምክር መስጠት፣

4.6. ደህንነቱን የጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት

- ከ12 ሳምንት በታች ለሆኑ ነፍሰጡር እናቶች ደህንነቱን የጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት በመመሪያው መሰረት መስጠት
    - ✓ በመድሀኒት የታገዘ የፅንስ ማቋረጥ
    - ✓ በMVA የታገዘ የፅንስ ማቋረጥ
- የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ከተሰጠ በኋላ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ላይ የምክክር አገልግሎት መስጠት

4.7. ከወሊድ ጋር በተያያዘ ምክንያት የሚከሰት ፊስቱላን መከላከል

4.7.1. ህብረተሰቡን ስለ ፊስቱላ ምንነት የማሳወቅ ስራ መስራት

- ከወሊድ ጋር የተያየዘ ፊስቱላ ምንነትን ማስተማር፣
- ሁሉም እናቶች ምጥ እንደጀመራቸው ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ክህሎት ባለው የጤና ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ማግኘት እንዳለባቸው ማስተማር፤
- ከወሊድ ጋር የተያየዘ ፊስቱላ መከሰት አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ምክንያቶችን በዝርዝር ለይቶ ማስተማር፤
- ከወሊድ ጋር የተያየዘ ፊስቱላን መከላከልና ከተከሰተም ችግሩን በህክምና ማዳን እንደሚቻል (ከህመሙ ታክመው የዳኑ ሴቶች/እናቶችን በመያዝ) ማስገንዘብ፣ማስተማር፤
- ከወሊድ ጋር የተያየዘ ፊስቱላ የሚያደርሰዉን ጉዳት (ሴቶች ሽንትና አይነምድር መቆጣጠር ባለመቻላቸው ምክንያት በሚፈጠር መጥፎ ጠረን የተነሳ ከትዳር አጋሮቻቸዉ መለየት፣ከቤተሰብ መገለልና ድብርት/ህመም) እንዲሁም ከህብረተሰቡ መገለል እንዳይደርስባቸውና ህብረተሰቡ ከጎናቸው ሆኖ ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያደርግላቸው ማስተማር/ማስተባበር፣
- ከህክምና በኋላ ከፊስቱላ የዳኑ ሴቶችን በፊት ይኖሩበት ከነበረ ማህበረሰብ ጋር የማቀላቀል ስራ መስራት፤

- በአርግዝና እና በወሊድ ጊዜ የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶችን በጊዜው እንዳያገኙ ሲያደርጓቸው የሚችሉ ምክንያቶችን በመለየት በጤና ኬላ ደረጃ የሚፈታውን ችግር መፍታት ሌሎቹን ደግሞ ለሚመለከተው ክፍል (ለአቅራቢያው ጤና ጣቢያ፣ለወ/ጤ/ጥ/ጽ/ቤት) ማቅረብና አብሮ መፍትሄ ማፈላለግ፣

4.7.2. ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላና የማህፀን መውጣት ተጠቂዎችን ልየታ፣ ምርመራና ሪፈራል

- የሽንት ወይም አይነምድርን /ሁለቱንም የመቆጣጠር ችግር ያጋጠማቸውን እንዲሁም የማህፀን መውጣት ችግር ያለባቸውን ሴቶች መለየት፤
- የሽንት ወይም አይነምድርን/ሁለቱንም የመቆጣጠር ችግር ያጋጠማቸውን እንዲሁም የማህፀን መውጣት ችግር ያለባቸውን ሴቶች ወደ ከፍተኛ ጤና ተቋም ለምርመራ ሪፈር ማድረግ
- የአካባቢውን ማህበረሰብ በማስተባበር እንደ አስፈላጊነቱ የገንዘብ መዋጮ በማሰባሰብ ለትራንስፖርት አገዝ እንዲደረግላቸው ማስተባበር፤
- በጎጥ ጤና መሪዎች፣ ሴቶች ልማት ቡድን፣ በሃይማኖት አባቶች፤ በልምድ አዋላጆች እና በሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች አማካኝነት የሽንትና አይነ ምድር መቆጣጠር ችግር ያጋጠማቸውን ሴቶች ለጤና ኬላ እንዲያሳውቁ ማድረግ
- የሽንት ወይም አይነምድርን /ሁለቱንም የመቆጣጠር ችግር ያጋጠማቸውን ሴቶች ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላ መሆኑን በምርመራ ማረጋገጥ
- የሽንት ወይም አይነምድርን /ሁለቱንም የመቆጣጠር ችግር ያጋጠማቸውን ሴቶች ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላ መሆኑ በምርመራ የተረጋገጠ ከሆነ ወደ ፊስቱላ የህክምና ማዕከል ሪፈር ማድረግ
- የማህፀን መውጣት ችግር ያለባቸውን ሴቶች ምርመራ ከተደረገላቸው በኋላ አገልግሎቱን ወደሚሰጡ ሆስፒታሎች ሪፈር ማድረግ
- ቀጣይነት ያለው የህመምተኞች ልየታ እንዲሁም ሪፈራል እንዲኖር ለማድረግ ከህመሙ ታክመው የዳኑ እናቶችን የልየታውን ስራ እንዲሰሩ በማስተባበር የፊስቱላ ተጠቂዎች ቶሎ ህክምና እንዲያገኙ በማድረግ ቀበሌውን/ዎችን ከ"ፊስቱላ ነፃ" የማድረግ ስራ መስራት፣

የመሰረታዊና አጠቃላይ ጤና ኬላ ባለሙያዎች ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላን በተመለከተ ለማህበረሰቡ ሲያስተምሩ ትኩረት የሚያደርጉባቸው ቁልፍ ነጥቦች:-

- በወሊድ ምክንያት የሚከሰተውን ፊስቱላ መከላከል እንደሚቻል
- ሴት ልጅን ማስተማር እንደሚያስፈልግ
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማስወገድ እንደሚገባ
- ጋብቻንና የመጀመሪያ ወሊድን ማዘግየት ጠቃሚ እንደሆነ
- የቤተሰብ እቅድ በመጠቀም ወሊድን ማራራቅ እንደሚገባ
- ክህሎት ባለው ባለሙያ በጤና ተቋም መውለድ ያለውን ጠቀሜታ
- የፊስቱላ ችግር ያጋጠማቸው ሴቶች በቀዶ ህክምና ሊድኑ እንደሚችሉ
- በዋና ዋና ርእሶች ላይ የቤተሰብ ጤና ትምህርት መስጠት፤
- ሴቶች በቅድመ ወሊድ፣ ወሊድ፣ እና በድህረ ወሊድ ወቅት ሊያውቋቸው የሚገቡ የማስጠንቀቀያ ምልክቶችን በተመለከተ ሙሉ መረጃ እንዲኖራቸዉ ማድረግ፤ ችግሩ ሲከሰትም በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም እንዲሄዱ ማስተማር፤

4.8. በጎ ፈቃድ ደም ለጋሾችን በመመልመል ደም ማሰባሰብ

- ❖ ከመደበኛው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ጎን ለጎን የበጎ ፈቃድ ደም ልገሳንና የጤናማ አኗኗር ዘዩቤዎችን በማህበረሰቡ ውስጥ በስፋት በማስተማር የደም ማሰባሰብ ፕሮግራምን ማሳካት፣

- ❖ የጤና ኬላ ባለሙያዎች ለህብረተሰቡ ከፍተኛ ቀረቤታ ስላላቸው የህብረተሰቡን አመለካከትና ባሕርዩ በቀላሉ መረዳት ስለሚችሉ ስለ ደም ማሰባሰብ ያለውን አሉታዊ አመለካከት ተከታታዩ ትምህርት እየሰጡ በማስተካከል የደም ልገሳ ጥቅም ማስረጽ የበጎ ፈቃድ ደም ለጋሾችን ቁጥርም ማበራከት ፤

- ❖ በደም መፍሰስ ምክንያት የሚሞቱትን እናቶች ለመታደግ ማህበረሰቡ የደም ልገሳ እንዳያደርግ ግንዛቤ መፍጠር እና ማነቃቃት

- ❖ ከጎጥ ጤና መሪዎች፣ ከልማት ቡድን መሪዎች፤ ከቀበሌ አመራሮች፣ በአካባቢው ከሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ እና መንግስታዊ የልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በትምህርት ቤቶች በመገኘት የበጎ ፈቃድ ደም ልገሳን ጥቅም ለሕብረተሰቡ በሚገባ ማስተማር፣

- ❖ ሰዎችን አስተምሮ፤ ቀስቀሶና መልምሎ የበጎ ፈቃድ ደም ለጋሾች እንዲሆኑ ለማድረግ ስለ ደም እና የደም ማስተላለፍ ህክምና አገልግሎት በቂ መረጃ መስጠት፡፡

  - ✓ አንድ ጤነኛ ሰው በጎ ነገር የማድረግ፣ ያለውን የማካፈልና ሌሎችን የመርዳት ባህልና ስሜት በውስጡ ዩኖረዋል ተብሎ ዩገመታል፡፡ ሆኖም **ደም** መቼ የት በማንና ለምን እንደሚፈለግ፤ የሚፈለገው **ደም** እርሱ/ሷ ያለው መሆኑን ተገንዝቦ/ባ ደም እንዲለግሱ ለህብረተሰቡ ማስረዳት፤

  - ✓ የደም እና የደም ተዋጽኦ ማስተላለፍ ሕክምና ለምንና ለማን እንደሚሰጥ፣ደም መለገስ የሚችሉና የማዩችሉ ሰዎች ስለመኖራቸው፣ ሰዎች ደም መለገስ ያለባቸው በበጎ ፈቃድ ብቻ ስለመሆኑ፣ ደም በመለገስ የሚመጣ ምንም ዓዩነት የጤና ችግር ስላለመኖሩ፣ለሰው የሚሆን ደም ከሰው ብቻ የሚገኝና በሌላ ሰው ሠራሽ መድኃኒት ሊተካ የማዩችል መሆኑን፣ ወዘተ. ግንዛቤ የማስጨበጫ ትምህርት ለህብረተሰቡ መስጠት፤

  - ✓ ደም ለጋሾች ጤናማ የአኗኗር ዘዩቤ መርህን እንዲከተሉ ማስተማር፣ ስለደም ማስተላለፍ ህክምና የሚነገሩ አንዳንድ አፈ-ታሪኮች ትክክል አለመሆናቸውን እውነታዎችን ለህብረተሰቡ በግልጽ ማስተማርና ማሳወቅ፤

- ❖ በጎ ፍቃደኞች ከተመለመሉ በኋላ በአከባቢው ከሚገኝ ደም ባንክ ሄደው እንዲለግሱ ወዩም በአከባቢው በዘመቻ ደም ሲሰበሰብ ተገኝተው ደም እንዲሰጡ ማድረግ፤

4.9. የእናቶች ሞት ቅኝትና ምላሽ

4.9.1. ህብረተሰቡን ስለ እናቶች ሞት ቅኝትና ምላሽ ማስተማር

- ❖ የእናቶች ሞት (Maternal Death) ምንነትና መንስኤን ማስተማር፤

- ❖ የእናቶች ሞት ቅኝት እና ተገቢው ምላሽ ምን እንደሆነና በማህበረሰብ ደረጃ የሚኖረውን የአተገባበር ሂደት ማስተማር፤

- ❖ ለእናቶች ሞት ቅኝትና ምላሽ መመሪያ፤ ለሞት መንስኤ የሚሆኑትን እና መከላከል በምንችላቸው ችግሮች ላይ መረጃ መስጠት፤ ከአርግዝና ጋር ተያይዞ በሚደርስ የእናቶች ሞት መጠን ላይ ትክክለኛ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ እንዲቻል መረጃን በአግባቡ መያዝ፤

4.9.2. በህብረተሰቡ ውስጥ የእናቶች ሞት ልየታን ማከናወን

- በማህበረሰቡ ውስጥ ማንኛውም ከ15- 49 ዓመት የሆች ሴት ከሞተች የሞተችበትን ምክንያት ለጤና ኬላ ሪፖርት እንዲያደርጉ ለጎጥ ጤና መሪዎችና ልማት ቡድን መሪዎች ማስተማር፣ሴሎች መረጃዎችንም በአስቸኳይ እንዲያቀርቡ ማስገንዘብ፤

- በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ለአቅመ-ሔዋን የደረሰች ሴት ሞት ምክንያት ምን እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ በመሆን የሚያገለግሉት የጎጥ ጤና መሪዎች፣ ሴቶች ልማት ቡድን፣ የቀድሞ ልምድ አዋላጆች፣ እና የሃይማኖት አባቶች መሆናቸውን በሚገባ ተገንዝቦ የእነሱን አቅም በተከታታይ ትምህርት ማጠናከር/መገንባት፤

4.9.3. በህብረተሰቡ ውስጥ የሞቱትን እናቶች መረጃ ወደ አቅራቢያ ጤና ጣቢያ መላክ

- ለተጠረጠሩ የእናቶች ሞት መንስኤ የቃል ምስክር መረጃ (verbal autopsy) በሟች ቤት በመሄድ መሰብሰብ። የተሞላዉን የቃል ምስክር መረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ ለመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ (ለጤና ጣቢያ) ወይም ለወረዳው ማቅረብ፤

4.10. አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

4.10.1. የስራ መርጃ መሳሪያና መመሪያዎች (Job aids)

- የቅድመ-እርግዝና መመሪያ
- የቅድመ-ወሊድ መመሪያ
- ቅድመ ወሊድ፣ወሊድ እና ድህረ ወሊድ ክትትል ፕሮቶኮል
- ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ጽንስ/ልጅ እንደይተላለፍ መከላከል ፕሮቶኮል
- የጤና ኤክስቴሽን ሰራተኞች የእናቶችና ጨቅላ ህፃናት/CMNCH የተሃድሶ ስልጠና ማኑዋል
- የእናቶች ሞት ቅኝትና ምላሽ መመሪያ
- ደህንነቱን የጠበቀ የተሟላ የጽንስ ማቋረጥ መመሪያ

4.10.2. የህክምና ቁሳቁሶች እና ሊኖሩ የሚገቡ የህክምና መድሐኒቶችና የህክምና ቁሳቁሶች

- የቤተሰብ ጤና ማህደር
- ወንበር፣ጠረጴዛ፣መደርደሪያ፣
- የክብደት መለኪያ፣መወጣጫ፣የምርመራ አልጋ፣የማዋለጃ አልጋ-
- መሸፈኛ ጨርቅና ላስቲክ/ Draw sheet and Rubber sheet/፣
- የደም ግፊት መለኪያ
- የፅንሱ የልብ ትርታ ማዳመጫ፣የሙቀት መለኪያ፣
- የቀጠሮ መስጫ ካርድ፣የጋዋን መስቀያ፣
- የማዋለጃ እና የእስተች /Episiotomy and delivery set/፣Kidney dish፣

- የጥጥና የፋሻ ማስቀመጫ/Drum cotton/gauze፣
- ሰማዋሰድ የሚያገለግሉ የህክምና አልባሳት/Personal protective materials/ apron, eyegoogle, Boots shoe/፣
- የመጠቅለያ ጨርቆች/Different size drapes/፣
- የህክምና እቃ ማቅረቢያ/Trolly/፣
- በረኪና፣ኦሞ፣
- አውቶክሌቭ/Autoclave/፣
- የእንግዴ ልጅ መጣያ ባልዲ/Placenta disposal container/፣
- የቆሻሻ መጣያ (Dust bin) ፣ሴፍቲ ቦክስ/Safety box/፣
- ጓንት/Glove/፣ፋሻ/Gause/፣በደም ስር የሚሰጥ ፈሳሽ ማስቀየ/IV stand/፣
- በደም ስር የሚሰጡ መድሐኒቶች መስጫ መርፌ/IV canula different size/፣
- የእትብት ማሰሪያ ክር/Cord clamp/፣
- ፕላስተር ፣
- torniquate፣IV set፣መርፌ/Syringe with needle different size፣
- አምቡ ባግ/Ambu bag (Adult and infant size) suction machine/፣Tape meter፣Suction bulb manual/Machine፣
- የመመርመሪያ መብራት/ Examination light/፣
- የጨቅላ ህፃን መለኪያ ሚዛን/Baby weight scale፣
- Antiseptics፣Suction tube፣
- Catheter adult size፣Birth certificate፣Gause/cotton swab ፣Antiseptics ፣Deteregent/soap

4.10.3. በጤና ኬላ ሊኖሩ የሚገቡ የህክምና ግብዓቶችና መድሐኒቶች

- በደም ስር የሚሰጡ ፈሳሾች/IV fluids/ NS, DNS, DW, RL, Glucose 40%)
- Erogometrine, ceftraxion, Vitamin K, TTC Eye ointment፣ BCG & OPV vaccine
- Amoxacillin, Gentamycin injection፣
- የኤች አይ ቪ ምርመራ ኪት፣
- Pitocine/ oxitocine, MgSO4፣Iron folate and folic acid
- የመንጋጋ ቆልፍ ከትባት መድኃኒት (TD vaccine)፣
- Albendazol

4.11. በማህበረሰብ/ጤና ኬላ ደረጃ የሚሰጠውን አገልግሎት እንዴት በጤና ጣቢያ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ማስተሳሰር እንደሚቻል

- ❖ በማህበረሰብ ደረጃ የጎጥ ጤና መሪዎችና የልማት ቡድን አደረጃጀቶችን በመጠቀም ነፍሰጡር እናቶችን/በቅድመ ወሊድ፣ወሊድ፣ድህረ ወሊድ፣የጨቅላ ህጻናትን በመለየት በጤና ኬላ ደረጃ አስፈላጊውን አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ፣ከአቅም በላዩ የሆኑ አገልግሎቶችን ወደ የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ አሃድ አምቡላንስ በመጠቀም ሪፈር ማድረግ፣ከጤና ጣቢያ ግብረ መልስ መቀበል፣
- ❖ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የተቀናጀ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም ሙያዊ እና የግብዓት ድጋፍ ያደርጋሉ፣

4.12. በእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ❖ በቀበሌው የሚገኙ ሁሉም ነፍሰጡር እናቶች ከ3 ወር በፊት የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ያገኛሉ
- ❖ በቀበሌው የሚገኙ ሁሉም ነፍሰጡር እናቶች ስምንትና ከዚያ በላዩ የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ያገኛሉ
- ❖ ሁሉም የቀበሌው ነፍሰጡር እናቶች የቂጥኝ ምርመራ ያገኛሉ
- ❖ ሁሉም የቀበሌው ነፍሰጡር እናቶች በሰለጠነ የጤና ባለሙያዎች በጤና ተቋም የወሊድ አገልግሎት አገልግሎት ያገኛሉ
- ❖ ሁሉም በቀበሌው የሚገኙ በጤና ተቋም የወለዱ እናቶች የ24 ሰዓት የድህረ ወሊድ ቆይታና ክብካቤ በጤና ተቋሙ ያገኛሉ
- ❖ ሁሉም በቀበሌው የወለዱ እናቶች በመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ ተከታታዮችን የድህረ ወሊድ አገልግሎቶች ያገኛሉ
- ❖ ሁሉም ነፍሰጡር እናቶች ቅድመ ወሊድ፣ወሊድ፣ድህረ ወሊድ ወቀት የኤች አይ ቪ ምርመራና ምክር አገልግሎት ያገኛሉ
- ❖ ሁሉም በቀበሌው የሚገኙ ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላ እንዲሁም የማህፀን መውጣት ችግር ያለባቸው እናቶች ልየታ፣ ምርመራ፣ ሪፈራልና ህክምና ያገኛሉ
- ❖ ሁሉም በቀበሌው የሚገኙ የታከሙ ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላ ችግር ያለባቸው እናቶች መልሶ የማቋቋም ስራ ይሰራል
- ❖ በቀበሌው የሚገኙ በመውለድ እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሴቶች በመመሪያው መሰረት ደህንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ያገኛሉ
- ❖ ሁሉም በቀበሌው የሚገኙ በመውለድ እድሜ ክልል ሆነው የሞቱ እናቶች ሪፖርት ይደረጋሉ
- ❖ በጎ ፈቃደኛ የደም ለጋሾች ይመለመላሉ

4.13. የእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ክትትልና ግምገማ

- ❖ አገልግሎቱን የጥራት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በትክክል መተግበር፣ እቅዱ በትክክል እየተፈጸመ መሆኑን መከታተል፤ የአፈጻጸም ችግሮችን ለይቶ እንደየባህርያቸው በቅደም ተከተል ማስቀመጥና መፍትሄ መስጠት፣
- ❖ ጤና ጣቢያ ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ደግሞ ለጎጥ ጤና መሪዎችና ልማት ቡድኖች አደረጃጀቶች ክፍተትን መሰረት ያደረገ የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣሉ፣
- ❖ ከመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ፣ ከጎጥ ጤና መሪዎችና ልማት ቡድን መሪዎች እንዲሁም ከቀበሌ አስተዳደር አካላት ጋር በየጊዜው የእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዕቅድ አፈዓጸምን በተመለከተ ግምገማ ማካሄድ፣

4.14. የእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ መለኪያዎች

- ለመጀመሪያ ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል ያገኙ ነፍሰጡር እናቶች ብዛት
- ለአራተኛ ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል ያገኙ ነፍሰጡር እናቶች ብዛት
- ለስምንተኛ ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል ያገኙ ነፍሰጡር እናቶች ብዛት
- ለቂጥኝ የተመረመሩ ነፍሰጡር እናቶች
- በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ ነፍሰጡር እናቶች ብዛት
- የድህረ ወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ብዛት
- የኤች አይ ቪ ምርመራና የምክር አገልግሎት ያገኙ ነፍሰጡር እናቶች ብዛት፣
- ከተመረመሩት ነፍሰጡር እናቶች ውስጥ በደማቸው ኤች አይ ቪ የተገኘባቸው፣ተገኝቶባቸው ህክምናውን የሚከታተሉ እናቶች ብዛት
- ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላ ታማሚ መሆናቸው የተለዩ እናቶች ብዛት፣
- ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፊስቱላ ታማሚ ሆነው በምርመራ የተረጋገጡ እናቶች ብዛት፣
- የተለዩ የማህፀን መውጣት ችግር ያለባቸው እናቶች ብዛት፣
- ደህንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ብዛት፣
- ሪፓርት የተደረጉ የእናቶች ሞት ቁጥር
- በጎ ፈቃደኛ የደም ለጋሾች ብዛት

ምዕራፍ 5
የስርዓተ-ምግብ አገልግሎት

5

5.1. በመሰረታዊና በአጠቃላይ ጤና ኬላዎች የሚከናወኑ የስርዓተ-ምግብ ተግባራት

ተቁ	ዋና ዋና አገልግሎቶች	በመሰረታዊ ጤና ኬላ	አጠቃላይ ጤና ኬላ
I.	**የቅድመ እርግዝና የስርዓተ ምግብ አገልግሎቶች**		
1	የቅድመ ወሊድ የስርዓተ ምግብ ሁኔታ ልኬት ዳሰሳና የምክክር አገልግሎቶች መስጠት	√	√
2	የአዩረን ፎሌት እንክብል (30 – 60 ሚግ አዩረን እና 0.4 ሚግ ፎሌት) ከእርግዝና ሶስት ወራት በፊት መስጠት	√	√
3	ለከፍተኛ የፎሌት እጥረት ተጋላጭነት ላላቸው ሴቶች መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ፎሌት (5 ሚግ በየቀኑ) ቢያንስ ለሶስትወራት ከእርግዝና በፊት ይሰጣል፡፡	X	√
II.	**ለነፍሰጡር እናቶች ሥርዓተ ምግብ አገልግሎቶች**		
1	የነፍሰጡር እናቶች የክብደት አጨማመር ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት እና የተመጣጠነ ምግብ አመጋገብ ላይ የምክክር አገልግሎት መስጠት	√	√
2	ለነፍሰ ጡር እናቶች በቅድመ ወሊድ ክትትል ጊዜያት የአዩረን ፎሌት እንክብል (30–60 ሚ.ግ አዩረን እና 400 ሚ.ግ ፎሊክ አሲድ) በየቀኑ ለ180 ቀናት (6ወራት) መስጠት፤ ስለጥቅሙ፣ በተከታታይ ስለመውሰድ እንዲሁም ቢከሰቱ ስለሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶችች ክትትልና ድጋፍ በየጊዜው ማድርግ፡፡	√	√
3	የነፍሰጡር እናቶችን አጣዳፊ የምግብ እጥረት ልየታና ህክምና አገልግልት እና የምክክር አግልግሎት መስጠት	√	√
4	የመጀመሪያ ሶስት ወራት እርግዝና ከሞላቸው በኋላ ባለ 400 ሚሊ ግራም አልቤንዳዞል ወይንም ባለ 500 ሚሊ ግራም ሜብንዳዞል ኪኒን አንድ ጊዜ መስጠት	√	√
5	የነፍሰጡር እናቶች የደም ማነስ ምርመራና ህክምና መስጠት	X	√
6	ለነፍሰጡር እናቶች የካልሲየም ንጥረነገር (**1.5–2.0** ግራም) በእርግዝና ክትትል ወቅት መስጠት	X	√
7	እናቶችን ከወሊድ በኃላ ወዳያውኑ ጡት ማጥባት እንዲጀምሩና ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት የጡት ውተት ብቻ ልጆቻችውን መመገብ እንዳለባቸው፤ የምክክር አገልግሎት መስጠት	√	√
III	**ለሚያጠቡ እናቶች ስርአተ ምግብ አገልግሎቶች**		
1	አጣዳፊ የምግብ እጥረት ልየታና ህክምና	√	√
2	የምግብ ዋስትና ችግር ያለባችውን እናቶች በመለየት በልማታዊ ሴፍትኔትና ሌሎች የማህበረሰብ ጥበቃዎች ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ	√	√
3	በፊት ከሚመገቡት በተጨማሪ ሁለት መክሰስ መመግብ እንዳለባቸው የምክክር አገልግሎት መስጠት	√	√
4	ያልጨረሱት የአዩረን ፎለት እንክብል ካለ እንዲውስዱ ማድረግ	√	√
IV	**የወጣቶች የስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች**		
1	እድሜያቸው ከ10 እስከ 19 ዓመት ለሆኑ ወጣቶች የስርአተ ምግብ ሁኔታ ልኬት በየሶስት ወራቱ አንድ ጊዜ፤ በጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች በወጣት ማእከላትና ሌሎች የማህበረሰብ ተቋማት መስጠት፡	√	√
2	አጣዳፊ ምግብ እጥረት ልየታ (BMI for Age) መለካትና የምክክርና ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፤	X	√
3	የምግብ ዋስትና ችግር ያለባችውን ወጣቶች በመለየት በልማታዊ ሴፍትኔትና ሌሎች የማህበረሰብ ጥበቃዎቸ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ	√	√
4	ሳምንታዊ የአዩረን ፎሌት (60 ሚግ አዩረን እና 2.8 ሚግ ፎሊክ አሲድ) እንክብል በሳምንት አንድ ጊዜ ለሶስት ተከታታይ ወራት፤በዓመት ሁለት ጊዜ መስጠት	√	√
5	የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች መከላከየ 400 ሚግ አልቤንዳዞል ወዩም 500 ሚግ ሜቤንዳዞል ክኒን በየ6 ወራት አንድ ጊዜ (በዓመት ሁለት ጊዜ) በጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ በወጣት ማእከላትና ሌሎች የማህበረሰብ ተቋማት መስጠት	√	√

V	**የህፃናት የስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች (0-59 ወራት ላሉ)**		
1	ለእድሜ ተመጣጣኝ የሆነ የጨቅላና ታዳጊ ህጻናት አመጋገብ ምክክር አገልግሎት እድሜአቸው ከ0_24 ወራት ለሆኑ ህጻናት ወላጆችና አሳዳጊዎች መስጠት (የጡት ማጥባትና ተጨማሪ ምግብ)	√	√
2	የእድገት ክትትልና ማበልፀግ አገልግሎት እድሜአቸው ከ0_24 ወራት ለሆኑ ህጻናት በየወሩ መስጠት	√	√
3	የተጨማሪ ምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ላዩ እድሜአቸው ከ6_24 ወራት ለሆኑ ህጻናት እናቶችና አሳዳጊዎች፤ የምግብ ሰርቶ ማሳየ በየወሩ በጤና ተቋማት፣ ማህበረሰብ፣ የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማካሄድ	√	√
4	እድሜአቸው ከ6-59 ወራት ለሆኑ ህጻናት በስድስት ወር አንድ ጊዜ (በአመት ሁለት ጊዜ ቫይታሚን ኤ ጠብታ መስጠት	√	√
5	የአጣዳፊ የምግብ እጥረት ልየታ እድሜአቸው ከ6_59 ወራት በቋሚነትና ታመው ለህክምና በሚመጡበት አጋጣሚ መስጠት	√	√
6	እድሜአቸው ከ12-24 ወራት ለሆኑ ህጻናት በስድስት ወር አንድ ጊዜ (በአመት ሁለት ጊዜ) የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች መከላከያ ኪኒን (400 ሚግ አልቤንዳዘል ወይም 500 ሚግ ሜቤንዳዘል መስጠት)	√	√
7	አጣዳፊና ከፍተኛ የምግብ እጥረት ህክምና በተመላላሽ መስጠት (6-59 ወራት ላሉ)	√	√
8	አጣዳፊና መካከለኛ የምግብ እጥረት አስተኝቶ ህክምና አገልግሎት (6-59 ወራት) ህጻናት መስጠት	X	√
VII	**የታዳጊ ልጆች የስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች (5¨-10 ዓመት)**		
1	የስርአተ ምግብ ሁኔታ ልኬትና የምክክር አገልግሎት በየሶስት ወራት አንድ ጊዜ ማድረግ	√	√
2	የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች መጠን ከፍተኛ በሆነባቸው አካባቢዎች በአመት አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ የአልቤንዳዘል ወይም ሜቤንዳዘል እደላ ማድረግ	√	√
3	ጤናማ አመጋገብና የአካል እንቅስቃሴ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ማድረግ	√	√
VIII	**ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ (ከአኗኗር ዘይቤ ጋር የሚያያዙ) በሽታዎች ላሉባቸው ሰዎች የስርአተ ምግብ አገልግሎቶች**		
1	እንደ HIV, TB, Malaria የመሳሰሉ ተላላፊ በሽታዎች ላሉባቸው ታካሚዎች በየጊዜው የስርአተ ምግብ ሁኔታ ልኬት፤ የምክክርና ሪፈራል አገልግሎቶችን መስጠት	√	√
2	እንደ ደም ግፊት፣ ስኳር፣ ውፍረት/ከመጠን ያለፈ ውፍረት የመሳሰሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች/ሁኔታዎች ላሉባቸው በየጊዜው የስርአተ ምግብ ሁኔታ ልኬት፤ የምክክርና ሪፈራል አገልግሎቶችን መስጠት	√	√
VIII	**የምግብና ስርአተ ምግብ ዘርፈ ብዙ ቅንጅታዊ አሰራር መደገፍ፣ በቴክኒክ መምራት**		
1	ከግብርና፣ ትምህርት፣ ሴቶች ህጻናትና ወጣቶች፣ ውሃ፣ የመሳሰሉ ዘርፎች ጋር የምግብና ስርአተ ምግብ ትግበራ በጋራ ማቀድ፣ መተግበርና መገምገም	√	√
2	የቀበሌ ኮሚቴው በየጊዜው ተገናኝቶ የስርአተ ምግብ ተግባራት እንዲገመግሙ ማመቻቸት፣ ሪፓርቶችን ማቀናጀትና ለሚመለከተው መላክ	√	√
IX	**የቅድመ እርግዝና የስርአተ ምግብን ማሻሻል**		
1	የቅድመ ወሊድ የስርዓተ ምግብ ሁኔታ ዳሰሳና የምክር አገልግሎት	√	√
2	የአይረን ፎሌት እንክብል (30 - 60mg አይረን እና 400µg/0.4mg ፎሌት) መስጠት	√	√
3	መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ፎሌት (5mg በየቀኑ) ቢያንስ ለሶስት ወራት ከወሊድ በፊት ይሰጣሉ።	X	√

5.1.1. መረጃ መሰብሰብና ማቀድ

- የጤና ኬላ ባለሙያዎች በጎጥ ጤና መሪዎችና ልማት ቡድን መሪዎች በመታገዝ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ቅድመ እርግዝና አገልግሎት ታሳሚ ሴቶችን ለዩታ መረጃ መያዝ፣
- ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ማቀድ
- ከሌሎች ሴክተሮች ጋር የሚሰሩ ተግባራትን መለየትና የጋራ ማድረግ
- ለእናቶችና ለህጻናት በማህበረሰብ ውስጥ የስርዓተ-ምግብ ልየታ ሄ,ሁኔታ ልየታ ስራዎችን በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ

5.2. ለነፍሰጡር እናቶች የስርዓተ-ምግብ ሁኔታ ማሻሻል

- የጤና ኬላ ባለሙያዎች በጤና ኬላ ወይም በቤት ለቤት ጉብኝት ወቅት ለቅድመ ወሊድ እንክብካቤ ወይም ለሌላ አገልግሎት ነፍሰ ጡር እናቶችን በሚያገኙበት ወቅት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡
    - ✓ በእርግዝና ወቅት የተመጣጠነ ምግብ አለመመገብ ሊያስከትላቸው ስለሚችላቸው ችግሮች ማስተማር ለምሳሌ፡- በእናቲቱና በህጻኑ ላይ ስለሚደርሰው የጤና መታወክ፣ በምግብ መጎዳት ለውርጃና ያለቀን ለመውለድ ማጋለጡን፣ በህጻኑ ላይ ሊደርስ ስለሚችለው የአንጎልና የአካል እድገት መስተጓጎል እና ጨቅላው ሲወለድ ዝቅተኛ ክብደት ሊኖረው እንደሚችል ታስረዳለች
    - ✓ ነፍሰ-ጡር እናቶች ቤት ያፈራውን የተለያዩ የምግብ ምድብ ስብጥሮችን መመገብ አለባቸው፡፡ በተለይም የእንስሳት ውጤቶች/ ሥጋ፣ አሳ፣ወተት እና የወተት ተዋጽኦዎች፣ እንቁላል፣ ወዘተ/ ፍራፍሬዎች እና አትክልት/ፓፓያና ማንጎ፣ ብርቱካን፣ ካሮት፣ዱባ፣ ሙዝ፣ አቮካዶ፣ስኳር ድንች፣/፤ ጥራጥሬዎችን/አተር፣ምስር፣ባቄላ፣ሽምብራ.../የአህል ዘሮች/ገብስ፣ስንዴ፣ጤፍ፣ቆጮ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው፡፡
- ነፍሰ-ጡር እናቶች ተጨማሪ የሃይል ፍላጎታቸውን ለማሟላት በቀን ቢያንስ አንድ ተጨማሪ በንጥር ምግብ ይዘቱ የበለጸገ መክሰስ መመገብ አለባቸው፤ የነፍሰጡር እናቶች የክብደት አጨማመር ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት መስጠት
- የነፍሰጡር እናቶች አጣዳፊ የምግብ እጥረት ልየታና ህክምና አገልግልት መስጠት
- የደም ማነስን ለመከላከል ለሁሉም ነፍሰጡር እናቶች በየቀኑ ለስድስት ተከታታይ ወራት የሚሆን አይረን ፎሌት እንክብል መስጠት፤ በትክክል መውሰዳቸውንም በማህበረሰብ አደረጃጀቶች በኩል በመታገዝ ክትትል ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በመጀመሪያ ሶስት ወራት እርግዝና ከሞላቸው በኋላ ባለ 500 ሚሊ ግራም ሜብንዳዞል/400 ሚሊ ግራም አልበንዳዞል ኪኒን አንድ ጊዜ ይሰጣሉ፡፡
- የነፍሰጡር እናቶች የደም ማነስ ምርመራና ህክምና መስጠት
- ለነፍሰጡር እናቶቸ የካልሺየም እንክብል አደላ በየቀኑ (1.5-2.0ግራም) ለ180 ቀናት መስጠት
- ከወሊድ በኃላ ውዳያውኑ እናቶችን ጡት ማጥባት ማስጀመር እና ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት የጡት ውተት ብቻ ልጆቻችውን መመገብ እንዳለባቸው የምክክር አገልግሎት መስጠት
- የደም ማንስን ለመከላከል ለነፍሰ ጡር እናቶች በቅድመ-ወሊድ ክትትል ጊዜያት የአይረን ፎሌት እንክብል (30 – 60 ሚ.ግ አይረንና 400 ሚ.ግ/0.4 ሚ.ግ ፎሊክ አሲድ) በየቀኑ ለ180 ቀናት (6ወራት) መስጠት፤ ስለአወሳሰዳቸው እንዲሁም ሊከሰቱ ስለሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶቶች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

- ❖ የጎጥ ጤና መሪዎችና የልማት ቡድን መሪዎች ስለ ነፍሰጡር እናቶች አመጋገብ በመንደራቸው ከሚገኙ ነፍሰጡሮች ጋር አስፈላጊውን ምክክርና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ አገዛና ክትትል ማድረግ፤ የቤተሰቡ አባላት፣ በተለይም ነፍሰ ጡር እናቶች ለምግብነት የሚጠቀሙት ጨው በአዮዲን የበለጸገ እንዲሆን ማበረታታት
- ❖ የትዳር አጋሮችና ሴሎች የቤተሰቡ አባላት ለነፍሰጡር ሴቶች በሥርዓተ ምግብ ዙሪያ አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያደርጉ ምክክር ማድረግ
- ❖ ለሁሉም ነፍሰጡር እናቶች የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታ ልኬታና እንደየሁኔታውም ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ

5.3. የሚያጠቡ እናቶች ስርዓተ-ምግብ ማሻሻል

- ❖ የሚያጠቡ እናቶች የሀይልና ሴሎች ንጥረ ምግቦች ፍላጎት ይጨምራል፤ ይሄንንም ለማሟላት በየቀኑ የተሰባጠረ ምግብ ቢያንስ ከአምስት የምግብ ምድቦች መመገብ እንዳቻሉ ምክክርና ድጋፍ ማድረግ፤ ሁለት ተጨማሪ መክሰስ መመገብ ይኖርባቸዋል።
- ❖ አጣዳፊ የምግብ እጥረት ልየታና ህክምና ፤ የምግብ ድጋፍ በልማታዊ ሴፍትኔትና ሴሎች የማህበረሰብ ድጋፎች እንድያገኙ ማድረግ
- ❖ በጎጥ ጤና መሪዎችና በልማት ቡድን መሪዎች በመታገዝ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙትን የሚያጠቡ እናቶችን ለይታ መመዝገብና ማወቅ ይኖርባታል
- ❖ የሚያጠቡ እናቶችን በቤት ለቤት ጉብኝት ወቅት፣ በጤና ኬላ ድህረ ወሊድ ክትትል ወይም ለሴላ አገልግሎት በምታገኝበት ወቅት የሚከተሉትን ተግባራት እንድታከናውን ይጠበቃል።
    - ✓ የሚያጠቡ እናቶች ጤንነታቸው የተስተካከለ እንዲሆን የተለያዩ ምግቦችን (የእንስሳት ውጤቶች/ሥጋ፣ ወተት እና የወተት ተዋጽኦዎች፣ እንቁላል፣ ጉበት፣ኩላሊት፣ዓሣ፣ዘይት ወዘተ/ፍራፍሬዎች እና አትክልት/ፓፓያና ማንጎ፣ ብርቱካን፣ ካሮት፣ዱባ፣ ሙዝ፣ አቮካዶ፣ስኳር ድንች፣አተር ፣ምስር፣ባቄላ፣ሽምብራ፣ገብስ፣ስንዴ፣ጤፍ፣ቆጮ ወ.ዘ.ተ) መመገብ እንዳለባቸው ምክር መስጠት። እንዲሁም ወትሮ ከሚመገቡት ሁለት ጊዜ በተጨማሪ መብላት እንደሚኖርባቸው ማድረግ
    - ✓ ባሎችና ሴሎች የቤተሰቡ አባላት ለሚያጠቡ እናቶች ሲያደርጉላቸው ስለሚገባ እገዛ ምክክር ማድረግ
    - ✓ ለሁሉም የሚያጠቡ እናቶች የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታ ልየታ ማድረግ እንደየሁኔታውም ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ

5.4. የህፃናት የስርዓተ-ምግብ ማሻሻል

የሕጻናት የሰውነትና የአንጐል ዕድገት እንዲሁም ጤናማነት በእርግዝና ወቅት በመጀመሪያዎቹ አንድ ሺህ ቀናት ማለትም በእናቲቱ የአመጋገብና ጤና ሁኔታ፤ ከተወለዱ በኋላም እስከ ሁለት ዓመት ድረስ በሚያገኙት ምግብና እንክብካቤ ይወሰናል። ስለሆነም እድሜያቸው ከሁለት አመት በታች ያሉ ህጻናት ላይ ትኩረት በማድረግ የጤና ኬላ ባለሙያዎች የሚከተሉቱን ተግባራት ያከናውናሉ

- ❖ በጎጥ ጤና መሪዎችና በልማት ቡድን መሪዎች በመታገዝ በቀበሌዋ የሚገኙትን ከሁለት አመት በታች ያሉ ህጻናትን ለይተው መያዝ
- ❖ በጎጥ ጤና መሪዎችና በልማት ቡድን መሪዎች በመታገዝ ወርሃዊ የእድገት ክትትል እና ማጎልበት ክፍለ ጊዜዎችን ማካሄድ እንደየእድገት ደረጃቸውም የምክር አገልግሎት መስጠት
    - ✓ ህጻናት እንደተወለዱ የመጀመሪያውን የጡት ወተት እንዲያገኙ መምከር
    - ✓ ትክክለኛ የህጻን አስተቃቀፍና የጡት አጎራረስ ለእናቶች ማሳየት
    - ✓ ህፃናት መጥባት በፈለጉ ጊዜ (ቀንና ሌሊትን ጨምሮ) የእናት ጡት ማግኘት እንዳለባቸው ማስተማር

- ✓ በአካባቢው የተለመዱ ጎጂ የህጻናት አመጋገብ ልማዶችን ለዩቶ አስፈላጊውን ትምህርት እና ውይይት ማድረግ፤ በጎጥ ጤና መሪዎችና በልማት ቡድን መሪዎች በመታገዝ ክትትልና ድጋፍ መስጠት
- ✓ ሁሉም ህጻናት ለመጀመሪያዎቹ 6 ወራት የእናት ጡት ብቻ እንዲጠቡ መምከር፤ በተለያዩ ምክንያት የእናት ጡት ማጥባት ሳልቻሉ ህጻናት የላም ወተት ወይም የቆርቆሮ ወተት እንዲወስዱ አስፈላጊውን እገዛና ክትትል ማድረግ
- ✓ እናቶች ህጻናት ልጆቻቸው ቢያንስ 2 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ጡት ማጥባት እንዲቀጥሉ ማበረታታትና አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ

❖ እድሜአቸው 6 ወር ለሞላቸው ህጻናት ለእድገታቸው አስፈላጊውን የሆነ ንጥረ ነገር በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ ለማድረግ ከእናት ጡት በተጨማሪ የተመጣጠነ ተጨማሪ ምግብ መስጠት እንደሚያስፈልግ መምከር

❖ ሕጻናት በቀን ውስጥ መመገብ ያለባቸው ምን ያህል እና ስንት ጊዜ እንደሆነ ማስረዳት

❖ የተመጣጠነ ተጨማሪ ምግብ አዘገጃጀት ለእናቶች፣ ለጎጥ ጤና መሪዎችና ለልማት ቡድን መሪዎች ሰርቶ ማሳየት

❖ ሁሉም 6 ወር የሞላቸው ህጻናት በመመሪያው መሰረት ቫይታሚን ኤ ማደል፤ አምስት ዓመት እስኪሞላቸውም በየ6ወሩ ቫይታሚን ኤ መስጠት

❖ ሁለት ዓመት የሞላቸው ህጻናት በሙሉ የአንጀት ጥገኛ ትላትል ህክምና መድኃኒት (Albendazole) ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤ እስከ 5 ዓመትም በየስድስት ወሩ መስጠት

❖ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት አመት የሞላቸው ህጻናት የአንጀት ጥገኛ ትላትል ህክምና መድኃኒት (ግማሽ 400 Albendazole ወይም 500 m.g Mebendazole) በየስድስት ወሩ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ

❖ ለሕፃናቱ በሚዘጋጅ ተጨማሪ ምግብ ውስጥ በአዮዲን የበለጸገ ጨው መጨመር በጣም አስፈላጊ መሆኑን ማስተማርና አጠቃቀሙንም መከታተል

❖ ከጡትና ከጡት ማጥባት ጋር የተያያዙ ችግሮች ላላቸው እናቶች አስፈላጊውን እንክብካቤ እና ህክምና ማድረግና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ ጤና ጣቢያ መላክ

❖ እናቶች የታመሙ ህጻናትን እንዴት መመገብ እንዳለባቸው መምከር

5.5. የወጣቶች ስርዓተ-ምግብ ማሻሻል

❖ እድሜያቸው ከ10 እስከ 19 አመት ለሆኑ ወጣቶች የስርአተ ምግብ ሁኔታ ልኬት በየሶስት ወራት አንድ ጊዜ በጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ሌሎች የማህበረሰብ ተቋማት አገልግሎቱን መስጠት። የስራዓተ-ምግብ አቋማቸውን መሰረት በማድረግ፣ ጤናማና የተመጣጠነ አመጋገብ ላይ ምክክርና ድጋፍ ማድረግ፤ ወጣቶች እድሜያቸውና ቁመታቸውን የማከለ ክብደት እንዲኖራቸው ጤናማ አመጋገብና አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ከወጣቶችና አሳዳጊዎቻቸው ጋራ ምክክር ማድረግ

❖ አጣዳፊ ምግብ እጥረት ልየታ የምክክርና ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፤ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን ወጣቶች በመለየት የምግብ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ

❖ የወጣት ሴቶችን የአመጋገብ ሥርዓት የሚያሻሽሉ የምክር አገልግሎቶች በቤተሰብ፣በማህበረሰብ ፣በትምህርት ቤትና በጤና ተቋማት ደረጃ መስጠት

❖ ወጣት ሴቶች ተጨማሪ ጥቃቅን ንጥረ-ምግቦች (የቫይታሚን እና የማዕድን) አገልግሎት ማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ

✓ በአዮዲን የበለፀገ ጨው ተጠቃሚነትን ማበረታታት

✓ የአንጀት ጥገኛ ትላትል ህክምና መድሃኒቶችን በዓመት ሁለት ጊዜ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ማሰራጨት

❖ በማህበረሰብና ትምህርት ቤቶች፡ የሚገኙ ወጣት ልጃገረዶችን በመለየት፡ የአይረን ፎሌት እደላ ማካሄድ (60 ሚግ አይረን እና 2.8 ሚግ ፎሊክ አሲድ)። አደላውም በሳምንት አንድ ጊዜ ለሶስት ተከታታይ ወራት በመስጠት በቀጣዩ ሶስት ወራት በማሰረፍ ቀጥሎ ለ3 ወራት በሳምንት አንድ ጊዜ መስጠት፤በአጠቃላዩ በአመት ሁለት ጊዜ ለስድስት ወራት መስጠት

❖ የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች መከላከየ 400 ሚግ አልቤንዳዞል ወይም 500 ሚግ ሜቤንዳዞል ክኒን ለወጣቶች በየ6 ወራት (በአመት ሁለት ጊዜ) መስጠት።

❖ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል የባህሪ ለውጥ ተግባቦቶችን (መስተጋብርን) መተግበር

✓ ሴት ልጆች የለአድሜ ጋብቻን እንዳይፈፅሙ እንዲሁም ከጋብቻ በኋላ ወሊድን ለማዘግየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አብሮ መስራት

✓ ወጣት ሴቶች በበቂ ሁኔታ እንዳይመገቡ የሚከለክሉ ልማዳዊ አመለካከቶች (food taboos) ለማስቀረት ማህበራዊ ልማዶችን፣ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችንና አስተሳሰቦች ላይ የማህበራዊ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ከጎጥ ጤና መሪዎችና ልማት ቡድን ጋር በቅንጅት ትሰራለች

5.6. የጎልማሶችና አዋቂዎች አመጋገብ እንዲሻሻል ማድረግ

❖ ጎልማሶችና አዋቂዎች እንደየአድሜአቸውና የሰውነት እንቅስቃሴአቸው መጠን የተስተካከለ የአመጋገብ ስርዓት እንዲኖራቸው መምከርና እገዛ ማድረግ

5.7. የአረጋውያን ሥርዓተ ምግብ ሁኔታን ማሻሻል

❖ ዕድሜያቸው በጣም የገፋ ሰዎች ብዙ ሥራ ስለማይሰሩ ውስን እንቅስቃሴ ብቻ ስለሚያደርጉ የሚያስፈልጋቸው የኃይልና ሙቀት ሰጪ ንጥረ ምግቦች መጠን ዝቅተኛ ነው። ምግብን በአንጀት ውስጥ እንዲፈጭ የሚያደርጉ ቅመሞች ሰውነታቸው ውስጥ እየቀነሱ ስለሚሄዱ ጨማ፣ ቅባት የመሰሰሉት ምግቦች ማብዛት ተገቢ አለመሆኑን ምክር መስጠት

❖ አረጋውያንና ዕድሜአቸው በጣም የገፋ ሰዎች ከሰውነት ሁኔታቸው ጋር የተስተካከለ አመጋገብ እንዲኖራቸው መምከር

❖ የቤተሰቡ አባላት ለአረጋውያን ማድረግ ስላለባቸው እገዛና ድጋፍ ምክክር መስጠት

5.8. የሕመምተኞች አመጋገብን ማሻሻል

❖ በበሽታ የተጠቃ ሰው ከጤነኛ ሰው የተለየ የአመጋገብ ሥርዓት ቢኖረው እንደሚገባ መምከር

❖ የህመምተኛ አመጋገብ እንደህመሙ ዓይነትና እንደታማሚው ሁኔታ ስለሚለያዩ እንደየሁኔታው ተገቢውን ምክርና ድጋፍ መስጠት

❖ የጤና ኬላ ባለሙያዎች በጤና ኬላም ሆነ በቤት ለቤት ጉብኝት ወቅት ስለ ኤች.አይ.ቪ እና የአመጋገብ ሥርዓት ተገቢውን ምክርና ትምህርት መስጠት ይኸውም በዋናነት የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማተኮር ይኖርበታል፤

- ✓ በመደበኛ የጊዜ ገደብ ክብደታቸውን መለካት እንደሚኖርባቸው መምከርና መከታተል
- ✓ አስፈላጊ የሆነውን ክትትል ማድረግና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአስቸኳይ ወደሚቀጥለው የጤና እርከን ለተጨማሪ ምርመራና ሕክምና መላክ
- ✓ በደማቸው ኤች.አይ.ቪ ለሚገኝ ወገኖች የሚመከረው አመጋገብ ፍራፍሬዎችን፣ አትክልቶችን፣ የእህል ዘሮችን፣ የእንስሳትና ዕጽዋት ተዋጽኦዎችን ያካተተና የተመጣጠነ መሆን እንደሚገባው መምከር ይኖርባታል።

5.9. የጥቃቅን ንጥረ ነገሮች እጥረት ችግሮችን መከላከል እና መቆጣጠር

በጥቃቅን ንጥረ ነገሮች እጥረት ምክንያት ሲከሱ የሚችሉ ችግሮን ለመከላከልና ለመቆጣጠር

- ❖ ከጎጥ ጤና መሪዎችና ከልማት ቡድንና ከሌሎች የማህበረሰብ አደረጃጀቶች ጋር በመተባበር ታሳሚዎችን ማለትም፡-
  - ✓ ከ6 ወር እስከ 5 ዓመት የሚሆናቸው ሕዓናት፣ ነፍሰ-ጡር እና የሚያጠቡ እናቶችን ለዩታ ትመዘግባለች
  - ✓ እድሚያቸው ከ6-59 ወር ለሚሆን ሕዓናት በየስድስት ወሩ ቫዩታሚን ኤ መስጠት (ለዝርዝር አፈጻጸሙ የዘመቻ፣ የማሕበረሰብ ጤና ቀን እና መደበኛ ፈጣን ማጣቀሻውን ተጠቀሙ።)
- ❖ የቫዩታሚን ኤ እና የአንጀት ጥገኛ ትላትል መድሃኒት እንክብል ከሥርዓተ-ምግብ ሁኔታ ልየታ ጋር ተቀናጅቶ በሚከተሉት 3 የትግበራ መንገዶች ሲካሄድ ይችላል
  - ✓ በዘመቻ በየስድስት ወሩ
  - ✓ በማህበረሰብ ጤና ቀን (በየ3 ወር የሚደረግ የሥርዓተ ምግብ ሁኔታ ልየታ እንዲሁም በየ6 ወሩ የቫዩታሚን ኤ እና የአንጀት ጥገኛ ትላትል መድሃኒት እንክብል እደላ)
  - ✓ በመደበኛና በውሉገብ መርሐግብር

የቫይታሚን ኤ ዕደላ

ሰንጠረዥ 1: የቫይታሚን ኤ እደላ መጠንና ፕሮግራም

ቫይታሚን ኤ ዕደላ (ለበሽታመከላከል የተዘጋጀ ፕሮቶኮል)		
ዕድሜ	**መጠን**	**የድግግሞሹ ሁኔታ**
ከ6-11ወራት እድሜ ባላቸው ሕዓናት	የ100,000አዩ (1 እንክብል)	አንድ ጊዜ
ከ12-59 ወራት እድሜ ባላቸው ሕዓናት	የ200,000አዩ (2 እንክብል)	በ6 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ አንዴ
በኩፍኝ ለተጎዱ ህጻናት በቫይታሚን ኤ መስጠት		
የቫዩታሚን ኤ ተቀባዮች (targets)	መጠን (dosage IU)	ድግግሞሽ (frequency)
ከ6 - 11 ወራት ለሆኑ ሕጻናት	100,000	በመጀመሪያ ከጤና ባለሙያዋ ጋር ሲገናኝ መሠጠት ከዚያም በመመሪያው መሠረት የሚቀጥል ይሆናል።
ከ12 - 59 ወራት ለሆኑ ሕጻናት	200,000	በመጀመሪያ ከጤና ባለሙያዋ ጋር ሲገናኝ መሠጠት ከዚያም በመመሪያው መሠረት የሚቀጥል ይሆናል።

ዜሮፍታልሚያ ወይም ኩፍኝ ለያዛቸው ልጆች		
መርሐ ግብሩ (schedule)	**መጠን ከአንድ ዓመት በታች ለሆኑ ሕጻናት (dosage IU)**	**መጠን ከአንድ ዓመት በላይ ለሆኑ ሕጻናት (dosage IU)**
በምርመራ ወቅት ወዲያውኑ	100,000	200,000
በቀጣዩ ቀን	100,000	200,000
ከ15 ቀናት በኋላ	100,000	200,000

የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች መድሃኒት እደላ (deworming)

- ❖ እድሜያቸው ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት ለሚሆን ሕዓናት የፀረ ትሳትል መድኃኒት መስጠት
- ❖ ሶስት ወር ሳለፋቸው ነፍሰ ጡር እናቶች የአንጀት ጥገኛ ትሳትል መድሃኒት መስጠት

ሰንጠረዥ 2፡ የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች መድኀኒት ታላሚዎች፣ መጠንና የጊዜ ገደብ

ምድብ	ሕክምና	ጊዜ
ነፍሰጡር ሴቶችና የሚያጠቡ እናቶች	500 ሚ.ግ. ሜቤንዳዞል በአንድ ጊዜ	በመጨረሻዎቹ የእርግዝና ወራት (third trimester)
ከ1 ዓመት አእስከ 2 አመት ዕድሜ ያሳቸው ሕጻናት	ግማሽ 400 ሚግ (200 ሚግ) Albenda-zole ወይም 500 ሚግ Mebendazole	በየስድስት ወሩ
ከ2 ዓመት በሳዩ ዕድሜ ያሳቸው ሕጻናት	500 ሚ.ግ. ሜቤንዳዞል ወይም 400 ሚግ አልቤንዳዞል በአንድ ጊዜ	በየስድስት ወሩ
ለወጣቶች (10 እስከ 19 አመት)	500 ሚ.ግ. ሜቤንዳዞል ወይም 400 ሚግ አልቤንዳዞል በአንድ ጊዜ	በየስድስት ወሩ

የአይረን ፎሌት እንክብል እደላ

- ❖ ለነፍሰጡርና ለሚያጠቡ እናቶች የአዩረን ፎሴት አንክብል መስጠት
- ❖ ትክክለኛ አወሳሰዱን ከጎጥ ጤና መሪዎችና ከልማት ቡድን መሪዎች ጋር በመተባበር ክትትልና አገዛ ማድረግ

ሰንጠረዥ 3፡ ለነፍሰጡሮችና ለሚያጠቡ እናቶች የሚሰጥ የአይረን ፎሌት መጠንና የጊዜ ገደብ

ምድብ	አይረን-ፎሌት መጠን	የጊዜ ገደብ
ነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች	አዩረን =60 ሚ.ግ/በቀን ፎሴት = 400 ማዩ.ግ/በቀን	በእርግዝና ወቅት ስድስተኛው ወር ሳዩ ደም ማነስ ሥርጭቱ ከ40 በመቶ በታች ሲሆን
		በእርግዝና ወቅት ስድስተኛው ወር ሳዩ እና ከወሊድ በኋሳ ሦስተኛው ወር ሳዩ የደም ማነስ ሥርጭቱ 40 በመቶ እና ከዚያ በሳዩ ሲሆን
		አንዳት ሴት በእርግዝና ወቅት ስድስተኛው ወር ሳዩ መውሰድ ካልቻለች ከወሊድ በኋሳ መሠጠት ወይም መጠኑን ወደ 102 ሚ.ግ/በቀን ማሳደግ ይቻሳል።

አዮዲን

- ❖ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ለምግብነት የሚጠቀመው ጨው በአዮዲን የበለጸገ መሆኑን ማረጋጥ
- ❖ የአዮዲን መመርመሪያ ኪት በመጠቀም ገበያ ላይ ለሰው ምግብነት የሚውለው ጨው በአዮዲን የበለጸገ መሆኑን በምርመራ ማረጋገጥ

5.10. የእድገት ክትትልና ማበልፀግ

- ❖ ከጎጥ ጤና መሪዎችና ከልማት ቡድን መሪዎች ጋር በመሆን ታሳሚዎቹን መለየት

✓ *ታላሚዎቹ ከልደት እስከ 2 ዓመት እድሜ ያላቸው ሕፃናት ናቸው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ይህ እድሜ ከፍተኛ የሆነ የአካላዊና አእምሮአዊ እድገት የሚጎለበትበት ወቅት ስለሆነ እና ከ2 ዓመት እድሜ በፊት የሚከሰቱ ችግሮችን የሕፃኑ እድሜ 2 ዓመት ከሞላ በኋላ ለመቀልበስ ስለማይቻል ነው፡፡*

- ❖ ሦስቱን የ"መ" ኡደት (መረጃ መሰብሰብ፣ መተንተንና መተግበር) / Triple A cycle (Assesment Anaylsis Action) መተግበር
- ❖ በየወሩ በመደበኛነት ክብደት መመዘን
- ❖ የልጆችን እድገት ሴሎች የእድሜ አቻዎቻቸው ከሚገኙበት እድገት ደረጃና ከበፊተኛው ክብደት ጋር ማወዳደር እና የልጁን እድገት ፍጥነት መወሰን
- ❖ የእድገት ሁኔታ፣ የእድገት መጓደል መንስዔዎችንና ሊወሰዱ የሚገባቸውን መፍትሔዎች መለየት
- ❖ ከላይ በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሠረት የልጁን የዕድገት ሁኔታ ከመዘኑና ከተነተኑ በኋላ በሚገኘው ውጤት መሠረት መወሰድ ያለበት እርምጃ፡
    - ✓ ጥሩ የዕድገት ደረጃ = ማበረታታት
    - ✓ እየቀነሰ ያለ የዕድገት ደረጃ = በችግሩ ላይ መመካከር
    - ✓ የቆመ የዕድገት ደረጃ = በችግሩ ላይ መመካከር
    - ✓ ከወረደበት የሚጨምር የዕድገት ደረጃ = ማበረታታት

<u>ለምሳሌ</u> በታች የተቀመጡ ከአንድ እስከ አራት ያሉት ስእል ተመልከቱ

ማስታወሻ፡ የምክክር ሥርዓቱ የGALIDRAA ሂደትን በተከተለ መልኩ ሲከናወን እንደሚገባ ዘወትር ማስታወስ በጣም ይጠቅማል፡፡



ስእል 1:- ክብደት አልጨመረም/ችም



ስእል 2:- ክብደት ቀንሷል/ሳለች



ስእል 3 በቂ ያልሆነ ክብደት መጨመር



ስእል 4 በቂ ክብደት መጨመር

5.11. የስርዓተ-ምግብ እጥረትን በምርመራ መለየት

ሥርዓተ-ምግብ መጓደል ምክንያት የሚከሰቱ ክሊኒካዊ የሆኑ ምልክቶችን በመመልከት የሥርዓተ-ምግብ መጓደሎችን መለየት ይቻላል፤ ይህም ህመምተኛውን በመጠየቅ እና/ወይም በማየት ሊከናወን ይችላል።

ምልክቶች/ስሜቶች	የሥርዓተ-ምግብ መጓደሎች
✓ መገርጣት፡ የመዳፍ፣ የዐይን ሽፋል ውስጥ፣ ምላስ ✓ በቀላሉ የመዛል፣ የምግብ ፍሰጎት ማጣት፣ የትንፋሽ ማጠር	✓ ደም ማነስ፡ ይህም በአይረን፣ በፎሊክ፣ በቫይታሚን ቢ12፣ በአሲድ፣ ኮፐር፣ ፕሮቲን ወይም ቫይታሚን ቢ6 እጥረት ሊከሰት ይችላል።
✓ ቢቶትስ ስፖት (በዐይን ነጩ ክፍል ሦስት ማዕዘናዊ የሆኑ ነጫጭ ዐረፋማ ነገሮች መታየት)	✓ የቫይታሚን ኤ እጥረት
✓ እንቅርት (በአንገት ላይ የሚታይ እብጠት)	✓ የአዮዲን እጥረት
✓ የጥርስ መበስበስና መቦርቦር	✓ የፍሎራይድ እጥረት ወይም የሚጨምር ሃይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች አመውሰድ ወይም የአፍ ውስጥ pH ከአስፈላጊ በታች መሆን (ይህም ማለት ከ5.5 በታች ማለት ነው።) ይህንንም ተከትሎ የጥርስ ሽፋን መሟሟትን ያስከትላል።
✓ የሚጨምር የጥርስ በመለዝ፣ የሚጨምር የአጥንትና የጥርስ መለስለስ/መሰበር	✓ በጣም የበዛ ፍሎራይድ
✓ በሁለቱም እግሮች የሚሰረጉድ እብጠት ሲኖር	✓ አደገኛና አጣዳፊ የሥነ ምግብ መጓደል
✓ በግልጽ የሚታይ አደገኛ ክሳት	✓ አደገኛና አጣዳፊ የሥነ ምግብ መጓደል

5.11.1. የአንትሮፖሜትሪ ልኬት

ክብደት፣ የላይኛው ክንድ ዙሪያ ልኬት፣ ቁመት ወዘተ. በመለካትና ወደ አመልካቾች /indicators/ በመቀየር ወይም በማስላት የሚገኝ የሥርዓተ ምግብ ይዘት መረጃ ነው።

ክብደት መለካት

የሕፃናትን የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታና የእድገት አቅጣጫ በትክክል ለመለየት የሕፃኑን ክብደት በትክክል ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

የሚንጠለጠል ሚዛን/salter scale/

የሕፃናትን ክብደት በትክክል ለመለካት የሚከተሉትን ቅደም ተከተል መከተል ያስፈልጋል፡፡

- ደረጃ 1፤ ሚዛኑን 25 ኪ.ግ መያዝ የሚችል ማንጠልጠያ ላይ ይስቀሉት።
- ደረጃ 2፤ የመመዘኛ ቀርጫቱን ሚዛኑ ላይ ያንጠልጥሉ የሚዛኑ ንባብ ዜሮ ላይ እንዲሆን ያስተካክሉ።
- ደረጃ 3፤ ሕፃኑ የለበሰው ልብስ ወፍራም ከሆነ ያስወልቁ። የሕፃኑን ክብደት ለመጨመር የሚችል ልብስ መውለቅ አለበት።
- ደረጃ 4፤ ሕፃኑን የመመዘኛ ቀርጫቱ ላይ ያስቀምጡ።
- ደረጃ 5፤ የሚዛኑ የክብደት አመልካች መርፌ እስኪቆም ድረስ ይጠብቁ። የሕፃኑን ክብደት ሳያጠጋጉ ያንብቡ። ለምሳሌ 4.7 ከሆነ ወደ 4.5 ወይም 5 መጠጋጋት የለበዎትም።
- ደረጃ 6፤ ለእናትየዋ የሕፃኑን ክብደት ይንገሯት።
- ደረጃ 7፤ የሕፃኑን ክብደት በዕድገት ክትትልና ማጎልበቻ መዝገብ ላይ ይመዝግቡ።

በድጅታል ሚዛን

- የሕፃናትን ክብደት በትክክል ለመለካት የሚከተሉትን ቅደም ተከተል መከተል ያስፈልጋል፡፡
- ደረጃ 1፤ ሚዛኑ ደልዳላ/flat surface/ ቦታ ላይ አስተካክሎ ማስቀመጥ ።
- ደረጃ 2፤ የሚዛኑ ንባብ ዜሮ ላይ እንዲሆን ያስተካክሉ።
- ደረጃ 3፤ ሕፃኑ የለበሰው ልብስ ወፍራም ከሆነ ያስወልቁ። የሕፃኑን ክብደት ለመጨመር የሚችል ልብስ መውለቅ አለበት።
- ደረጃ 4፤ ሕፃኑ ራሱን ችሎ የሚቆም ከሆነ ሚዛኑ ላይ በማቆም ክብደቱን ይለኩት
- ደረጃ 5፤ የሚዛኑ የክብደት አመልካች መርፌ እስኪቆም ድረስ ይጠብቁ። የሕፃኑን ክብደት ሳያጠጋጉ ያንብቡ። ለምሳሌ 4.7 ከሆነ ወደ 4.5 ወይም 5 መጠጋጋት የለበትም።
- ደረጃ 6፤ ሕፃኑ ራሱን ችሎ የማይቆም ከሆነ ከእናትየዋ/ተከባካቢ ጋር በማድረግ ክብደቱን ይለኩ።
- ደረጃ 7፤ የእናትየዋ/ተከባካቢ ክብደት ለብቻ ይለኩና ከመጀመሪያ የለኩት ክብደት በመቀነስ የሕፃኑ ክብደት ይወቁ
- የሕፃኑን ክብደት በዕድገት ክትትልና ማጎልበቻ መዝገብ ላይ ይመዝግቡ።

የላይኛው ክንድ እኩሌታ መጠነ ዙሪያ(MUAC) መለካት

- ሲለኩ በሕፃኑ አይን ትይዩ ይሁኑ፤ ከተቻለ ይቀመጡ፤ በዚህ ወቅት በጣም ጨቅላ የሆኑ ሕፃናት በእናታቸው ቢያዙ ይችላሉ። የልጁን የግራ ክንድ በልብስ ተሸፍኖ ከሆነ ልብሱን እናትየዋ እንድታወልቅ ያድርጉ።

❖ የሕፃኑን ክንድ ዘና አድርጎ ወደ ታች በመልቀቅ ከመሀል ተነስቶ ቴፑን በክንዱ ዙርያ ይጠቅልሉ። ቁጥሮቹ ከቀኝ ጎን ወደ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

❖ በሕፃኑ ክንድ ላይ የመለኪያውን ቴፕ ይቆጣጠሩ፣ በትክክለኛው አቀጣጫ ላይ መሆኑን ያረጋግጡ፤

❖ መለኪያው በጣም መጥበቅ ወይም በጣም መላላት የለበትም። አስፈላጊ ሲሆን ማንኛውም ደረጃ ይድገሙ።

❖ መለኪያው በክንድ ላይ በትክክለኛው አቅጣጫና ቦታ ላይ ከሆነ መለኪያውን ወደ 0.1 ሴ.ሜ የቀረበውን ያንብቡ።

❖ ወዳያውኑ ያነበቡትን መጠን ይመዝገቡ።የዘመቻ EOS /የማህበረሰብ ጤና ቀን እና የመደበኛ የቫይታሚን ኤ እና የአንጀት ጥገኛ ትላትል መድሃኒት አደላና የስርዓተምግብ ልየታ ፈጣን ማጣቀሻ ተጠቀሙ

ለሕጻናት የላይኛው ክንድ እኩሌታ መጠነ ዙሪያ (MUAC) ልየታ

የሥርዓተ-ምግብ መጓደል ደረጃ	የሥርዓተ-ምግብ መጓደል ደረጃ ትርጉም	የ MUAC ቴፕ ቀለም
MUAC > 12.5 ሴሜ	በቂ የሆነ ምግብ ሁኔታ	አረንጓዴ
MUAC 11.5-12.5 ሴሜ	መካከለኛ የምግብ እጠረት	ቢጫ
MUAC < 11.5 ሴሜ	ከፍተኛ የምግብ እጠረት	ቀይ
ክብደት ለእርዝመት/ቁመት/WHZ/ ልኬት		
≥-2z-score	በቂ የሆነ ምግብ ሁኔታ	
- 3 to <-2 z scores	መካከለኛ የምግብ እጠረት	
<-3zs-score	ከፍተኛ የምግብ እጠረት	

ለነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች የላይኛው ክንድ እኩሌታ መጠነ ዙሪያ (MUAC) ልየታ

የሥርዓተ-ምግብ መጓደል ደረጃ	የሥርዓተ-ምግብ መጓደል ደረጃ ትርጉም
የላይኛው የክንድ እኩሌታ አማካዩ ዙሪያ ልኬት (MUAC) ≥ 23 cm	በቂ የሆነ ምግብ ሁኔታ
የላይኛው የክንድ እኩሌታ አማካዩ ዙሪያ ልኬት (MUAC) < 23 cm	በጣም የተጐዳ

5.11.2. የታችኛው እግር እብጠትን ማረጋገጥ

❖ ለሦስት ሰከንድ በሁለቱም እግሮች ላይ በአውራ ጣት መጫን።

❖ በሁለቱም እግሮች ላይ የእብጠት አሻራው ጎድጉዶ ከታየ በሕፃኑ ሰውነት ላይ የሚታዩ እብጠት (Edema) አለበት ማለት ነው።

❖ በሁለት እግሮቻቸው ላይ የሚታዩ እብጠት (Edema) ያለባቸው ሕፃናት ብቻ በምግብ እጥረት የተደጎዱ ስለሆኑ የከፍተኛ ምግብ እጥረት ህክምና ይሰጣቸዋል።

5.12. ከፍተኛ የምግብ እጥረት ህክምና

❖ በየወሩ ከጎጥ ጤና መሪዎችና ከልማት ቡድን መሪዎች ጋር በመሆን የምግብ አለመመጣጠን ችግር ያለባቸው መለየት (በቤት ለቤት ጉብኝት፣ በጤና ኬላ እና በዘመቻ ጊዜ)

❖ ከፍተኛና አጣዳፊ የምግብ እጥረት ያለባቸውን ህጻናት የሚለየት በታችኛው እግሮች እብጠት ወይም የላይኛው የክንድ እኩሴታ አማካዩ ዙሪያ ልኬት ከ11.5 ሴ.ሜ. በታች ከሆነ)

❖ ከፍተኛና አጣዳፊ የምግብ እጥረት የሥርዓተ-ምግብ በተመላላሽ ህክምና በprotocol መሰረት አገልግሎት እንዲጀመሩ ማድረግ፤ የተወሳሰበ በጣም ከባድና አጣዳፊ የምግብ እጥረት በሽታ ከሆነ ደግሞ ወደ መመገቢያ የህክምና ማዕከል መላክ (ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል)

❖ ሁሉንም ነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች መለየት

- ✓ በጣም ከባድ የምግብ እጥረት ያለባቸውን ብቻ ለየ (የላይኛው የክንድ አማካዩ ዙሪያ ከ18 ሴ.ሜ. ያነሰ ከሆነ) ለሥርዓተ-ምግብ ተመላላሽ ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ወይም የህክምና ቀጠሮ መያዝ ወይም ወደ መመገቢያ የህክምና ማዕከል መላክ
- ✓ በመካከለኛ ደረጃ /Modertly malnurushed (የላይኛው የክንድ አማካዩ ዙሪያ ከ19-23 ሴ.ሜ. ከሆነ) ስለ አመጋገብ አስፈላጊውን ምክር መስጠት ፣ከተቻለም ወደ ተጨማሪ ምግብ እደላ ፕሮግራም /SFP/ ጋር ማያያዝ

ተጨማሪ ምግብ እደላ ባለባቸው ቦታዎች፡-

❖ ህጻኑ በተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ለመስጠት በታች የተዘረዘሩ ነጥቦች ሲኖረው ነው፤

- ✓ መካከለኛ = የላይኛው የክንድ አማካዩ ዙሪያ ከ11.5-12.5 ሴ.ሜ.እንደዚህ ላሉ ሕፃናት መደረግ ያለበት ስለ ተገቢ የሕፃናት አመጋገብ ለእናት/ተንከባካቢ አስፈላጊውን ምክር መስጠት እንዲሁም የተጨማሪ ምግብ እደላ ራሽንካርድ በመስጠት ወደ ተጨማሪ ምግብ እደላ ፕሮግራም /SFP/ ጋር ማያያዝ፣
- ✓ በጣም ከባድ እብጠት ወይም የላይኛው የክንድ አማካዩ ዙሪያ ከ11.5 ሴ.ሜ. በታች ላሉ ሕፃናት መደረግ ያለበት ለተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ቀጠሮ መስጠት ወይም የተወሳሰበ ከፍተኛና አጣዳፊ የምግብ እጥረት በሽታ ከሆነ ደግሞ ወደ ጤና ጣቢያ/አስተኝቶ ማከም ማዕከል ሪፈር ማድረግ።የሥርዓተ-ምግብ ትምህርት እና ምክር አገልግሎት መስጠት

የጎጥ ጤና መሪዎችና የልማት ቡድን መሪዎች ጋር በመሆን ከታች የተዘረዘሩትን ትምህርት እና ምክር አግልግሎት መስጠት፤ ስለምግብ፣ምግብ ውስጥ የሚገኑ ንጥረ ምግቦች እና ጥቅሞች ለህብረተሰብ ትምህርት መስጠት፤ አካል ገነቢ/ፐሮቲን/፣ሐይል ሰጪ/ካርቦሃይድሬት/፣በሽታ ተከላካይ/ቫይታሚንና ማዕድን/ እና ውሃ የህብረተሰብ ስርዓተ ምግብ እንዲሻሻሉ ትምህርት መስጠት

- *ነፍሰጡር ባለቤትዎ ጤንነታቸውና ጥንካሬያቸው የተጠበቀ እንዲሆን ወትሮ ከሚመገቡት ምግብ አንድ ተጨማሪ ምግብ እንዲመገቡ ያድርጉ። ነፍሰጡር እናቶች የተለያዩ ምግቦችን መመገብ አለባቸው። በተለይም የእንስሳት ውጤቶች /ሥጋ፣ ወተት፣ እንቁላል ወዘተ/ ፍራፍሬዎች እና አትክልት/የበሰሉ ፖፖያና ማንጐ፣ ብርቱኳን፣ ካሮት፣ ዱባ፣ ጉበት/ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው።*

- *ነፍሰጡር ባለቤትዎ ብርቱና ጠንካራ ሆነው እንዲቆዩ አይረን/ፎሌት እንክብል እየወሰዱ መሆኑን ያረጋግጡ።*

- *ነፍሰጡር ባለቤትዎ ሶስት ወር ከሞላቸው በኋላ የአንጀት ትላትል ማጥፊያ እንክብል 500 ሚሊ ግራም መውሰዳቸውን ያረጋግጡ።*

- *ጡት በማጥባት ላይ ያሉ ባለቤትዎ እና የልጅዎ ጤንነት የተስተካከለ እንዲሆን ባለቤትዎ ወትሮ ከሚመገቡት ተጨማሪ ሁለት ምግብ እንዲወስዱ ያድርጉ።*

- *ልጅ እንደተወለደ በመጀመሪያ የሚወጣውን ቢጫ መልክ ያለውን የጡትዎን ወተት /እንገር/አዲስ ለተወለደው ሕፃን ማጥባት ከምግብነቱ በተጨማሪ በሽታ እንዲቋቋም ይረዳዋል።*

- *እናቶች ልጅ እንደተገላገሉ ወዲያውኑ ጡት ማጥባት ይጀምሩ፤የእንግዴ ልጁ እስኪወጣ አይዘግዩ፤ይህም ጡታቸው ቶሎ ወተት እንዲያግት ያደርጋል፣ ጡት ወዲያውኑ በመጀመሪያው አንድ ሰዓት ውስጥ ማጥባት የእንግዴልጁ በቶሎ እንዳወጣ በማድረግ የደም መፍሰስን ይቀንሳል።*

- *ከጡት ወተት በፊት የሚሰጡ እንደውሃ፣ ውሃ በስኳር፣ ቅቤና እርሾ የመሳሰሉ ነገሮች አላስፈላጊ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በመጀመሪያዎቹ ቀኖች መኖር የሚገባውን የጡት ወተት አመጋገብን ያዛባል።*

- *ስድስት ወር እስኪሞላቸው ድረስ ህፃናትን የእናት ጡት ወተት ብቻ ማጥባት ይገባል፤ውሃም ቢሆን አይሰጥም፤ይህ ጠንካራና ጤናማ ልጅ እንዲሆኑ ይረዳል*

- *ህፃናት ጡት መጥባት በፈለጉ ጊዜ ጡት ይጥቡ፤ ቀንናሌሊትን ጨምሮ ከ10-12 ጊዜ ማጥባት ያስፈልጋል፤ይህን ማድረግ ጡት እንዲያግትይረዳል፤ሕፃኑም በቂ ወተት ያገኛል፤የተስተካከለ ዕድገትም ይኖረዋል፤ጤናማም ይሆናል።*

- *ጡት ሲጠባ ሕፃኑን በተገቢው መንገድ መታቀፍ፣ ጡቱን በሚገባ መጉረሱን ማረጋገጥ፣ይህ ሕፃኑ በቂ ወተት እንዲያገኝከማድረጉ በተጨማሪ የጡት ጫፍ መቁሰል መሰነጣጠቅና ሌሎች የጡት ችግሮችንም ያስወግዳል።*

- *ከጡትና ከጡት ጫፍ ጋር የተያያዙ ችግሮች ያላቸው እናቶችበአስቸኳይ የጤና ተቋም መሄድ አለባቸው።*

- *ማጥባት የጀመሩትን አንደኛውን ጡት ወተቱ እስከሚሟጠጥድረስ ማጥባት፣ከዚያም ወደ ሌላውን ጡት ማዞር ይህም ሕፃኑ ከበስተኋላ የሚመጣውን በምግብ የዳበረውን የጡት ወተት ለማግኘት ያስችለዋል።*

- *የእናቲቱና የሕፃኑ ጤንነት የተጠበቀ እንዲሆንጡት የሚያጠቡ እናቶች ከወትሮ በተጨማሪ ሁለት ጊዜ ምግብ እንዲመገቡ ማድረግ።*
  - ✓ *የእንስሳት ውጤቶች /ሥጋ፣ ወተት፣ እንቁላል፣ጉበት ወዘተ*
  - ✓ *የፍራፍሬ አይነቶች /የበሰለ ፓፓያ፣ ብርቱካን፣ ማንጐ ወዘተ*
  - ✓ *የአትክልት አይነቶች /ካሮት፣ ዱባ፣ ጐመን ወዘተ/*
- *ህፃናት ከታመሙ ቶሎ ቶሎ ማጥባት በአጭር ጊዜ እንዲድኑ ይረዳቸዋል፣*
- *ከስድስት እስከ አሥራ ሁለት ወር ያሉ ሕፃናት ዕድገታቸው የተስተካከለ እንዲሆን በቀን ከሁለት እስከ ሶስት ጊዜ ከሚሰጠው በተለያዩ የምግብ አይነቶች ከበለጸገው ገንፎ በተጨማሪ አንዴ ወይም ሁለቴ መክሰስመስጠት ይገባል*
- *በደማቸው ኤች.አይ.ቪ ለሚገኝ ወገኖች በመደበኛ የጊዜ ገደብ ክብደታቸውን መለካት እንደሚኖርባቸው መምከርና መከታተል*
- *በደማቸው ኤች.አይ.ቪ ለሚገኝ ወገኖች የሚመከረው አመጋገብ ፍራፍሬዎችን፣ አትክልቶችን፣ የእህል ዘሮችን፣ የእንስሳትና ዕጽዋት ተዋጽኦዎችን ያካተተና የተመጣጠነ ሊሆን ይገባል።*

<u>የተጨማሪ ምግብ አዘገጃጀት ቁልፍ መልእክቶች</u>

ሀ. በአከባቢ የሚገኑ የምግብ ሰብሎችና ጥራጥሬዎች እንዲሁም አትክልቶች እና ፍራፍሬዎች መለየት
ለ. ምግብ ከመዘጋጀቱ እና ከመመገብ በፊት የእጅ ንጽህና መጠበቅ
ሐ. የተመጣጠነ ምግብ አዘጋጅቶ መመገብ
መ.ትክክለኛ የምግብ አዘገጃጀት ዘዴን ተግባራዊ ማድረግ።
ሠ. በአዮዲን የበለፀገ ጨው መጠቀም

5.13. የሥርዓተ-ምግብ ቅንጅታዊ አሠራር

5.13.1. ከግብርና ሴክተር ጋር የሚሰሩ ተግባራት፣

- በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ተግባራት መካከል፣ የጓሮ አትክልት፣የእንስሳት ተዋፆ ምግቦችን አቅርቦትና ተጠቀሚነት ማሻሻል፣
- ወተትና የወተት ተዋፅኦዎች፣ የአሣ እርባታ እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣
- የንጥረ-ምግብ ይዘታቸው ከፍተኛ የሆኑ ምግቦች አቅርቦትና ተጠቃሚነትን ለማሻሻል እሴት የመጨመር ተግባራትን ማበረታታት፣
- በግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እና የግብር ልማት ባለሙያዎችን በመጠቀም በማህበረሰብ ደረጃ የተለያዩ የምግብ አዩነቶችን (diverisified food) መመገብን ማስተዋወቅ እና ልማድ እንዲዳብር ማበረታት የሚሉት ናቸው።
- በተጨማሪም የሴፍቲኔት ፕሮግራም እና የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ ከሥርዓተ-ምግብ ፕሮግራም ጋር ለማስተሳሰር ሰፊ ሥራ እየተሰራ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

- በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እና በግብርና የልማት ሰራተኞች መካከል ትስስር እና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር በቤተሰብ ደረጃ የአመጋገብ ባህል እና ልማድን ማሻሻል፤

- እናቶችን በልማት ቡድን እና የስራ ማህበራት (cooperatives) በማደራጀት በአካባቢው ተጨማሪ የህፃናት ምግቦች እንዲያመርቱ መደገፍ እና እናቶች ኢኮኖሚያቸውን የሚያጠናክሩበትን የገበ ማስገኛ እድል መፍጠር።

5.13.2. ከትምህርት ሴክተር ጋር የሚሰሩ ተግባራት፣

- በት/ት ቤቶች አካባቢ የሥርዓተ-ምግብ ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ የመምህራን፣የመምህራንና የቤተሰብ ህብረት/ጥምረት እንዲሁም የትምህትር ቤቶች ክበባትን በመጠቀም ቁልፍ የስርዓተ-ምግብ ተግባራትን ለማስተዋወቅና ማበረታታት፣

- ወደ ማህበረሰቡ ሊስፋፉ የሚችሉ የጓሮ አትክልቶችን ማምረት እና መጠቀምን፣የተለየ የጥቃቅን ንጥረ-ምግቦች እጥረትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚተገበሩ ስራዎችን በትምህርት ቤቶች ውስጥ መተግበር።

- ከነዚህም መካከል የአንጀት ጥገኛ ትላትል ህክምና ኪኒን እደላ እና የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ይዘታ ያላቸው ምግቦችን የመጠቀም ልማድ በትምህርት ቤቶች እንዲዳብር ማስተማርና መደገፍ

- በተጨማሪም የንፁህ መጠጥ ውሃ፣ የግል እና አካባቢ ንፅህና አገልግሎቶችን አቅርቦት እና ተደራሽነት በትምህርት ቤቶች ማሻሻል፣

- ተማሪዎችን በመጠቀም ቤተሰብ ውስጥ በአዮዲን የበለጸገ ጨው ተጠቃሚነትን ማስተዋወቅና ማበረታታት እንደሚገባ መረዳት ያስፈልጋል፣

5.13.3. ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር የሚሰሩ ተግባራት

- ስርዓተ-ጾታና ስርዓተ-ምግብ ሲነጣጠሉ የማይችሉ የድህነት ዑደት (አዙሪት) አካል ናቸው።

- የፆታ እኩልነት አለመኖር የረሃብና የምግብ አለመመጣጠን ችግር መንስኤም ውጤትም ሲሆን ይችላል። የጾታ እኩልነትና የሴቶችን አቅም ማጎልበት ወይም ማብቃት የሰው ልማት እና ብልጽግና አንዱ አካል ሲሆን በመላው የህይወት ዑደትም ውስጥ በስርዓተ-ምግብ ላዩ ለውጥ የሚያመጣ ነው።

- ስርዓተ-ጾታና የምግብ አለመመጣጠን ችግር በቤተሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ በህይወት ዘመን በሙሉ ከገበ ምንጭ ዋስትና ጋር ተያያዥና ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው። ይህም ከእርግዝና ጊዜ (በእናት ሆድ ውስጥ እያለ) ጀምሮ በጨቅላነት፣ በልጅነት፣ በጉርምስና፣ በጎልማሳነት እና በእርጅና ዘመን በሙሉ ማለት ነው።

- ሴቶች አብዛኛውን ቤተሰብ ውስጥ ምግብ የማዘጋጀት፣ ማገዶ የመልቀም፣ ውሃ የመቅዳት፣ የታመመን የመንከባከብና የመሳሰሉ ሃላፊነቶችን ከመሸከማቸው እና ካለባቸው ከባድ የስራ ጫና የተነሳ አብዛኛውን ጊዜ ልጆቻቸውንና ራሳቸውን በተገቢ ሁኔታ የሚንከባከቡበት ጊዜ አይኖራቸውም።

- ከዚህ አንፃር ለሴቶች ልዩ ድጋፍ በማድረግ የስርዓተ-ምግብ ሁኔታቸውን ለማሻሻል ሰልጠኞች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፤

5.13.4. ከሥርዓተ-ምግብ ፕሮግራም ተግባሪ ሴክተር መስሪያቤቶች በትብብር መስራት

- ከሌሎች ሴክተር ባለሙያዎች ጋር በአንድነት የሚሰሩ የሥርዓተ-ምግብ ሥራዎችን መለየት፣ማቀድ እና በጋራ መተግበር

- በሥርዓተ-ምግብ የተቀናጀ ፕሮግራም ተጠቃሚ ቤተሰቦችን እና ግለሰቦችን መለየት እና የአገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

- የሥርዓተ-ምግብ ትምህርት በትምህርት ቤት፣ በገበሬዎች ማሰልጠኛ ተቋም፣ በሴፍቲኔት ፕሮግራም፣ በሴቶች ኮንፈረንሶች ወዘተ ማስተማር ይተበቀባቸዋል፣

5.14. አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ፈጣን ማጣቀሻ ለጤና ኬላ ባለሙያዎች-የማህበረሰብ ጤና ቀን ወደ ጤና ኤክስቴንሽን መደበኛ ፕሮግራም ለሚያሸጋግሩ አካባቢዎች
- ማጣቀሻዎች / quck references
- የተመሳሰሽ ህክምና ፕሮቶኮል

የህክምና ቁሳቁሶች

- MUAC ሜትር (የህጻናት)
- MUAC ሜትር (የአዋቂዎች)
- ሚዛን (Digistal)
- የቁመት መለኪያ (Height and Length Board)
- Nutrition Card
- መዝገብ
- ታሊ ሺት
- የተለያዩ ቅጾች
- ዎል ቻርት
- የዕድገት ክትትል ቻርት
- Reference Charts for BMI for Age and WHZ
- የተለያዩ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች
- የተለያዩ የጽሕፈት መሣሪያዎች
- የቤተሰብ ጤና ካርድ
- ቫይታሚን ኤ መቀስ
- Maternal Weight Gain Monitoring Chart
- VAS Monitoring Chart

የተለያዩ አስፈላጊ መድኀኒቶች

- ❖ ቫይታሚን ኤ ካፕሱል
- ❖ ብረት (አይረን)
- ❖ አዮዳን
- ❖ ሜቤንዳዞል
- ❖ አለቤንዳዞል
- ❖ ዚንክ
- ❖ ካልሲየም
- ❖ ፕላምፒነት
- ❖ አይረን ፎሌት
- ❖ ፎሊክአሲድ
- ❖ CSB++
- ❖ Plumpysup
- ❖ Amoxaciline

5.15. የሚጠበቁ ውጤቶች

ለስርዓተ-ምግብ አገልግሎት ማስፈፀሚያ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ሥራ ላይ ሲውል፡-

1. የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ስለሥርዓተ-ምግብ ምንነትና አስፈላጊነት ግንዛቤያቸው ከፍ ይላል፣ የተለያዩ ምግቦችን የማዘጋጀት ክህሎታቸው ይዳብራል፣
2. የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታ ልኬት ይከናወናል፤ በዚህም የሥነ ምግብ ሁኔታቸውን አውቀው አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ የሚወስዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር ይጨምራል፣
3. በኅብረተሰቡ ዘንድ የተመጣጠነ ምግብ አዘጋጅቶ የመመገብ ፍላጎትና ተግባር ይጨምራል፤በዚህም ምክንየት በተመጣጠነ ምግብ እጥረት በሽታ የሚጠቃው ሕዝብ ቁጥር ይቀንሣል፣
4. አዲስ የሚወለዱ ልጆች በወሊድ ወቅት የሚኖራቸው ክብደት ጤናማ ይሆናል፡፡
5. ለሕጻናት የእናት ጡት ወተት ብቻ በመጀመሪያው ስድስት ወር የሚሰጡ እናቶች ቁጥር ይጨምራል፡፡
6. ለሕፃናት ተጨማሪ ምግብ የመስጠት ልምድ ይዳብራል፤በውጤቱም በምግብ እጥረት በሽታ የሚሰቃዩትና የሚሞቱት ሕፃናት ቁጥር ይቀንሳል፣
7. በቫይታሚንና ማዕድናት እጥረት ለሚከሰቱ በሽታዎች በቀላሉ የሚጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም በዚህ በሽታ የሚጠቁ የእናቶችና የሕፃናት ቁጥር ይቀንሣል፣
8. በአዮዳን የበለጸገ ጨው የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ብዛት ይጨምራል፣
9. ለተጨማሪ ሕክምና ወደ ቀጣዩ የጤና እርከን የተላኩ ሰዎች ቁጥር ይጨምራል/ይቀንሳል፣

5.16. ክትትልና ግምገማ

5.16.1. ክትትል

- ቤተሰቡ ምግብን በተመጣጠነ መልኩ እያዘጋጀ መመገቡን፣
- ልጆች፣ ነፍሰጡሮችና የሚያጠቡ እናቶች የፀረ ጥገኛ ትላትል ሕክምና፣ ቫይታሚን ኤ እና አዮረን ፎሌት ማግኘታቸውን፣
- የህብረተሰቡ አካላት ስለሥነ ምግብ ምንነትና አስፈላጊነት ያላቸውን ግንዛቤ፣ (ግንዛቤአቸው መጨመሩን)
- የህብረተሰቡ ልዩ ልዩ የተመጣጠኑ ምግቦችን የማዘጋጀት ክህሎት መዳበሩን፣
- የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታ ልኬት መከናወኑን፤ በዚህም የሥነ ምግብ ሁኔታ ልኬት ውጤት መሠረት አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን፣
- ወላድ እናቶች ለጨቅላው የእናት ጡት ወተት ብቻ በመጀመሪያው ስድስት ወር እየሰጡ መሆናቸውን፣
- ዕድሜአቸው ከስድስት ወር በላይ የሆኑ ሕፃናት ተጨማሪ ምግብ እያገኑ መሆናቸውን፣
- ቤተሰቦች በአዮዲን የበለጸገ ጨው እየተጠቀሙ መሆኑን፣
- ለተጨማሪ ሕክምና ወደ ቀጣዩ የጤና እርከን የተላኩ ቤተሰቦች ተገቢውን እርዳታ ማግኘታቸውንና የታዘዙትን እየፈጸሙ መሆናቸው፣

5.16.2. ግምገማ

- የፕሮግራሙ አጠቃላዩና ዝርዝር ዓላማዎች መሳካታቸውን ማረጋገጥ
- ዓላማዎቹን ለማሣካት የተዘጋጀ ዝርዝር ዕቅዶች መፈጸማቸውን መከታተል
    - ✓ ዕቅዶቹን ለማስፈፀም የዋሉ ግብአቶችን መለየት
    - ✓ የሰው ሐይል /ብዛትና የሙያ አይነት/
    - ✓ የማቴሪያል /በአካባቢ የሚገኙ ቁሣቁሶችና ድጎማዎች/
    - ✓ የገንዘብ መጠን /ከህዝብና ከእርዳታ/ የተገኘ
- የግምገማ ማስፈፀሚያ ስልቶች
    - ✓ የሞኒተሪነግ ቻርት/Vitamin A and De-worming
    - ✓ በመስክ በመዘዋወር
    - ✓ ሪፓርቶችን በማሰባሰብና በመተንተን
    - ✓ ተገልጋዮችን በማነጋገር
- የተከናወኑ ተግባራት
    - ✓ የሽፋን መለኪያዎች በመጠቀም /በፐርሰንት፣ በቁጥር፣ በሬሺኦ/

- የተገኙ ደካማ ጎኖች
- የተከናወኑ ተግባራት በህብረተሰቡ ጤና ላዩ የመጣው ለውጥ
- ያጋጠሙ ትግሮችና ትግሮቹን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች

5.17. የፕሮግራም ጠቋሚዎች

- የቅደመ ውሊድ አገልግሎት ያገኑ ሴቶች ብዛት
- የክብድት መጠመር ክትትልና ምክከር የተደረገባቸው ነፍሰጡር እናቶች ብዛት
- አዩረን ፎሌት (ቢያንስ 90+) የውሰዱ ነፍሰጡር እናቶች ብዛት
- የስርአተ ምግብ ልየታ ያገኑ ወጣቶች ብዛት
- የአንጀት ጥገኛ ትላትል ህክምና ያገኑ ውጣቶች ብዛት
- አዩረን ፎሌት ያገኑ ውጣት ሴቶች ብዛት
- ስለ ሥርዓተ-ምግብ ትምህርት ያገኑ ሰዎች ብዛት (በፆታ)
- ለስድስት ወራት የእናት ጡት ወተት ብቻ የሚሰጡ እናቶች ቁጥር
- ለሕዓናት በተገቢው ጊዜ ተጨማሪ ምግብ የመስጠት ልምድ ያዳበሩ ቤተሰቦች ብዛት፣
- በአዮዳን የበለጸገ ጨው የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ብዛት፣
- ቫይታሚን ኤ የተሰጣቸው ሕጻናት፣ የሚያጠቡ እናቶች ብዛት፣
- አዩረን ፎሌት የተሰጣቸው ሕጻናት፣ ነፍሰጡሮችና ለሚያጠቡ እናቶች ብዛት፣
- የፀረ ጥገኛ ትላትሎች አደላ ያገኑ ሕጻናት እና ነፍሰጡሮች ብዛት፣
- የዚንክ እንክብል የተሰጣቸው በውሃ ተቅማጥ የታመሙ ሕዓናት
- የእድገት ክትትል የተደረገባቸው እድሜያቸው ከ2 አመት በታች የሆኑ ህዓናት ብዛት
- የሥርዓተ-ምግብ ሁኔታ ልኬት የተደረገባቸው ሕጻናት ብዛት፣
- አጣዳፊ በከፍተኛ የምግብ አለመመጣጠን የተጎዱ፣የሚታከሙ (Cured, death, defaulter and transfer)
- አጣዳፊና መካከለኛ የምግብ እጥረት የተጎዱ፣የሚታከሙ ህዓናት (Cured, death, defaulter and transfer)
- አጣዳፊና መካከለኛ የምግብ እጥረት የተጎዱ፣የታከሙ ነፍስጡርና የሚያጥቡ እናቶች (Cured, death, defaulter and transfer)
- በወሊድ ወቅት ጤናማ ክብደት የሚኖራቸው አዲስ የሚወለዱ ልጆች ብዛት፣
- ተላላፊና የማይተላለፉ በሽታዎቻ ያሉባቸውና የስርዓተ-ምግብ ልየታና ምክከር የተደረገባቸው ብዛት
- ዘርፈ ብዙ የምግብና የስርአተ ምግብ የቀብሴ ቴ/ኮሚቴ የተደረጉ ስብሰባዎችና የተወሰኑ ውሳኔዎች

በአጠቃላይና መሰረታዊ ጤና ኬላዎች የሚተገበሩ የእናቶች፣ ህጻናት፣ አፍላ ወጣቶች ጤና እና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች ማኑዋል